# የትግል ልዩ ምዕራፍ እድገቶች እና የምከታችን ቀጣይ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎች

**(ቁጥር - ሁለት)**

**በጥብቅ የሚያዝ**

የህ.ወ.ሓ.ት ጽ/ቤት

መስከረም 30/2013ዓ.ም

መቐለ

*ማውጫ* *ገጽ*

***መግቢያ***

**ክፍል አንድ፡- አለማዊ፣ ሀገራዊ እና ክልላዊ ሁኔታዎች እድገት ግምገማ.................................2**

1.1. ከሀገራችን አንፃር አለማዊ እና አካባቢያዊ አዳዲስ እድገቶች ...........................................2

አለማዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታ አዳዲስ እድገቶች .......................................................................2

1.1.1. በዞናዊ ሁኔታ አዳዲስ ክስተቶች/ እውነታዎች .........................................................8

1.2. በሀገራዊ ሁኔታዎች አዳዲስ ክስተቶች/ እውነታዎች ......................................................12

1.2.1. በጠላት ሁኔታ አዲስ ክስተት / እውነታ ...................................................................12

በብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ተጨማሪ ክስተቶች/ እውነታዎች ....................................17

በምርጫ ጉዳይ እና ሀገራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ክስተት/ እውነታዎች ............................19

በሀገራዊ ሁኔታ/ እውነታ ጠቃሚ ፖለቲካዊ ድምዳሜ ..........................................................22

1.3. ////////////////////////////////////////// .................................................................................................

////////////////////////////////////////////// ..........................................................................................

ወደ አዲስ ፖለቲካዊ ምዕራፍ ያሸጋገረ የትግራይ ምርጫ .......................................................28

በትግራይ የምከታ እድል እና ፈተና ድምዳሜ .................................................................31

**ክፍል ሁለት፡ የቀጣይ ምከታ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎች** ...............................32

2.1. የስትራቴጂዎቻችን፣ ስልቶቻችን እና አቅጣጫዎቻችን ገዢ መነሻዎች .............................32

2.2. የትግራይ የምከታ አቅም ወደ ማያዳግም ደረጃ ማሸጋገር ....................................................36

2.2.1. የትግራይ የምከታ አቅም የሚያጎለብት ስትራቴጂ...........................................................36

2.2.2. የማስፈፀሚያ ስልቶችን እና አቅጣጫዎችን ለይቶ መረባረብ ...........................................38

2.2.2.1. ፖለቲካዊ ስልቶችን እና አቅጣጫዎችን ለይቶ መረባረብ ...........................................38

2.2.3. ሁሉን አቀፍ ተቋማዊ አቅም የገነባች ትግራይ (ዲፋክቶ ትግራይ) ................................53

2.3. ለትግራይ ጥቅም ጠላትን መጣል እና የሀገሪቱ አዲስ ማስተካከያ ....................................53

2.3.1. ጠላትን የመጣል ዘመቻ ..................................................................................................53

2.3.2. ከአለም እና ሀገራት ምን እንማር .......................................................................................71

2.3.3. የዚህች ሀገር እና የትግራይ ህዝብ የመጨረሻ ጉዞ .........................................................79

2.3.4. ለትግራይ ህዝብ ዘላቂ ጥቅም የማያዳግም መፍትሄ .......................................................80

(አይደገምም - ኔቨር አጌን)

## የትግል ልዩ ምዕራፍ እድገቶች እና የምከታችን ቀጣይ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎች

## መግቢያ

በዚሁ በአይነቱ የተለየ የትግል መድረክ ህዝባችንን እየመራን ያለነው ታጋዮች የዚሁ መድረክ መሰረታዊ ጥያቄዎችን፣ የትግላችን አግባብ እና ለማሳካት የተነሳንለትን መሰረታዊ አላማ በግልጽ አስቀምጠን በትግላችን ሁሉ ምዕራፎች የአመለካከት አብርሆት ፈጥረን ያጋጠመንን ፈተና/ ተግዳሮት በጽናት ስንመክት ቆይተናል። በባለፉት ሁለት አመት ተኩል ጊዜያት ውስጥ ለኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይ ለትግራይ ህዝብ ደግሞ በአይነቱም ሆነ በይዘቱ ለየት ያለ አደጋ አጋጥሞን ቆይቷል። አሁንም ከዚሁ ነባራዊ አደጋ አልወጣንም። በትግላችን እና በጽናታችን ማገልገላችን ግን አይቀርም። የእስካሁኑ ትግላችን እና ምከታችን ለሌሎች ህዝቦች አብነት ሆኖ ተከታያችን፣ የትግል አጋራችን እንዲበራከት አድርገናል። መሆን የሚገባንን ያህል እና አሁን ለተፈጠረው ተፈላጊነታችን ሁሉን አቀፍ ጥንካሬ ከመኖር አንፃር አሁንም ከነችግራችን ብንሆንም እንኳ ሁኔታዎችን በመለወጥ ግን ቁልፍ ሀይል ሆነናል።

ጠላት በአንድ በኩል ውስጣዊ ግጭቶቹ እየጎሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ዲሞክራሲያዊ መገለል (ተነጣይነት) እየሰፋ በተለይ ደግሞ ከብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በከፍተኛ ደረጃ እየተነጠለ ቁልቁል ወርዷል። አሁን ጠላት (ተምታቶበታል) ተዛንፏል/ ተዛብቷል። ይህ ነው የሚባል ደጀን የለውም። በዚህ ላይ ከመስከረም 25 በኋላ ስልጣን ላይ መቆየት የማይገባው ኢ-ህጋዊ ሀይል ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ እድሜውን ለማራዘም ሲል የተስፋ መቁረጥ አውዳሚ እርምጃዎቹን ለመውሰድ ይጥራል። በአንፃሩ ደግሞ እኛ ህገ-መንግስቱን አክብረን፣ ታሪካዊ ምርጫ አካሂደን፣ ህጋዊ መንግስት መስርተን ምከታችንን ወደተሻለ ገዢ መሬት ከፍ እንዲል አድርገናል።

በመሆኑም በዚህ ወቅት በሁሉም መልኩ ፀረ ጠላት የሚደረገው ትግል ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ተሸጋግሯል። የተምታታበትን ጠላት መፈናፈኛ በማሳጣት በአጭር ጊዜ ለመጣል እና ለመቅበር ወደ የጋርዮሽ ስትራቴጂካዊ ጥቃቶች የተሸጋገረበት ወቅት ላይ ደርሰናል። አሁን ከባዱ እና የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሰናል። ጊዜም የለም አልቋል። መቆየት ብንፈልግም አንችልም። የትግሉ መልክም እየተቀየረ ነው። እንደመጣንበት እና እንደቆየነው ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ሁኔታዎቹን በጥንቃቄ ማየት፣ ወስነህ /ቆርጠህ በጽናት መታገልን የሚጠይቅ፣ ጉድለት ለመፈጸም እድል የማይሰጥ ሁኔታ ላይ ደርሰናል። ታግለን ያስመዘገብነው ድልን ለሌላ ፈተና/ ተግዳሮት እና ትግል እንድንዘጋጅ እያደረገን ነው። የያካሄደውነው ስኬታማ ምርጫ በሀገር ደረጃ ለሚደረገው ትግል ብቻ ሳይሆን ትግራይ ውስጥ ለሚኖሩን ስራዎችም ከፊት ለፊታችን ከባድ ፈተና እንዲኖር

አድርጓል፡፡ ይህ ጽሁፍ ባለፈው ጊዜ የተመለከትነውን የትግል ልዩ ምዕራፍ እድገት እና ቀጣይ አቅጣጫዎችን መነሻ አድርጎ ከዛበኋላ ያደገ/ የተከሰተ ሁኔታ እና ቀጣይ የሚኖረንን አቅጣጫ የሚመልስ ነው፡፡ ያለፈው ጊዜ ጽሁፋችን ይሁን ውይይታችን ወደ አንድ ወሳኝ ምዕራፍ አሸጋግረነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የወለዳቸው ጥያቄዎች መከተላቸው/ መምጣታቸው አልቀረም፡፡ ከዚህ በኋላ ወዴት ነን? ጠላት እንዴት ነው መውደቅ የሚችለው? የአብይ ቡድንን ከጣል በኋላ ወዴት ነን? ዘላቂ መፍትሄውስ ምንድን ነው የሚሆነው? የትግራይን ጥቅም የሚያረጋግጥ ዘላቂ ማስተካከያስ ምንድን ነው የሚሆነው? የሚሉ በህዝባችን፣ አመራራችን እና አባላችን ዘንድ ቁልፍ ጥያቄዎች ሆነዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች መነሳት ያለባቸው እና ሊመለሱ የሚገቡ ናቸው ፡፡

ስለዚህ ይህ የመነሻ ጽሁፍ የእስካሁኑ ምከታችንን ገምግሞ እነዚህን የመድረኩ ነባራዊ ወይም ወቅታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የተዘጋጀ ነው፡፡ በሁለት ክፍል ተከፍሎ ነው የቀረበው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል አሁን ያሉት እድገቶች እና ምከታችን የደረሰበትን ደረጃ የሚገመግም ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የትግላችን ቀጣይ ስትራቴጂ፣ ስልት እና አቅጣጫዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህ ክፍል የመድረክ ተልዕኮ እና ቁልፍ ጥያቄዎችን ለመመለስ፣ ምርጥ ሀሳቦችን ለመለየት፣ ለማቀናጀት እና ለማብላላት ነው የሚሞክረው፡፡ ያለቀለትን ነገር ማቅረብ አይቻልም፡፡ በመሰረታዊው የመርህ/ አቋም ጥያቄዎች እና ሀሳቦች ዙሪያ መግባባት ላይ ተደርሶ፣ ይህንን የመዘርዘሩ ጉዳይ በቀጣይ መሟላቱ ግን የማይቻል አይደለም፡፡

## ክፍል አንድ፡- አለማዊ፣ ሀገራዊ እና ክልላዊ ሁኔታዎች እድገት ግምገማ

### 1.1. ከሀገራችን አንፃር አለማዊ እና አካባቢያዊ አዳዲስ እድገቶች

#### 1.1.1.አለማዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታ አዳዲስ እድገቶች

ባለፈው ጊዜ አለማዊ ሁኔታው/እውነታው ከሀገራችን ጋር ያለውን እና የነበረውን ትስስር በየጊዜው እየተመለከትነው ቆይተናል፡፡ በሁሉም ውይይቶቻችን ቢሰፋም ቢጠብም ይህንን እያነሳን የምንመለከተው ከነባራዊው አለማዊ ሁኔታ ራሳችንን ውጪ አስወጥተን ማየት ስለማንችል ነው፡፡ በብዙ ሀገራት ልክ በሀገራችን አሁን እንዳጋጠመው ሁሉ በውስጣዊ ጉዳዮቻቸው ችግር ሲያጋጥማቸው እና ከመስመሩ ሲዛነፉ የአለማችን ልዕለ ሀያላን መንግስታት ሁኔታዎቹን በፍጥነት ተቀብለው በተወሰኑት ላይም ራሳቸው መሪ ሆነው እነርሱ በፈለጉት እንዲሄድ ምን ድረስ እንደሚረባረቡ በራሳችን ላይ እያየነው ነው፡፡ ስለዚህ ወደድንም ጠላንም ከእነዚህ ረጃጅም እጆች ልንደበቅ አንችልም፡፡ ሁኔታዎቹን በየጊዜው እያወቅን እና እየተገነዘብን፣ ፈተና/ ተግዳሮት እና እድሎቹን ለይተን እድሎቻችንን ለማስፋት የሚገጥመንን ፈተና ወይም ተግዳሮት ለመቀነስ

መስራት ነው ያለን አማራጭ፡፡ ይህንን ነባራዊ ሁኔታ መገምገም ለአጭር ጊዜ በሚኖረው ፋይዳ ብቻ መሆን የለበትም፡፡ በቀጣይ ምዕራፎች የሚኖሩ እድገቶች/ ክስተቶች ለራሳችን በሚኖረው ጠቀሜታ መተንበይም አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ሀገራት በተለይ የጎረቤት ሀገራት ከእኛ ጋር ሲገናኙ ሀገራዊ ጥቅማቸውን መሰረት ያደረገ ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡ የሀያላን ጌቶቻቸው ጥቅም እና ፍላጎት አስቀምጠውም/ አስቀድመውም ስለሚሆን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ በእጅጉ የተወሳሰበ እንደሚያደርገውም መገመት አይከብድም፡፡ ስለዚህ በዚህ እና ሌሎች ምክንያቶች ነው በየጊዜው ማየት/ መመልከት አስፈላጊ የሚሆነው፡፡

በቆየው አለማዊ እድገቶች/ ክስተቶች በተለይ ኮቪድ-19 ያስከተለው ኢኮኖሚያዊ ድቀት እና በቆየው ፉክክር ተጨማሪ እና ሌላ መልክ ይዞ የነበረውን መፋጠጥ/ መጠባበቅ ወደ ከፍተኛ ደረጃ አሸጋግሮት እንደሚገኝ አይተነው/ ተመልክተነው ነበር፡፡ የስትራቴጂካዊ ሽግሽግ አሰራርም ሆነ የሚኖረው ለውጥ ለሀገራት እና ህዝቦች ትልልቅ እድሎችን እና ተግዳሮቶችን ይዞ መምጣቱም አይቀሬ ነው፡፡ የሚፈጠረውን እድል በአግባቡ ለመጠቀም እና የሚያጋጥመውን ችግር መቀነስ የሚችል ትልቅ የቴክኖሎጂ አቅም የሚፈጥር እና ግዙፍ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለመፍጠር እድል የሚሰጥ ሁኔታም መኖሩ አይቀርም፡፡ በ25 አመታት ውስጥ ትግራይን ትራንስፎርም ማድረግ አለብን የሚል ሀሳብ አንዱ መነሻው በሚኖረው ጊዜ እና ሂደት በአለም ደረጃ ትልልቅ ለውጦች መከሰታቸው/ መምጣታቸው ስለማይቀር የሚፈጠሩን እድሎች ለመጠቀም እና የሚያጋጥሙንን ከባድ ፈተናዎች በብቃት ለመመከትም ተስተካክለን ለመቆየት/ ለመጠበቅም ነው፡፡ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት በቀጣይ በመካከለኛ እና አጭር ጊዜ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን አርቀን ማየት እና አስፍተን ልንመልስም ይገባል፡፡ ለአሁን ግን ከነባራዊ ሀገራዊ ሁኔታ ጋር ተዛምዶ የሚኖር የአጭር ጊዜ ክንዋኔ እና ባደጉት ዋነኛ ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥተን እናነሳለን፡፡

ምዕራባዊያን በተለይ የአሜሪካ አስተዳደር በአፍሪካ የሚኖራቸውን ቦታ ከፍታ ለመጨመር በበዙ አካባቢዎች ሀይሉን እያሰባሰበ በተለይ በአካባቢያችን የሚጠቀምባቸው የሚጠበቅላቸው ዞናዊ ጉልበተኞችን በማስታጠቅ የየአካባቢው አውራዎች እዲፈጠሩ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ አሁንም ይህንን አጠናክረው ዘልቀውበታል፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት ኮቪድ-19 የፈጠረውን መናጋት፣ የግሎባላይዜሽን ህጎች ቅኝት የሚፈልግ ሁኔታ መፍጠሩን እና ስትራቴጂካዊ ጥቅሞቻቸውን የሚያሟላ ሁኔታ ለመፍጠር ዝግጅት እያደረጉ መቆየታቸው፣ በቻይና በኩል የቆየው በአፍሪካ ተደላድሎ የመቆየት እንቅስቃሴ፣ ሩሲያም በበኩሏ በቅርብ ጊዜ ከደቡብ አፍሪካ ጋር በጀመረችው አዲስ አጋርነት/ እንቅስቃሴ፣ በአሜሪካ በኩል ደግሞ የቻይና እና ሩሲያ የማገት (ኮንቴንመንት)

ፖሊሲ ለመተግበር በሰፊው ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ይህንን በሚያስተማምን ደረጃ እንዲፈጽሙ በአፍሪካ ቀንድ ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ያላት፣ ብዙ ህዝብ የሚኖርባት ትልቋ ሀገር ኢትዮጵያ በእጃቸው እንድትገባ ብዙ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ይህንን ተልዕኮዋቸውን ሊያስፈጽምላቸው የሚችል ሀይልም በቀላሉ አግኝቷል፡፡ የአብይ ቡድን ይህንን ተልዕኮ ተቀብሎ በእንቅስቃሴ ላይ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ እነርሱ የተመኙትን ሊተገብርላቸው አልቻለም፡፡ የጀመሩት ሪፎርም አደጋ ላይ መውደቁን እና አብይ ይዞት ሊቀጥል እንደማይችል፣ የሱ ፍላጎት እና ፍላጎታቸው እንደማይጣጣም አረጋግጠዋል፡፡ የእነሱን ፍላጎት ማስፈፀም ይቅር እና ለራሱ በዚሁ የሚቀጥልበት እድል እደሌለው በገሀድ እየታየ ስለሆነ የሞተን ፈረስ አይጋልቡም፡፡ ስለዚህም ሌላ አማራጭ ለማፈላለግ ተገደዋል፡፡ በዚህ ወቅት አንዱ ዋነኛው ክስተት/ እድገት እዚህ ላይ የመጣው ለውጥ ነው፡፡

ጠላት በምዕራባዊ አለም ያለውን ቅቡልነት ቶሎ እንዲወርድ በማድረግ ላይ ሌሎች ምክንያቶችም አሉ፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው አሜሪካ የምርጫ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ ፕሬዝደንት ዶናልድ ትራምፕ መጪውን ምርጫ ለማሸነፍ ብዙ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህ ምርጫ እንዲመረጥ በሰፊው ሲሰራበት የቆየ እና ያለው አንድ ቁልር ነገር ደግሞ በመካከለኛ ምስራቅ ያለውን ችግር በመፍታት የእስራኤልን ትልቅ ድጋፍ ማግኘት ነው፡፡ የእስራኤልን ጥቅም በአስተማማኝ ደረጃ የሚያረጋገጥ ያሉበትን መሬት አስተማማኝ እንዲሆን በማድረግ ፍልስጤምን ደግሞ እስራኤል የያዘውን ከያዘ በኋላ ሉአላዊነታቸው እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ የሚል ነው፡፡ በመካከለኛው ምስራቅ አዲስ ታሪክ ሰርቷል ተብሎ እንዲመረጥ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ይህንን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የአረብ ሀገራት ከጎኑ እንዲሰለፉ ማድረግ ዋናው ጠቃሚ ነጥብ ነው፡፡ ይህንን የዶናልድ ትራምፕ ፍላጎትን እና የእስራኤልን ጥቅም ለማረጋገጥ የአረብ ሀገራት ቁልፍ ተላጊነት አላቸው፡፡ የአረብ ሀገራትን በማግባባት እና በማሳመን ረገድ ትልቁን ሚና መጫወት የሚችሉ ደግሞ እነ ግብጽ ነበሩ፡፡ ግብፃዊያንም ይህንን ተቀብለው እንቅስቃሴውን ሲጀምሩ በእነርሱ በኩል እንዲፈታ የሚፈልጉትን የህዳሴው ግድብ ጉዳይ አላቸው፡፡ ስለዚህ አሜሪካ ይህንን በመፍታት እጇን እንድታስገባ ፍላጎታቸውን ገልፀዋል፡፡ የዶናልድ ትራምፕ አስተዳደር ይህንን ለመፍታት ተነሳሽነቱን ወስዶ ወደ እንቅስቃሴ ገብቷል፡፡ አሜሪካም ሆነ የአለም ባንክ እንታዘባለን በሚል ገብተው የግብጽን ጥቅም በሚያስጠብቅ መንገድ እንዲፈፀምም ተንቀሳቅሰዋል፡፡

አሜሪካ የአብይ ቡድን በህዳሴ ግድብ ማድረግ የሚገባውን መመሪያ መስጠት ብቻ አልነበረም፡፡ ከፍ ሲል ከገለጽነው ፍላጎት የሚመነጭ በአብይ በኩል ሱዳን ከእስራኤል እና አረብ ሀገራት ጋር የተሻለ ዝምድና እና ግንኙነት እንድትፈጥርም ጥረት እንዲያደርግ እቅዳቸውን/ ትዕዛዛቸውን ተቀብሏል፡፡ አብይም ይህንን ለእኔ ተውት፣ አደርገዋለሁ ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ አብይ የተቀበላቸው እነዚህ ሁለት ተልዕኮዎችን መፈፀም አልቻለም፡፡ በህዳሴ ግድብ በኢትዮጵያ ህዝብ ያጋጠመውን ሰፊ ተቃውሞ ፈርቶ የቀረበለትን ውሳኔ ተቀብሎ መፈፀም አልቻለም፡፡ በሱዳንም የተሰጠውን ተልዕኮ መፈፀም አልቻለም፡፡ ይልቁንም ያልፈጸመውን ፈጽሚያለሁ በማለት የአሜካሪካን መንግስት የሚያዋርድ ተግባር ነው የፈፀመው፡፡ ሱዳን ለእርሱ የተባለውን ተቀብለው መፈጸም ይቅርና ጊዜ ሰጥተው ሊያዳምጡትም አልፈቀዱም፡፡ በዚህ ምክንያት በትራምፕ አስተዳደር የነበረው ግንኙነት እና ተአማኒነት በእጅጉ እንዲበላሽ እና ትርጉም የሌለው ሀይል አድርገው መውሰዳቸው ሌላው የነበረው ምክንያት ይህ ነው፡፡ ስለዚህ የአብይ ቡድን በአሜሪካ የነበረው ድጋፍ አሁን የለም ሊባል ይችላል፡፡

ከዚህ አልፎ በመጪው ምርጫ ዴሞክራቶች ሊመረጡ የሚችሉበት እድል ሰፊ ይመስላል፡፡ የአሜሪካን ምርጫ መገመት ከባድ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ባለው ሂደት ባይደን እየመራ ነው፡፡ ባይደን ከተመረጠ ደግሞ የኦባማ ቁልፍ ሰዎች ወደ ስልጣን እንደሚመጡ ይገመታል፡፡ እዚህ ስበብስብ ውስጥ ያሉት ሰዎች ደግሞ ሪፎርም በሚሉት ላይ ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆንም እንኳ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ያላቸው አቋም የተሻለ ይመስላል፡፡ የተሻለ ግንኙነት ለመፍጠርም እድል ይኖረናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንድ አንድ የአሜሪካ ግዛቶች የኦሮሞ ተወላጆች እንቅስቃሴ በምርጫው ውጤት ላይ ቀላል የማይባል ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በተለየ ባይደንን ደግፈው እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ከዶናልድ ትራምፕ በኋላም ቢሆን የአብይን ቡድን ሊሰማው የሚችል አይኖርም፡፡ በመሰረቱ አሜሪካ በባህሪው የራሱን ጥቅም ማዕከል ያደረገ አማራጭ እያስቀመጠ ስለሚሰራ ያሏቸውን ጥቅማ ጥቅሞች/ ፍላጎቶች በሙሉ በአብይ ሳጥን (ቦክስ) ውስጥ አስቀምጠው ይሄዳሉ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ከዚህም አልፎ በውጪ ሀገር እየተካሄደ ያለው ፀረ አብይ ንቅናቄ/ እንቅስቃሴ እና ሀገር ውስጥ እያጋጠመ ያለው ሰብዓዊ ቀውስ ሳቢያ ብዙ አካላት ፀረ አብይ አቋም እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡

የአሜሪካ ኮንግረንስ አባላት፣ አይሲጂ፣ ፍሪደም ሀውስ፣ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ… እያካሄዱት ያለው ተቃውሞ እና እንቅስቃሴ የዚህን ቡድን ቅቡልነት በእጅጉ ሊያወርድ እና ራቁት ሊያስቀረው የሚችል ነው፡፡ ከእነዚህ አዳዲስ እውነታዎች ተነስተን አሜሪካ ከአብይ ጋር ለመቀጠል እየፈለገች

አይደለም። ከአብይ ጋር መቀጠል አይፈልጉም ማለት ግን ሪፎርም ማድረጉን ይተውታል ማለት አይደለም። ሌሎች አማራጮችን ተጠቅሞ እንዲቀጥል ከማድረግ ወደኋላ ሊሉ አይችሉም።

በአውሮፓ አብዛኞቹ ሀገሮች ሀገር እየፈረሰች ነው የሚል ሰፊ ስጋት አለባቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጠር በሚችል አለመረጋጋት ምክንያት የአፍሪካ ቀንድ በአጠቃላይ ይታመሳል የሚል ስጋት አለባቸው። በዚህ ሊፈጠር የሚችል አለመረጋጋት ከዚሁ እየፈለሰ የሚሄደው ስደተኛም በእጅጉ እያሳሰባቸው ነው። ሀገር ውስጥ እያጋጠመ ያለው መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ይህንን ተከትሎ በውጪ ሀገር እየተካሄደ ያለው ሰፊ ተቃውሞ አብይ ይህችን ሀገር መምራት የሚችል አይደለም ሲሉ እያነሱ ነው። እኛ የያዝነውን አቋም እና መፍትሄም መስማት ጀምረዋል። ከዚህ በመነሳትም ብዙ የአውሮፓ መንግስታት ሆነ የሩቅ ምስራቅ ሀገራት ከኢትዮጵያ ውጪ ከእኛ ጋር የመገናኘት ፍላጎት እያሳዩ ነው። አሁን የአውሮፓ ህብረትም ሆነ የአውሮፓ ሀገራት በተናጥል ወደ ድርድር (negotiation) ሰፊ እና ጥቅል ክርክር እና ውይይት (ዲያሎግ) እንድንገባ ግፊት እያደረጉ ነው። መፍትሄው ውይይት (ዲያሎግ) ነው የሚል አቋም እየያዙ ነው። በእነዚህ በኩል የሚመጣ ድርድር እና ውይይት ደግሞ በብዙ የአፍሪካ አካባቢዎች የታየውን ፍላጎታቸውን የሚያሟላ እንዲሆን የሚጥሩ ይሆናል። ይህንን ተከትሎም አንተ ይህንን አድርግ እናንተ ይህንን ፈጽሙ የሚል መፍትሄ የማያስገኝ እና ትግሉን ወደኋላ የሚመልስ ሁኔታ ሊመጣ ይችላል። በመሰረቱ እነርሱ ከሚመሩት ድርድር መፍትሄ ማግኘት የሚታሰብ አይሆንም። እንደተለመደው የማያቋርጥ፣ የተራዘመ እና አሰልቺ ድርድር እንዲደረግ እና በዚህ ደግሞ ሁሉም ዘንድ እንደሚታየው የተቋሞቻቸው ማስማሪያ እና አዲስ ስራ መፍጠሪያ ለማድረግ ነው የሚጥሩት። ወጣም ወረደ በአንድ በኩል ወሳኝ መልክ/ይዘት ያለው ሆኖ እየመጣ ያለው ይህ ነው። ይህ እየታየ ያለው እውነታ/ ክስተት በአንድ በኩል በአብይ ላይ እየወሰዱት ያለውን አቋም ደግፈን እንዲጠናከር ለማድረግ በሌላ መልኩ ደግሞ ሊመጣ የሚችለውን የድርድር/ ውይይት ሀሳብ ግልጽ የመደራደሪያ ስትራቴጂ ቀርፀን ጠላትን ለመደምሰስ ለሚደረገው ትግል የማያደናቅፍ፣ የትግራይን ነባራዊ እና ዘላቂ ጥቅም የማይነካ፣ በድርድር የማንሻገራቸውን መሰረታዊ አጥሮችን አስቀምጠን ጥቅማችንን እና ፍላጎታችንን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን እንሰራለን። በዚህ ረገድ የሚኖረን ስትራቴጂ ከቆይታ በኋላ በዝርዝር የምንመለከተው ሆኖ ባለፉት 2 አመታት ባካሄድነው ትግል እና የአለምን ሙሉ ቀልብ የሳበ በቅርብ ጊዜ ያካሄድነውን ምርጫ ተከትሎ ተፈላጊነታችን በተወሰነ ደረጃ ከፍ ብሏል። ህ.ወ.ሓ.ትን እና የትግራይን ህዝብ በማግለል የኢትዮጵያን ችግር መፍታት አይቻልም እያሉ ነው። ለወደፊቱ የመደራደር አቅማችን ጎልብቶ እንዲወጣ ተፈላጊነታችንም

እንዲያድግ በርትተን መስራት አለብን፡፡ ካልሆነ ከጥቅሙ ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው፡፡ በአብይ ጉዳይ ላይ እየያዙት ያለው አቋም ግን ለትግላችን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡

የመካከለኛው ምስራቅ ሁኔታ/ እውነታ ከአለማዊ ሁኔታ/ እውነታ ለብቻው ተነጥሎ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ መጠነ ሰፊ ቀውስ ያልተለየበት - ከሀያላን ሀገራት በላይ እየታመሰ የሚገኝ አካባቢ ነው፡፡ የእነዚህ ሀገራት አሰላለፍ የአፍሪካ ቀንድ - ጂኦ-ፖለቲካል ሁኔታን ቀይሮታል፡፡ ምዕራባዊያን እየተፈጠረ/ እየተከሰተ ያለው ሁኔታ በውስጥ ጉዳዮቻቸው ላይ ተጠምደው ስለቆዩ የገልፍ ሀገራት በውክልና በአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች እንዲገቡ እና የፈለጉትን እንዲፈጽሙ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ አሜሪካ የደህንነት ስትራቴጂውን ለመፈፀም እስራኤልን፣ ሳውዲ አረቢያን እና ኤምሬትን በመወከል ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ከአሜሪካ ምርጫ ጋር ተያይዞም ጉልህ ትብብር እና ወዳጅነት ፈጥረው ነው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት፡፡ በዚሁ እንቅስቃሴም የአብይ ቡድን ያለው ሚና ቀደም ሲል አይተነዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ከእነዚህ ሀገራት ጋር ተፈጥሮ የነበረው ዝምድና በእጅጉ ተዳክሟል፤ የዚሁ ቅጥያ ነው - አብይ የተሰጠውን ተልዕኮ መፈፀም ስላልቻለ ግብጽ በህዳሴ ግድብ ዙሪያ ያመነጨችውን ሀሳብ በአረብ መንግስታ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ከአብይ በተቃራኒ ለመቆም የቻሉት፡፡ ከኢምሬትም ሆነ ሳውዲ አረቢያ መጀመሪያ ላይ የነበረው ድጋፍ እና ትብብር እየቀጠለ አይደለም፡፡ ተገብቶለት የነበረው ስለትም አላገኝም፡፡ ስለዚህ ጠላት ከሁሉም ጋር ሳይሆን ተነጥሎ የቀረበት ሁኔታ ነው እየተከሰተ ያለው፡፡ እየተመለከትነው ከቆየነው አካባቢያዊ ክስተት ተነስተን የምንደርስበት ድምዳሜ አንዱ ሁሉ መንግስታት በአብይ እምነት እያጡ ከእነርሱ እየተነጠለ እየሄደ መሆኑን ነው፡፡ ሁለተኛው ጠቃሚ ነጥብ ችግሩ በድርድር እንዲፈታ ተነሳሽነት እንዲወስድ እየፈለጉ መሆናቸውን፣ ሶስተኛው ጠላትን ለመገርሰስ በሚደረገው ትግል አንዱ አዎንታዊ ጎኑ በቀጥታ ወደ ውስጣችን ዘለው ሊገቡ የሚችሉበት እድል ጠባብ መሆኑ ነው፡፡ በሩቁ ከማስፈራራት፣ ተላላኪ ከመላክ እና ማዕቀብ ከመጣል የሚዘል ሊሆን እንደማይችል አይተን ትግሉ እንዲቀላጠፍ/ እንዲሳለጥ ማድረግ የምንችልበት እድል እየሰፋ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ካለንበት ጨምረን አቅማችንን እንዲጎለብት ካደረግን ተፈላጊነታችን እየጨመረ አንዱ የዚሁ አካባቢ አቅም አድርገው ሊመለከቱን ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ተግዳሮቶች የሉበትም ማለት አይደለም፡፡ አብይን መተካት እንጂ ሪፎርሙ ወደኋላ እንዲመለስ አይፈልጉም፡፡ መፍትሄ የሚሉም በተለይ እነሱ ከገቡበት በማያቋርጥ ንትርክ ውስጥ እንድንኖር የሚያደርግ ነው፡፡ በዋናነት ደግሞ ምዕራባዊያኑ በመስመራችን/ መርሆዎቻችን/ አቋማችን ሆነ እምነቶቻችን ላይ ያላቸው ጥላቻ እና ጥርጣሬ ለወደፊቱም ፈተና ነው፡፡ በጥቅሉ ግን በዚህ ወቅት

ጠላት ከሁሉም እየተነጠለ መሆኑን፣ ለእኛ የተሻለ ሁኔታ እና የመላወሻ እድል እንዳለን መደምደም እንችላለን፡፡

### 1.1.2. በዞናዊ ሁኔታ አዳዲስ ክስተቶች/ እውነታዎች

ባለፉት አመታት የአፍሪካ ቀንድ ጂኦ-ፖለቲካዊ እና በቀይ ባህር አካባቢ ሁኔታ መለዋወጥ በአለማችን ትልቅ ተጽእኖ የሚፈጥር አካባቢ እየሆነ እንደሚገኝ ተመልክተን ነበር፡፡ ከእኛ ጋር የሚኖራቸው ዝምድና እና ተጽእኖም መጠን እና ስፋቱ እንደፈለገ ቢሆንም እየነካካነው ቆይተናል፡፡ አሁን ያ ሁኔታ/ ክስተት እየተወሳሰበ፣ ሌላ መልክ እየያዘ እየሄደ ነው፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ግጭት እና ሰብዓዊ ቀውስ ከነበረበት እየጨመረ እየሄደ ነው፡፡ በቀይ ባህር አካባቢ ያለው ሁኔታም ይህንን በቀጥታ እያባባሰው ነው፡፡ የቀይ ባህር ጂኦ-ፖለቲካል ሁኔታ እና በዚሁ አካባቢ ፖለቲካዊ ክስተቶች/ እውነታዎች ዙሪያ የመጣው ለውጥ የአፍሪካ ቀንድ የቀውስ ማዕከል እና ውስብስብ እንዲሆን እያደረገው ነው፡፡ የእነዚህ ሀገራት ውስጣዊ ሁኔታ ሲቀየር ከትልልቅ ሀገራት ጋር የሚኖር ግንኙነትም እየተለዋወጠ ነው፡፡ እነዚህ ልዕለ ሀያላን መንግስታትም ሆነ የገልፍ ሀገራት በጎረቤት ሀገሮች የሚኖራቸው ጥቅም እኛን በአዎንታዊ እና አሉታዊ መንገድ ተጽእኖ የሚፈጠርበት ሁኔታ እየተከሰተ ነው፡፡ ስለዚህም ከእነዚህ ሀገራት ጋር የሚደረግ ግንኙነት ከራሳቸው ሀገራዊ / ብሔራዊ ጥቅም ብቻ ሳይሆን የሀያላን መንግስታት እና የአረብ መንግስታት ፍላጎት እና ጥቅም ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ ሁኔታ/ እውነታ እየታየ ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚኖረው ለውጥ ለግንኙነታቸውን ወሳኝ እንደሆነ ልናስተውለው ይገባል፡፡

ሀይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ወታደራዊ እና የደህንነት ጉዳይ ምክንያት ተደርጎ እየተከሰተ ያለው ፉክክር በቀይ ባህር እና አፍሪካ ቀንድ ላይ ከባድ ስጋት እንዲያንዣብብ ምክንያት ሆኗል፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በአንድ በኩል የባህረ ሰላጤ ሀገራት እያደረጉት ያለውን ፉክክር ግዳይ ሲሆኑ በሌላ መልኩ ደግሞ ፉክክሩ የራሳቸውን ውስጣዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ሲጠቀሙበት እየታየ ነው፡፡ ስለዚህ የአፍሪካ ቀንድ እና ቀይ ባህር የሀያላን ተፎካካሪዎች የጦርነት አውድማ ከመሆኑም በላይ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በዚሁ ፉክክር ውግንናቸውን ለመለየት እየተገደዱ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ የፖሊሲ ነፃነት እያጡ በደንበኛ ሀገር (ክላይንት ስቴት) ባህር እንዲይዙ ሲደረግ የቆየው እንቅስቃሴ አሁን ተጠናክሮ ወጥቷል፡፡ አብዛኞቹ የኢጋድ አባል ሀገራት የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት እና አጋር/ ጥላ የሚሆንባቸው ሀገር ለማግኘት ሲሉ በአረብ ሀገራት እጅ ወድቀዋል፡፡ በኢጋድ አባል ሀገራት

የተፈጠረው/ የተከሰተው ውስጣዊ ተጋላጭነት ድርጅቱን አጋጥሞታል፡፡ ለውጪ ሀይሎች ጣልቃ ገብነትም አጋልጦታል፡፡

ይህ የሚያሳየን የአፍሪካ ቀንድ ውስጣዊ ችግር የፈጠረው ቀውስ ለውጪ ሀይሎች መጠነ ሰፊ ጣልቃ ገብነት የተጋለጠ አካባቢ መሆኑ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ለእኛ የሚኖረው ተግዳሮት/ ፈተና ሆነ ጸጋ ሊታይ የሚችል ደርዝ መኖሩ አይቀርም፡፡ አንዱ ጠቃሚው ነጥብ ግን ኢጋድን በማዳከምም ሆነ የቀጠናው ችግሮቹን በማወሳሰብ ሂደት የኢሳያስ እና አብይ ሚና ትልቅ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ የዞናችን/ ቀጠናችን ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋር የነበራቸው ዝምድና እየተቋረጠ መከራን እንጂ መፍትሄን ማምጣት የማይችል የወቅቱ እንቅፋት/ መንግስት እያሉት ይገኛሉ፡፡ የአፍሪካ ህብረትም ቢሆን ተጽእኖ የሚያሳድር መሪ የለውም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታም ተስፋ እየቆረጡ ቀስ በቀስ ማዕከላቸውን ከአዲስ አበባ አንስተው ወደ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ለመሄድ በማመንታት ላይ ናቸው፡፡

በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የአካባቢያችን ሀገራት ከእኛ ጋር ያላቸው ሁኔታ አሳጥሮ ማየት ጠቃሚ ነው፡፡ ሱዳን በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ፀጥታዊ ወዘተ... ጠቀሜታ ምክንያት የዲፕሎማሲ ስራዎችን ቁልፍ ማዕከል እንደሆነች ብዙ ያልንበት ጉዳይ ነው፡፡ ሱዳን በብዙ መልኩ ጥቅሞቻቸው ከጥቅሞቻችን ጋር የተያያዘ/ የተቆራኘ ቢሆንም እንኳ በአንድ በኩል ከአሜሪካ ማዕቀብ መውጣታቸው፣ ከእስራኤል ጋር የተጀመረው ግንኙነት፣ በተቋሚዎች መካከል የተፈጠረው ስምምነት የተሻለ ሁኔታ እንዲኖር የሚያደርግ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የአሜሪካ ወደ ሱዳን መግባት መጀመር እና በውስጣቸው ያለውን ከባድ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እና ያልተረጋጋ መንግስት ስራዎቻችንን ሊያወሳስበው እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ በዚህ ላይ አብይ ቡድን በሁሉም የሱዳን አካባቢዎች የእኛን እንቅስቃሴ ለመከታተል እና ለማደነቀፍ ከኤምባሲ ጀምሮ በእያንዳንዱ ጫፍ ብዙ የሰው ሃይል አሰማርቶ እየሰራ ነው፡፡ በኢትዮጵያ እና ሱዳን መካከል ያለው የድንበር ውዝግብ/ ጥያቄ መፈታት የሱዳን ፍላጎት ጠንከር ያለ ነው፡፡ የአብይ ቡድን ደግሞ ችግሩን ለመፍታት ከትግራይ አካባቢ እንጀምር እና ቀስ እያልን ወደሌላው አካባቢ እንሄዳለን የሚል አማራጭ በማቅረብ፣ ይህንን ተጠቅሞ በመካከላችን መቃቃር እንዲፈጠር ጥረት እያደረገ ነው፡፡ መግቢያ እና መውጫ ሊያሳጡን ከሻዕቢያ ጋር በጋራ ሆነው እየሰሩ ነው፡፡ እርግጥ ነው ሱዳን እየተከናወነ ያለውን ሴራ ተገንዝበው ሊቀበሏቸው አልቻሉም፡፡ ቁም ነገር እንዳለው ሀይል አድርገውም እያዩት አይደለም፡፡ ስለዚህ ሱዳን እስካሁን ድረስ ስለእኛ አዎንታዊ ሚና እየተጫወቱ ነው ያሉት፡፡ ለወደፊቱም አብረን እንድንሰራ ይፈልጋሉ፡፡ የመግቢያ እና መውጫ አስተማማኝ

ማድረግ ብቻ ሳይሆን ከዚያ እየተነሳን በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ለምንሰራው ፖለቲካዊ ስራም ጠቀሜታው መተኪያ የለውም።

የጅቡቲ እና የአምባገነኑ ቡድን ግንኙነት እስካሁን ድረስ እንደቀረፈደ ነው። አዲስ የተፈጠረ መሻሻልም የለም። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየተከሰተ ያለውን መጥፎ ሁኔታ እያዩም እንደ አማራጭ ሊያዩት አይፈልጉም። በኢህአዴግ ዘመን የነበረውን የተሻለ ዝምድና እያዩ ከቻይና ጋር ያላቸውን ጥብቅ የጥቅም ትስስር፣ በኢሳያስ ቡድን ላይ ያለን የጋራ አቋም እና በእነዚህ ሁለት አመታት ለመብታችን እና ጥቅማችን ያደረግነውን ትግል አይተው ከእኛ ጋር የተሻለ መቀራረብ እና መተጋገዝ እንዲፈጠር ጥረት እያደረገ ነው። የሶማሊያ ፌደራል መንግስት ከአብይ ጋር ያለው ግንኙነት እንደነበረው ነው። በክልሎቹም ከአብይ ጋር አብሮ መስራት የሚፈልግ የለም። ፑንትላንድ፣ ሶማሌላንድ፣ ጁባ ላንድ ሁሉም ከአብይ በተቃራኒ ናቸው። ከእኛ ጋር አብረው ለመስራት እና ለመገናኘት ያላቸው ፍላጎትም ትልቅ ነው። ከኬኒያ ጋርም በተመሳሳይ ግንኙነቱ የደፈረሰ ነው። በጥቅሉ በዚህ ዞን ውጥም ጠላት ተቀባይነት የሌለው፣ የሚሰማው የሌለው ሆኗል። በአንፃሩ ከእኛ ጋር መገናኘት እና አብሮ መስራት የሚፈልጉ ናቸው። እስካሁን ድረስ ባደረግነው እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች እየታዩ ናቸው።

ኤርትራን አስመልክቶ ባለፈው ግምገማችን ምን አይነት መልክ ይዞ እየሄደ እንደሆነ አይተነው ነበር። ያስቀመጥነው ግምገማም የኢሳያስ ቡድን በኢትዮጵያ ጉዳይ በተለይ ደግሞ ህ.ወ.ሓ.ትን እና የትግራይን ህዝብ ለማስተኛት በቀጥታ እጁን አስገብቶ እያመሰ መሆኑን አብይ እና ኢሳያስ በወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን ግንባር ፈጥረው ሀገር እያፈረሱ መሆኑን ደምድመን ነበር። አሁንም ቢሆን ይኸው ተግባር በሁሉም መልኩ ተጠናክሮ እየቀጠለ ነው። የአንዳቸው ህልውና በአንዳቸው ህልውና መጥፋት ላይ እንደሚመሰረት አስበው እየሰሩበት ነው። በግልጽ የሚታይ ወታደራዊ መደጋገፍ ለማድረግ የሚያግዝ ስልጠና፣ የስለላ መዋቅር ስምሪት፣ የጥበቃ እና ገዳይ የሰው ሃይል ስምሪት እያደረጉ ይገኛል። አልሳካ ብሏቸው እንጂ የተለያየ መልክ ያለው ግብረአበራዊ ስራ ለመስራትም ሲሞክሩ ነው የቆዩት። ለወደፊቱም ኢሳያስ እስካለ እና ማድረግ እስከቻለ ድረስ ህ.ወ.ሓ.ትን ለማጥፋት ይሰራል። ስለዚህ አሁንም ቢሆን ኢሳያስ ግልጽ እና የአሁኑ ዋነኛ ጠላት ሆኖ ነው እየቀጠለ ያለው።

በሌላ መልኩ ደግሞ በኤርትራ ፀረ-ኢሳያስ ቡድን የህዝብ ተቃውሞ በእጅጉ እየጨመረ ነው የሚገኘው። ብዙ ፖለቲካዊ ሀይሎችም ሆነ በውጪ ሀገር የሚኖሩ ኤርትራዊያን ከወያኔ ጋር አብሮ መስራት እንደ መክዳር አድርገው ሲመለከቱት የነበሩት ዛሬ በግልጽ ተሰብሯል።

ከህ.ወ.ሓ.ት ጋር ከትግራይ መንግስት ጋር መስራት አለብን የሚል ተጠናክሮ መጥቷል፡፡ በቅርብ ጊዜ የነበረውን እንኳ ብንመለከት የኤርትራ ወጣቶች የጀመሩት የ ‹‹ይአክል/ይበቃል ህዝባዊ ንቅናቄ››፣ ሌሎች ታዋቂ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የተሻለ የትግል መንፈስ ይዘው ከእኛ ጋር አብረው ለመስራት እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ ያጋጠመንን የአንበጣ መንጋ ወረራ ለመመከት እየተደረገ ባለው ጥረት ሂደት ኤርትራዊያኑ እያደረጉት የሚገኘው ድጋፍም አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በኤርትራ ህዝብ ዘንድም ቢሆን በኢሳያስ ላይ እያሳየው ያለው የከፋ ጥላቻ ከእንግዲግ ወዲያ ይህ ስርዓት ይብቃን፤ አብረን መኖር የለብንም - ብሎ የጨረሰ ይመስላል፡፡ የኤርትራ ሰራዊትም ቢሆን ጥያቄዎችን እያነሳ ነው፡፡ ከትግራይ ጋር ወደ ጦርነት መግባት የለብንም የሚል ጥያቄም እየተነሳ ነው፡፡ ከየአህዱዎቹ እየወጣ የትም የሚሄድ/ የሚኮበልል ወታደርም ቀላል አይደለም፡፡

በእኛ በኩልም ከቆየው አካሄዳችን የተወሰነ መሻሻሎችን አምጥተን የተሻለ ትኩረት እና መደጋገፍ ለማድረግ የተጀመረ ስራ አለ፡፡ ይሁን እንጂ የኢሳያስን ውድመት/ መገርሰስ የሚያሳልጥ ዘላቂ ዋስትናችንን የሚያረጋግጥ ስራ በሁሉም መልኩ ሰርተናል ሊያሰኘን አይችልም፡፡ ኢሳያስ ከኋላችን/ ከጀርባችን እንዲወጋን በቤታችን ደጃፍ ሆኖ እያመሰን ለመኖር በፍፁም መፍቀድ የለብንም፡፡ በኤርትራ እየተከሰተ ያለውን ሁኔታ/ እውነታ ደግፈን የኢሳያስን ቡድን ለመጣል እንስራለን፡፡ እርግጥ ነው ኤርትራ ጎረቤት ሀገር ብትሆንም በኢሳያስ ቡድን ላይ የሚሰራው ስራ ግን ዲፕሎማሲያዊ ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡ ሳይመጣብን መከላከልም ሊሆን አይችልም በኤርትራ የምንሰራው ስራ ለትግራይ ምከታ በሚኖረው ቀጥተኛ ፋይዳ/ ትርጉም ፀጥታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሌሎች መስኮችን በአግባቡ ያገናዘበ መሆን ይገባዋል፡፡ በመንግስት እና ድርጅት ደረጃ የሚካሄድ መሆንም ይገባዋል፡፡ ስለዚህ ለኤርትራ ለጥቅማችን ስንል ግልጽ የስራ እቅድ ይዘን እስካሁን ስናደርገው ከቆየነው በአይነቱ የተለየ ትግል ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልገናል፡፡

## 1.2. በሀገራዊ ሁኔታዎች አዳዲስ ክስተቶች/ እውነታዎች

### 1.2.1. በጠላት ሁኔታ አዲስ ክስተት / እውነታ

ከስድስት ወራት በፊት ገዳማ በአንድ በኩል ይህ አሀዳዊ አምባገነን ቡድን በህዝቦች የተጀመረውን ትግል በሀይል እየጨፈለቀ፣ በይፋ አንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ የሚሆንበት ሁኔታ ገሀድ እንደሆነ እና በጀመረው እንቅስቃሴ በቁልቁለት መንገድ ላይ ሆኖ በተነፃፃሪ ጠንካራ የማድረግ አቅሙ እንደጨመረ አስቀምጠን ነበር፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ባህሪያቱ እና ማንነቱ ገሀድ እየሆነ፣ የህዝቦች ትግል እየተጠናከረ እንደሚሄድ እና ይኸው ሃይል ረጅም ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ሊሸነፍ እንደሚችል ካለጥርጥር ደምድመን ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ያሉት ክስተቶች/ እውነታዎች ምንድን ናቸው የሚል

በዋነኛ ነጥቦች ላይ አተኩረን ማየት ቀጥሎ የሚኖረውን ትግል ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ለማሸጋገር ጠቃሚ መነሻ ይሆነናል፡፡

ጠላት በጥቅምት እና ህዳር 2012ዓ.ም ተጀምሮ የነበረውን መጠነ ሰፊ ህዝባዊ አመጽ እና ትግል መጠነ ሰፊፊ ሀይል እና ግፍ ፈጽሞ ለጊዜውም ቢሆን እንዲቀዛቀዝ አድርጎ ነበር፡፡ የሀገሪቱ አብዛኛው አካባቢ በወታደራዊ አስተዳደር ስር እንዲገባ በማድረግ ህዝባዊ ትግሉን ለመጨፍለቅ ያልተገራ ፀረ-ህዝብ ተግባራት ወደ መፈፀም ተሸጋግሯል፡፡ የተፈጠረው ሁኔታ እንደ መልካም አጋጣሚ ወስዶ ምርጫ በተያዘለት ጊዜ እንደማይደረግ እና በኢ-ህጋዊ መንገድ ስልጣን ላይ ለመቆየት ወስኖ በመንቀሳቀስ ላይ ቆይቷል፡፡ ይህንን ውሳኔ የማይቀበል ወይም እንቅፋት ሊሆን ይችላል የሚለውን ሀይል ወደ መጨፍጨፍ እና ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲ ተግባራት ወደ መፈፀም ጠቅልሎ የገባበት ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በአንፃሩ የዚህ የአሀዳዊ እና አምባገነን ቡድን ማንነት በየእለቱ ፀሐይ እየመታው ህዝቦች ከተሞክሮዋቸው ወደ ትክክለኛ ድምዳሜ እየደረሱ፣ ይህ ሀይል በትግል ከመገርሰስ/ ከመጣል ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ እየደመደሙ የመጡበት ሁኔታ እየጨመረ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ካለፈው ሰኔ ወር ጀምሮ በዋናነት በኦሮሚያ በሌሎች አካባቢዎችም ቢሆን ሰፊ ህዝባዊ አመጽ እና ትግል ተጠናክሮ የመጣበት ሁኔታ ነው የታየው፡፡

በዚሁ የታክቲካል መድረክ በኢትዮጵያ ያለው መሰረታዊ የሀይሎች አሰላለፍ በአንድ በኩል በአዳዲስ እና ነባር የብሔራዊ ጠቅላይ ሀይሎች (አሀዳዊያን) እንዲሁም በሌላ በኩል ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች መካከል ነው፡፡ በግልጽ በእነዚህ መካከል የሚደረገው ትግል ነው ጎልቶ የመጣው፡፡ ያ ነባራዊ ሁኔታ እንዲህ አይነቱ ግልጽ አሰላለፍ እና የትግል ሂደቱ ግልጽ መልክ ይዞ የወጣበት ምዕራፍ ላይ ነው የደረስነው፡፡ ይህ ፈላጭ ቆራጭ አሀዳዊ ቡድን ከህዝቦች እያጋጠመው ባለው ተቃውሞ እና ትግል ከህዝብ እየተነጠለ ቅቡልነቱ እየወረደ አቅሞቹ እየተመናመኑ ይገኛል፡፡ ስልጣን ላይ ባለው ቡድን መካከል ልዩነታቸው እየሰፋ አብረው መስራት የማይችሉበት ሁኔታ እየሰፋ ቆይቷል፡፡ በተለይ ደግሞ ከሀጫሉ ሞት በኋላ ከዚህ ቀጥሎም ሽመልስ ያለውን ወስደን በገዢው መደብ መካከል ያ የማይቀረው ግጭት በገሀድ እየታየ ነው፡፡

በትምክህት እና ጠባብነት መካከል ተፈጥሮ የቆየው ጊዜያዊ ህብረት (አሊያንስ) ሊፈርስ እንደሚችል ቀደም ስንል ለይተን የገለጽነው ግምገማ ነው አሁን በተግባር እየታየ ያለው፡፡ ይህም ተፈጥሮአዊ ግጭት (ኢንኸሪታንስ ኮንትራዲክሽን) ጎልቶ እየታየ ነው፡፡ በፓርቲው ውስጥ ሆነ በጥገኛ ባለሀብት እና ምሁር በመካከላቸው ያለው ስንጥቃት እየሰፋ ነው፡፡ በአብዛኛው አካባቢ የብልጽግና መዋቅር የተባለ እየፈረሰ፣ እያነሰ እና ከህዝብ እየተነጠለ እየተጓዘ ነው፡፡ የቡድኑ

መዋቅር ብቻ ሳይሆን እኒያ ደጋፊዎቹ የነበሩም እየተነጠሉ እና እየወጡ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ወቅት አንድ ሆኖ መግዛት የሚችልበት ሁኔታ እየተንጠፈጠፈ ነው፡፡ የአገዛዝ እድሉን ለማስፋት ሲል በሁሉም አካባቢዎች እየወሰዳቸው የሚገኝ በአይነቱ የተለየ ግፍ እና አፈና የተጀመረውን የህዝቦች ትግልን ይበልጥ ለማቀጣጠል ከማድረግ አልፎ በመጠኑ ያነሰ እና እየተከማቸ የቆየው መጠነኛ ለወጥ ወደ ሁለንተናዊው ለውጥ ሊሸጋገር የሚያስችል እና ጠላትን ጠቅልሎ ለመጣል ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ክስተት ነው እየታየ ያለው፡፡ ከፖለቲካዊ ረገድ እየታየ ያለው ክስተት/ እውነታ መነሻ አድርገን ጠላት ዝንፈት ውስጥ እንደወደቀ እና ከዚህ ቀጥሎም ወደ ሙሉ መዛባት እና መደምሰስ መሻገር እንደሚቻል ለመደምደም አያዳግትም፡፡ ይሁን እንጂ ቀጥሎ ያሉት ሌሎች ተዛማጅ ዋነኛ ነጥቦችን እናንሳ እና ሁሉንም አይተን ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን፡፡

በኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ዙሪያ ጉዳዩን ከተመለከትን ችግሩ ወደ ከፋ ደረጃ እየደረሰ ነው፡፡ በተከታታይ ለሁለት አመት ተኩል መሪ ያጣው የዚህች ሀገር ኢኮኖሚ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ እየወረደ ነው፡፡ ጠላትም የነበረውን የልማት ፖሊሲ ከመሰረቱ ንዶ አድርግ የተባለውን አዲስ አቅርቦት የሚኖረው ኢኮኖሚ ብሎ ከከተማው ደሃ እና አርሶ አደር በተቃራኒው የቆመ እና የህዝብ ውግንና የሌለው አብዛኛውን ህዝብ ሙሉ በሙሉ ከኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚያስወጣ እና ባይተዋር የሚያደርግ ለመጽዋቾች እና ላኪዎቹ ሰፊ እድል የሚሰጥ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ እየሞከረ ነው፡፡ አሁን የምናያቸው ጥገኞች ፍላጎቱን የሚያሟላበት ገንዘብ እየሰበሰበበት የሚገኝ ገበታ ለሀገር የሚል እንቅስቃሴ፣ የውሃ ፏፏቴ ግንባታ፣ አንድነት ፓርክ ግንባታ፣ የእንጦጦ ፓርክ ልማት እና የአዲስ አበባ ከተማ ወንዞች ልማት እና ሌሎች አብለጭላጭ ፕሮጀክቶች የያዘው ሰንካላ ፖሊሲ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ከዚህም አልፎ የዚህች ሀገር ሀብት በምዕራባዊያን ኩባንያዎች ይዞታ ስር እንዲገባ እያደረገ ነው፡፡ በገሀድ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አሁን የኔትወርክ ኢኮኖሚ ሆኗል፡፡ በተወሰኑ ጥገኛ ባለስልጣናት፣ ባለሀብቶች እና የውጪ ሀገር ዜጎች ስር ገብቷል፡፡ ሌላው ቀርቶ አብዛኛው የባንኮች ብድር የአማራው ኤሊት ነው ያለው፡፡ የገቢ እና ወጪ ንግድም እነዚሁ ጥቂት ሰዎች ናቸው የተቆጣጠሩት፣ አምራች ተቋማት በአጠቃላይ ቆመው አሁን ወደ ቁማር ኢኮኖሚ ነው እየተቀየረ ያለው፡፡

የ2012ዓ.ም የበጀት አመት ሀገራዊ እድገት ዙሪያ የተለያዩ ተቋማት ትንበያቸውን እያስቀመጡ ነው፡፡ አይ.ኤም.ኤፍ ባወጣው ሪፖርት 1.9በመቶ ብቻ እንደሆነ ገልፃል፡፡ በ2013ዓ.ም የበጀት አመት ደግሞ 0 እንደሚሆን ነው የተነበየው፡፡ ሌሎች አጥንተነዋል ያሉትን ደግሞ ከ0 በታች እንደሚሆን አመላክቷል፡፡ ስለዚህ የዚህች ሀገር ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በከፋ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ ምክንያትም የዋጋ ንረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እየሄደ ነው። በተለይ ደግሞ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር ተያይዞ በሀገር ደረጃ ግሽበት በእጅጉ ተባብሷል። የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን ባለው መረጃ መሰረት ባለፉት የሰኔ እና ሐምሌ ወራት የዋጋ ንረት 21.5% እና 22.3% በቅደም ተከተል እንደደረሰ ነው። በዚህ ወቅት ወደ ውጪ የሚላክ ምርት የለም ሊባል የሚችል ነው። የኢንቨስትመንት መጠን መጨመሩ ይቅርና የነበረውም እየቆመ ነው። በተለይ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (ኤፍዲአይ) በሚያስገርም መልኩ በ2012ዓ.ም በ19.4% አሽቆልቁሏል። ከላይ በገለጽናቸው ችግሮች ምክንያት የውጪ ምንዛሬ ከባድ ችግር ውስጥ ገብቶ ይገኛል። ለወደፊቱም መፍትሄ የሌለው ችግር ሆኖ ይቀጥላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ሁኔታ አሁን ያለባት የተከማቸ እዳ 28.7 ቢሊየን ዶላር ደርሷል። በ2012ዓ.ም ብቻ የ1.7 ቢሊየን ዶላር ጭማሬ አሳይቷል። በአንፃሩ ደግሞ እዳ መክፈል በ2012ዓ.ም ከበረው በ2.4% ቀንሷል። ስለዚህ በየአመቱ የሚወሰድ ብድር እየተከመረ በአንፃሩ ደግሞ በየአመቱ የሚፈል እዳ እየቀነሰ እየሄደ ነው።

የፋይናንስ አቅርቦት ሁኔታም ምንም ሳይቆራረጥ አደረጋ ውስጥ እንደገባ ነው። በሀገር ደረጃ የባንኮች አመታዊ ቁጠባ እድገት ባለፉት 10 አመታት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በ2012 ዓ.ም ወደ 16 በመቶ ወርዷል። በተመሳሳይ የባንኮች አመታዊ እድገት ለኢኮኖሚው ባቀረቡት የፋይናንስ መጠን ላይ በ2011ዓ.ም ከነበረው 23.2% በ2012 ወደ 20.9% ወርዷል። ከዚህም አልፎ ህዝብ በመንግስት እምነት እያጣ ገንዘቡን ወደ ውጪ የሚያሸሽ፣ ቤቱ ይዞ የሚቀመጥ እየተበራከተ ነው። ጠላትም ችግሩን ለመፍታት ሲል ተጨማሪ ችግር የሚፈጥር መፍትሄ ሲወስድ ቆይቷል። ኢኮኖሚውን ከመምራት እና ማነሳሳት ይልቅ የችግሩ መፍትሄ ከኢሳያስ የተቀበለው ምክር (ሞኒተሪ ፖሊስ) ተጠቅሞ ነው ለመፍታት እየሞከረ ያለው። በቅርብ ጊዜያት እየወሰዳቸው የነበሩትን እርምጃዎች ማየት እንችላለን ከባንክ የሚወጣው የገንዘብ መጠን መገደብ፣ ከባንክ ውጪ መያዝ የሚገባው የገንዘብ መጠን መገደብ፣ አሁን ደግሞ ብር ቀይሯል። በዚህ ረገድ የሚሰራው ስራ ብዙ የመስኩ ምሁራን ጥቅሙን እና ጉዳቱን ከግምት ያላስገባ እና ምክንያት የሌለው ኢኮኖሚ እያሉ ይገኛሉ። ሁሉንም ትተን ለህትመት የወጣው 3.9ቢሊየን ብር በጣም ብዙ ነው። ይህች ሀገር በከባድ ኢኮኖሚያዊ ችግር እና በኑሮ ውድነት ውስጥ እያለች ይህንን ያህል ገንዘብ ማውጣት በፍፁም ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሊኖረው አይችልም። በመሆኑም ይህ የብር ለውጥ ከኢኮኖሚያዊ ምክንያትም በላይ ፖለቲካዊ ምክንያት እንደሆነ ገሀድ ነው።

አሁን ስናየው በቆየነው ምክንያት ዛሬ በኢትዮጵያ ስለ እድገት/ ብልጽግና መናገር ቀርቶ መብላት እና አለመብላት ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ወደሚሆንበት ደረጃ እየተሸጋገርን ነው፡፡ አሁን ያለው ፖለቲካዊ ቀውስ ይህንን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በዋናነት እየጎዳው በዚህ ላይ ወደ መከራ የሚያመራ አማራጭ በያዘ ጠላት መኖር ረጅም ባልሆነ ጊዜ ውስጥ መቅሰፍት ሊፈጠር እንደሚችል እየታየ ነው፡፡ የሚላስ የሚቀመስ ያጣ ህዝብ ቤቱ ተዘግቶበት ሊሞት አይችልም፡፡ በዚህም በሌላ ፖለቲካዊ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወደ ትግል እንዲገባ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር በኢኮኖሚ ረገድም ተሸክሞት ረጅም ጉዞ መራመድ/ መቀጠል አይችልም፡፡ ይዞት መደርመስ የሚችልበት እድል ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድም ጠላት ከመሰረቱ እንዲዛባ አድርጎታል፡፡

ሌላው ጠቃሚ ነጥብ በዲፕሎማሲ ረገድ ጠላት ከምዕራብ ሀገራትም ሆነ ከአካባቢያዊ መንግስታት እየተነጠለ ለብቻው እየቀረ የሚገኝ ሀይል ነው፡፡ በመጀመሪያ ወቅት እንደነበረው አይነት ድጋፍ አሁን የለም፡፡ ይህንን ሲጀምር የተገባለት ስለትም ቢሆን ማግኘት አልቻለም፡፡ የተመኙትን ሪፎርም የኢትዮጵያ ህዝብ ስላልተቀበለው አደጋ ውስጥ ገብቷል፣ አብይ ሊቀጥልበት አይችልም የሚል ድምዳሜ እየያዙ ነው፡፡ አደናገረን፣ ቃሉን የማያከብር ከሀዲ መንግስት እያሉት ነው፡፡ በዋናነት ደግሞ በጎረቤት ሀገሮች ከሶማሊያ ማዕከላዊ መንግስት እና የኢሳያስ ቡድን በስተቀር በሌሎቹ ዘንድ የተናቀ ነው፡፡ በውጭ እየተካሄደ ባለው ተከታታይ ትግል በመንግስታት ላይ እየፈጠረው የሚገኝ ተጽእኖም ቀላል አይደለም፡፡ የተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በይፋ ገዳይ መንግስት እያሉት ነው፡፡ በምዕራቡ አለም እኛ ላይ ባላቸው ጥርጣሬ ምክንያት የሚኖር ተጽእኖ በቀላሉ የሚቃለል ባይሆንም ላለፉት ሁለት አመታት ባደረግነው ትግል እና በቅርብ ጊዜ ያካሄደውነው ስኬታማ ምርጫን ተከትሎ በዚህ አካባቢ በሚኖር ለውጥ እንደ አንድ አቅም አድርገው ሊያዩን እና ተፈላጊነታችን ከፍ እንዲል እድል ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንፃር የእርሱ ቅቡልነት መውረድ እኛም ሆንን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የምናደርገው ትግል ድጋፍ እያገኘ በቀጣይ ጊዜያት በጠላት ላይ ለሚደረገው ትግል እንቅፋት የሚሆኑ ሁኔታዎች እንዳይኖሩ ወይም እንዲቀንስ የሚያደርግ ውጫዊ ሁኔታ/ እውነታ ነው ብልጭ ድርግም እያለ ያለው፡፡

በፀጥታ፣ ደህንነት እና ሰላም ዙሪያ ያሉ ክስተቶች/ እውነታዎች ሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት በዚህች ሀገር አብዛኛው አካባቢ ሰላም የለም፡፡ ግጭት፣ ግፍ፣ የጅምላ ግድያ እና እስር ከነበረበት በእጅጉ ተባብሷል፡፡ ሰላማዊ ጥያቄ የጠየቁም ህዝቦች በሀይል መጨፍለቅ፣ ህዝቦችን በጅምላ መጨፍጨፍ ሁሉም የፀጥታ ሀይል ባገኘው አጋጣሚ የመሰለውን እርምጃ

እንዲወስድ እየተደረገ ነው። በኦሮሚያ፣ ደቡብ (ወላይታ እና ሲዳማ)፣ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ በየቀኑ የሚያልፍ ህይወት ስጉድ ነው። ይህ ፀረ ህዝብ ሀይል በዋናነት እየተጠቀመበት ያለው የደህንነት መዋቅር ነው። በየክልሉ ተሰባስቦ የሚገኘው ልዩ ሀይልም ህዝብን ለማረድ እየመጣ ነው። የመከላከያ ሀይልም አድርግ የተባለው እያደረገ ነው። በተለይ በኦሮሚያ ከመጠን በላይ እንዲያብጥ ያደረገው ልዩ ሀይል ልክ እንደ ባዕዳን ሀይሎች ንብረት ይወራል፣ ሴቶችን ይደፍራል፣ አመጽ ለማካሄድ ታስባለህ እየተባለ ወጣቶች በህዝቦች ፊት በጥይት እየተደበደቡ ይውላሉ። ከዚህ በላይ ክህደት፣ ጥቅመኝነት/ ተመጽዋችነት፣ ጸረ-ህዝብነት ምን ሊኖር ይችላል። በእንደዚህ አይነት ተግባራት ምክንያት ህዝብ በፀጥታ መዋቅሩ ላይ እምነት እያጣ እየተገለለ እየሄደ ነው። በዚህም ምክንያት በሀገር መከላከያ የመሰላቸት እና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እያደገ ነው።

ይሁን እንጂ ጠላት በዚህ ረገድ ያሉት አቅሞ ገና አልተዳከሙም። ሁሉንም ትቶ ሀይልን ተጠቅሞ ነው ሁኔታዎቹን ለመቀየር እየጣረ የሚገኘው። እርግጥ ነው ጠላት ህልውናውን ጠብቆ እንዲቆይ እያደረገው ያለው የፀጥታ እና ደህንነት መዋቅር ነው። ቀጣይ/ ዘላቂ ህልውናውን ለማደላደል ሲል በፀጥታ መዋቅር ዙሪያ ትልቁን ዝግጅት እያደረገ ነው። የቆየው የሀገር መከላከያ ሀይል በተለይ በትግራይ ያለውን እና የተላመደውን ሀይል አድርግ የተባለውን ሊያደርግ አይችልም ብሎ በጥርጣሬ እየተመለከተ በአዲስ ሀይል ለመተካት እየሞከረ ነው። በሀገር ደረጃም የነበረውን ሀይል ለመቀየር እጅግ በጣም ብዙ ቁጥር ያለው አዲስ ሀይል ወደ ማሰልጠኛ ማስገባት ጀምሯል። ቀደም ሲል ማደራጀት የጀመረውን የሪፐብሊካን ሀይልንም እያጠናከረው ነው። በኦሮሚያ ያለው ልዩ ሀይልም በሁሉም መልኩ እንዲታጠቅ እና እንዲጠናከር እያደረገ ነው። በአማራም ተመሳሳይ ስራዎችን እየሰሩ ነው። የኢሳያስ ሀይልም ቀላል የማይባል ሀይል ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ አድርጓል። በስልጠና፣ በስለላ፣ በሰው ሀይል ስምሪት እየተደረገ ያለው መደጋገፍ ጠላት ሌላው አቅሙ ወይም ችሎታው ከፍ እንዲል የሚያደርግ ነው። ከዚህ ተነስተን ጠላት በወታደራዊ ድጋፍ በኩል ገና አልተዛባም/ አልተዳከመም። እዚህ ላይ ነው የተንጠላጠለው። እርግጥ በሌሎቹ ዘንድ ያለው ለውጥ በዚህ ወታደራዊ ክንፍ በኩልም የሚወሰን የሆነው የሀይል ሚዛኑ መቀየር ካለበት ግን በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ሂደት የሚያጋጥሙ መዛባት በወታደራዊ ክንፍ በኩል ተመሳሳይ ውጤት/ ክስተት መምጣት ከቻለ ነው። ስለዚህ በዚህ ረገድ ወሳኝ ስራ ይጠይቀናል። ይህንን ለማድረግ ከሁሉም በፊት ሊሰራበት የሚገባው የመከላከያ ሀይል ነው። ሁሉንም አይነት አማራጭ ተጠቅመን የዚሁ ሀይል መሳሪያ ሆኖ እንዳይቀጥል ማድረግ አለብን።

### 1.2.2. በብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ተጨማሪ ክስተቶች/ እውነታዎች

በዚህ ወቅት የማንነት ጥያቄ፣ የዴሞክራሲ፣ ሰላም እና የልማት ጥያቄ ህዝቦች በኢትዮጵያ እየታገሉባቸው ያሉ ቁልፍ ተቀጣጣይ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ ሌላም አዳዲስ ቅሬታዎች ይዘው እየወጡ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ብሔር፣ ብሔረሰቦች ይህ ሀይል ነፍጠኛ እና አሀዳዊ ነው ብለው ደምድመዋል፡፡ የማይታመን፣ አታላይ፣ አጭበርባሪ እና ፀረ-ህዝብ ነው የሚል በሁሉም ዘንድ ሊባል በሚችል ሁኔታ ተመሳሳይ ድምዳሜ ይዘዋል፡፡ የተፈለገው ነገር ቢባልም ይህንን እምነት ለመሸርሸር ወደኋላ ሊመለስ አይችልም፡፡ ከመደምደም አልፎም በየአካባቢያቸው ገደብ አልባ ወደ ሆነው አመጽ ተሸጋግረዋል፡፡ ህዝቦች ከተሞክሯቸው እየተማሩ ትክክለኛ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ለህዝቦች መብት በሚደረገው ትግል እና በአፈና ሀይል መካከል የሚደረገው ትግል ነው ጎልቶ እየታየ ያለው፡፡ የዚህ ትግል መልክም ሰላማዊ ሊሆን እንደማይችል እና የሰላም መንገድ እየተዘጋ መሆኑን አይተው እያደረጉት ያለ ዝግጁነትን ነው፡፡ በዚህ ረገድ ለትግል ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር እና ትግሉ የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ የሆነ ህዝብ ተጠናክሮ ወጥቷል፡፡

ካለፈው ክረምት ጀምሮ የህዝቦች ትግል በየቀኑ አዳዲስ ክስተቶችን/ እውነታዎችን እያሳየ እና እየተጠናከረ ይገኛል፡፡ በአብዛኞቹ አካባቢዎች ማለትም ከተሞችን መሰረት አድርገው ሲካሄዱ የቆዩ አመጾች የገጠር ማህበረሰብ በዋናነት አርሶ አደሩ እየተቀላቀለ የመላው ህዝብ መልክ ይዞ እየሄደ ነው፡፡ በአይነትም ሆነ በመጠን ከነበረው በእጅጉ ጨምሮ በኦሮሚያ ሲካሄድ የቆየው እና ያለው ትግል የህዝቡ ነው፡፡ የቄሮ ንቅናቄ ህዝባዊ ንቅናቄ ነው፡፡ ወደኋላ ሊመለስም አይችልም፡፡ እንደ ህዝብ ከልጆቹ ጋር ሆኖ ነው እየታገለ ያለው፡፡ አብዛኛው ደግሞ ውስጥ ሆኖ በየቀኑ መስዋትነት እየከፈለ ፀረ-ስርዓቱ እየታገለ ነው፡፡ በውጪ ያለውም ቢሆን ከማንኛውም ጊዜ በላይ ተደራጅቶ ዕየታገለ ነው፡፡ በቤንሻንጉልም ጫካ ገብተው የአቅማቸውን ትጥቅ ይዘው፣ ባህላዊ መሳሪያ ተጠቅመው ከፀጥታ ሀይሎች ጋር ወደ ተከታታይ ትግል ገብተዋል፡፡ በጋምቤላም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በአመጽ እየተደረገ ካለው ንቅናቄ/ እንቅስቃሴ በተጨማሪ በኦሮሚያ ቄሮ እና ኦነግ ሸኔ፣ በአማራ ከሚሴ እና ቅማንት፣ በቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ አፋር እጉጉመ እና ሌሎችን በትጥቅ በመደገፍ ለሚደረገው ትግል የተሻለ እድል የሚሰጥ ሁኔታ/ አውነታ እየተከሰተ ነው፡፡

በደቡብ በተለይ በወላይታ እስካሁን ድረስ የዘለቀው ህዝባዊ አመጽ እና ትግል ለወፊቱም ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚችል ነው፡፡ በአፋርም ጠላት የአካባቢውን ሰላም ለማደፍረስ ከእኛ ጋር ወደ ግጭት እንድንገባ ብዙ ሞክሮ አልሆነለትም፡፡ በአማራ የመንግስት መዋቅር በብዙዎቹ አካባቢ ፈርሷል

ሊባል የሚችል ነው። ስርዓት የለም፣ ሰላም፣ ልማት የሚባል ተረስቷል። ከዚህም አልፎ በሌሎች አካባቢዎችም እየደረሰ ያለው ችግር/ ተግዳሮት ቀላል አይደለም። በዚህ ምክንያት የአመራ ህዝብ ተስፋ እየቆረጠ እና እየተማረረ ይገኛል። በዋናነት ግን በቅማንት፣ አገው፣ በወሰን/ ድንበር አካባቢ የሚገኝ ህዝብ እንደሌሎቹ ህዝቦች ተመሳሳይ ትግል እያደረገ ነው። የትግራይ ህዝብ እና መሪ ድርጅቱ ህ.ወ.ሓ.ት እስካሁን ድረስ ያደረጉት አቋማዊ / መርሆዋዊ ትግል እና ጽናት ለህዝቦች ትግል እና መደጋገፍም ቁልፍ ሚና እየተጫወተ ቆይቷል። በዚህ ምክንያት ከእኛ ጋር ሆኖ መታገል እና በጋራ እንድንሰለፍ የሚፈልግ ብዙ ነው። ለወደፊቱ እንዲኖር የሚፈልጉት መፍትሔም የተለያዩ የመጡ/ የታዩ አመለካከቶች እና እምነቶች ቢኖሩም እንኳ የአብይን ቡድን ለመገርሰስ በሚደረገው ትግል ላይ ግን ተመሳሳይ እምነት ይዘዋል።

ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ንቅናቄው/ እንቅስቃሴዎች የተደራጀ እና የተጠናከረ አመራር የለውም። እንደ አቅሙ የነበረው ሀይልም ላይ ጉድት ደርሶበታል። ጠላት ንቅናቄውን የመሩትን እና ሊመሩ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን እየበተናቸው እና እያሰራቸው ነው። ታች ድረስ ወርደው ህዝባዊ ንቅናቄውን መምራት እና ማስተባበርም አልቻሉም። በአካሄዳቸውም ለጥቃት የተጋለጡ ሆነው ነው የቆዩት። ይህ ትግል በተለይ በኦሮሚያ የተጀመረው አመጽ በአይነትም ሆነ በመጠን እንዲቀየር የሚያደርግ የአመራር ክፍተት ገዝፎ እየታየ ነው። በሌሎችም ተመሳሳይ ጉድለት ነው ያለው። በሀገር ደረጃ የህዝቦቹ ትግል አልተሳሰረም/ አልተቆራኘም። ባህላዊ ሁኔታዎች አለማሟላት ምክንያት ጠላት እስካሁን ድረስ እንዲቆይ እድል ሰጥቶታል። እዚህ ላይ ያለው ችግር ባለመፈታቱ መሰረታዊ ለውጥ (ሜጀር ሽፍት) መምጣት አልቻለም። ወደ ሙሉ ጥቃት የምንሸጋገርበት ሁኔታ አሁንም ጉድለት አለበት። ይህ ነው እያዘገየው የሚገኘው እንጂ ነባራዊ ሁኔታው ወደ ተፈለገው ደረጃ ደርሷል። ስለዚህ በዚህ ረገድ ያለውን ችግር ለመፍታት የጀመርነውን እንቅስቃሴ/ ንቅናቄ በማጠናከር ላይ እንድናተኩር እና ይህንን በማሟላት/ መሙላት የሚኖረን ሚናም በአግባቡ አውቀን እንሰራበታለን።

### 1.2.3. በምርጫ ጉዳይ እና ሀገራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ክስተት/ እውነታዎች

ጠላት ከ5 ወራት በፊት የኮሮና ወረርሽኝ ክስተትን ተገን አድርጎ ምርጫ ማድረግ እንደማይቻል እና ላልተወሰነ ወቅት ስልጣን ላይ እንደሚቆይ ወስኖ ቆይቷል። የዚህም ምክንያት ኮቪድ 19 እንዳልነበር የታወቀ ነው። እየተፈጠረ በነበረው የህዝብ አመጽ እና ትግል ምርጫውን አካሂዶ በሚያስተማምን ደረጃ ስልጣኑን ይዞ ማርፈድ የማይችል መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ህገ መንግስቱን ጥሶ እና ረግጦ ስልጣኑን ማራዘም ችሏል። ታዲያ ለምንድነው ከ5

ወራት በኂላ በዘንድሮ አመት ምርጫ አደርጋለው ያለው፡፡ የአብይ ቡድን ምርጫውን አደርጋለሁ የሚለው ከገባበት ውጥረት ለመውጣት ተገዶ የገባበት ነው፡፡ ይህ ግፊትም ከውስጥም ሆነ ከውጪ የመጣ ነው፡፡ አንዱ ቁልፍ ምክንያት ከውስጥ የሚመጣው ግፊት ነው፡፡ እስካሁን ድረስ ያሉ አመፆች እና ለወደፊቱም ሊኖር የሚችለውን ከባድ አመጽ እና ትግል አይቶ እንቅስቃሴዎችን/ ንቅናቄውን ለማቀዛቀዝ፣ በትግራይ ባካሄድነው ምርጫ በኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ የፈጠረው መነቃቃት/ ተነሳሽነት እና በአለም ማህበረሰብ ዘንድ የፈጠረው ተጽእኖ ከመስከረም ወር በኂላ ህጋዊ መንግስት አይደለህም የሚል ከህዝብ ሊመጣ የሚችል ተቃርኖ ፈርቶ እና ህልውናውን ለማስቀጠል ሲል የገባበት ነው፡፡ በፍፁም ምርጫውን ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ስላለ ወይም መደረግ አለበት ብሎ ስላመነ አይደለም፡፡ የተጀመረው ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ለመቸለስ እና አጀንዳን ለማስቀየር የፈጠረው አዲስ ድራማ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራር/ መዋቅሮች ከላይ እስከ ታች በማሰር እንዲበታተኑ እያደረገ ስለሚገኝ በምርጫ (እስከዛው ድረስ ከቆየ) በህዝብ ድጋፍ ሳይሆን ሀይልን ተጠቅሞ፣ ገንዘብ በትኖ፣ አስፈራርቶ፣ ኮሮጆ ገልብጦ እና አጭበርብሮ ስልጣን ላይ እቆያለሁ የሚልም ይኖረዋል፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን በመስከረም እና ጥቅምት የሚኖረውን ወጥመድ ለማምለጥ ብሎም ያደረገው ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ግን እርሱ የሚያዛቸው እና የሚዘውራቸው ድርጅቶችን ይዞም ለመስራት እየሞከረ ነው፡፡ በአማራ የብልጽግና መዋቅር ጠቅልሎ እየተኮማተረ ስለሆነ አሁን ላይ አብንን ይዞ ነው ለመስራት እየሞከረ ያለው፡፡ በኦሮሚያም ከፊሉን በገንዘብ ፍላጎታቸውን እየደፈነ እና እያታለለ ከጎኑ እንዲሰለፉ እያደረገ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ድራማ እየሰራ የሚኖረውንም ትግል የሚያዳክም ተግባራት እየፈፀመ እንዲቆይ እና ፋታ እንዲያገኝ እያደረገ ያለ ነው፡፡ በመሰረቱ ግን በህዝብ ትግል ተገፍቶ ቅርቃር ውስጥ ከገባ በኂላ የደረሰበት ውሳኔ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት የውጪ ሀይሎች አሁን ባለው ሁከት እና አመጽ ሰግተው ምርጫ ሳይደረግ ከሚመጣው ቀውስ (ክራይስስ) ይልቅ ምርጫ ተደርጎ የሚመጣው ይሻላል ከሚል እና ከትግራይ ጋር ወደ ጦርነት መግባት ሊያስከትል የሚችል መዘዝ ከፊል አማካሪዎቹ እና ዘዋሪዎቹ በቀላሉ ስለሚገነዘቡ የፈጠሩበት ተጽዕኖም ነው፡፡ በዚህ ምክንያት መስከረም 25 ሳይደርስ ምርጫውን አድርጋለሁ ብሎ ለማወጅ ተገዷል፡፡ ይህ ሁኔታ ለወደፊቱ በሚኖረው ፖለቲካዊ ክስተት/ እውነታ/ ሁኔታ ምን ሊፈጥር ይችላል የሚል መታየት ያለበት ነው፡፡ አሁን እየተፈጠረ ባለው ሁኔታ በብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ትግል ላይ ሊፈጥረው የሚችል መቀዛቀዝ ቀላል አይደለም፡፡

እንዲህ ያለበትን ምክንያት ለምን እንደሆነ ግልጽነት መፍጠር ካልተቻለን ሊከሰት የሚችለው መፋዘዝ ቀላል አይሆንም። በዚህ ላይ ያ የህዝቦች ትግል መጠነ ሰፊ አመራር እጦት ችግር አለበት ብለናልና። እየደረሰባቸው ያለው ጥቃትም ከባድ ነው። በዚህ ምክንያት መረባረብ ሊመጣ ይችላል። ምርጫ የሚደረግ ከሆነ በዚሁ ምርጫ ላይ አንዱን እናደርጋለን የሚል መዘናጋትም ሊፈጥር ይችላል። ስለዚህም ከፊት ያሉትን ተግዳሮቶች በአግባቡ ተገንዝቦ ጠላት ከምርጫው በፊት የሚሰናበትበትን እድል ሊያሰናክል ይችላል። ይህም በብዙ መልኩ አደገኛ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርግ ነው። በሀገር ደረጃ ሊፈጠር የሚችለው ትግሉን ወደኋላ መመለስ ብቻ ሳይሆን ችግሩ ተጠራቅሞ ወደ ትግራይ እንዲመጣ የሚያደርግም ነው።

ከውጪም ቢሆን ምርጫ አደርጋለሁ ካለ ታዲያ ምን እያላችሁ ነው የሚል ሊመጣ ይችላል። ይህንን መሰረት አድርጎ ወደ ድርድር እንድንገባ ተነሳሽነትን ሊጀምሩ እና አጠናክረው ጥረት ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህንን ሲያደርጉ በሁሉም የአፍሪካ ሀገሮች እንዳደረጉት አብዛኛዎቹን ፖለቲካዊ ሀይሎች በገንዘብ ከፊሉንም ስልጣን በማጋራት ለመፍታት ሊያስቡ ይችላሉ። አብዛኞቹ የቀሩት ድርጅቶች ደግሞ በዚህ ሊታለሉ እና ሊሸነገሉ ይችላሉ። ስለዚህ በዚህ ረገድ ሊመጣ የሚችለው ፈተናም ቀላል አይደለም። ይህ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የደረሰው ትግል አዙሪት ውስጥ ገብተን ጊዜ እንድናጠፋ የሚያደርግ ነው።

እኛ ምርጫ አድርገን ህጋዊ መንግስት አቋቁመናል። እሱ ደግሞ ህጋዊ ምርጫ አይደለም በማለት አውጇል። በሌላ መልኩ ደግሞ ከመስከረም በኋላ ህጋዊ አይደለህም ልቀቅ እያልነው ነው። አሁን ይፋዊ አቋም ይዘን በፌደራል የነበረውን በሹመት የተመደበውን የሰው ሀይላችን እንዲመጣ አድርገናል። ከዚህ አልፎም የችግሩ መፍትሄ መሆን ያለበትን ነጥብ ለይተን ግልጽ የሆነ የሰላም እቅድ ይዘን እየታገልን ነው። ጠላት ደግሞ ይህንን አይቀበልም። ስለዚህም አሁን ወደ ሙሉ ግጥሚያ (ኮንፍሮንቴሽን) ውስጥ ገብተናል። እኛን ለማሳነስ፣ ቅርቃር ውስጥ ለመክተት የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። እየሞካከረው እንደቆየው ውስጣችንን በተባበረ አመጽ/ ሁከት ሊያምስን ይሞክራል። በባንዳዎቹ እና ተላላኪዎቹ በኩል ከኢሳያስ ቡድን ጋር በመተባበር ብዙ ጥረት ያደርጋል። እኒያ ትግራይ ውስጥ የሚገኙት የተወሰኑ ተፎካካሪ ድርጅቶችም አደርገዋለሁ ካለው ምርጫ ጋር ተያይዞ ምን ሊሉ ይችላሉ የሚለውን የምናየው ይሆናል። ከፊሉ በምርጫው ተሳተፉ እናግዛችኋለን የሚላቸው ወገን ካገኙ አሁን እያሳዩት ካለው እምቡር - እምቡር ማለት ጋር ተያይዞ ቁልቁል ሊወርዱ ይችላሉ።

በዋናት ደግሞ በአንድ በኩል ህልውናውን ለማረጋገጥ ሲል ራሱ በቀጥታ ብዙ አማራጮችን ተጠቅሞ እኛን ቅርቃር ውስጥ ለማስገባት እና ለመምታት ጥረት ያደርጋል፡፡ አስቀድሞ በለስላሳ መሳሪያዎች (ሶፍር ፓወር) ሊጀምር ይችላል፡፡ ልክ አሁኑ ህጋዊ ያልሆነው የፌደሬሽን ምክር ቤት ወስኗል እንደተባለው የፌደራል መንግስት ከትግራይ መንግስት ጋር ግንኙነት መፍጠር የለበትም፤ የህዝብ መሰረታዊ ልማት እና መሰረታዊ አገልግሎቶችን ከመመለስ ውጪ ሌላ ግንኙነት አይኖረውም፣ ሲቀጥልም በጀት አንሰጥም ብሏል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው የሚለውን ዝርዝሩን ተገንዝበን ህዝብም እንዲያውቀው እናደርጋለን፡፡ ቀጥሎም በመሰረተ ልማት፣ የምንገባበትን እና የምንወጣበትን አካባቢዎች ለመዝጋት እና በሌሎች መስኮችም እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ ይህንን ጠቅለል ያለ ውሳኔ እንዳሻው/ እንደተመቸው ሊተገብረው ይችላል፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ወታደራዊ መስክ (ሀርድ ፓወር) ሊሻገር ይችላል፡፡ ይቻላል ብሎ ካሰበ ደግሞ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ይህንን ሁሉ ላያደርግ ይችላል፡፡ እኛ የሚኖረን ፈታኝ እርምጃ እና አስቀድመን ሁኔታዎች እንዲለወጡ ካደረገግን ሁሉንም ሳያደርግ እንዲቀር፣ ካለን ደግሞ ከቁጥጥራችን የማይወጣ እንዲሆን ማድረግ እንችላለን፡፡ ለማንኛውም ከምርጫ ጋር ተያይዞ እንዲህ አይነት ሁኔታዎች/ ክስተቶች ይኖሩ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ጠላትን ለመጣል በሚደረገው ትግል ምርጫን ምክንያት አድርጎ ሊፈጥረው የሚችለው መደናገር ዋነኛ ትኩረት ከምንሰጣቸው አንዱ አቅጣጫ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ሊፈጠር የሚችለውን መቀዛቀዝ ለመከላከልም ሆነ ጠላት አሁን ከገባበት ወጥመድ ለመውጣት እድል የሚነሳ እንቅስቃሴ/ ንቅናቄ ማድረግ የሁሉም ስራዎቻችን ማዕከል/ አስኳል አድርገን ልንረባረብበት ይገባል፡፡ የትግሉ መልክም መለወጥ አለበት፡፡

### 1.2.4. በሀገራዊ ሁኔታ/ እውነታ ጠቃሚ ፖለቲካዊ ድምዳሜ

ከላይ አለማዊ ሁኔታዎችን ከትግላችን፣ የጠላት ሁኔታ እና ከኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል አንፃር ምርጫ እና የሀገራችን ቀጣይ ፖለቲካዊ ክስተት/ ሁኔታ የሚመለከቱ ጉዳዮችን አይተናል፡፡ እስካሁን ድረስ እያየነው የቆየውን ተጨባጭ እና ነባራዊ እውነታ መሰረት አድርገን አንዱ ቁልፍ መደምደሚያ ትግሉ ወደ ወሳኝ ምዕራፍ እየተሸጋገሩ መሆኑን ነው፡፡ ጠላትን የምናሰናብትበት አመት፣ ወር፣ ቀን እና ሰዓት አሁን ነው፡፡ ጎን ለጎን መኖርም አይቻልም፡፡ እንደ ሀገርም ከባድ አደጋ ውስጥ ነን፡፡ ይህ አምባገነን እያለም ሆነ ከዚያ በኋላ ይህች ሀገር ልትፈርስ ትችላለች፡፡ የቆየው ሰላማዊ የትግል አግባብም እድሉ እየተዘጋ ነው፡፡ ወደ ሌላ አማራጭ የምንገባበት ሁኔታ/ እውነታ ላይ ነው የደረስነው፡፡ አሁን ማክረሩ እየተጠናከረ መምጣቱ መጥፎ አይደለም ለፈጣን ለውጥ እና ወሳኝ ትግል መሆን አለበት እንጂ፡፡

ጠላት በብዙ መልኩ ተዛብቷል፡፡ የተዛባውም ጠላት እድል ሳያገኝ ሙሉ በሙሉ መሰናበት/ መገርሰስ፣ መደምሰስ አለበት፡፡ አሁን ባለው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ፣ የኦሮሞ አመጽ የተሻለ አመራር አግኝቶ እየተጠናከረ እና እያደገ/ እየጨመረ ሲሄድ ሌሎች ብሔር፣ ብሔረሰቦች ከዚህ በኋላ ህጋዊ መንግስት አይደለህም ብለው ወደ ትግል እና አመጽ ካመሩ ጠላት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊወድቅ ይችላል፡፡ እኛ የጀመርነው ትግል በሁሉም መልኩ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ገጽታዎቹን አቀናጅተን በሰፊው ከተሰማራንበት/ ከዘመትንበት ሀገር ደረጃ ለሚኖር ውጤት ጠቃሚ ሚና መጫወታችን አይቀሬ ነው፡፡ አሁን ባለንበት ደረጃ ለረጅም ጊዜ መቆየት የለብንም ከዚህ በኋላ ////////////

# ገጽ 20 ተዘሏል

የምከታ እንቅስቃሴ ብዙ ገጽታዎች ያሉት እና ሰፊ እና ጥልቅ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የምናደርገው ፖለቲካዊ፣ ፀጥታዊ፣ ልማታዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ድርጅታዊ እና መንግስታዊ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ይህንን አመራራችን፣ አባላችን እና ህዝባችን እንዲገነዘብ ማድረግ ማለት ነው፡፡ የምከታ ፖለቲካዊ ስራዎቻችን ከምንም በላይ ማየት ያለበት ህዝባችንን ነው፡፡ በሁሉም መልኩ እንዲያውቅ ማንኛውም ችግር ከመጣም ይህንኑ ተቋቁሞ በምከታው እንዲዘልቅ፣ የህዝብ እንቅስቃሴ/ ንቅናቄ የምከታችን ወሳኝ ሀይል መሆኑን ተገንዝበን እና መጠነ ሰፊ ስራ ሰርተናል፡፡ ደጀንን ማጠናከር ማለት የህዝብ ፖለቲካዊ ስራ፣ ተጋላጭነታችንን መቀነስ ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ ለሁሉም አቀፍ ወሳኝ ግጥሚያ እንዲዘጋጅ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በትግራይ የሰራነው ፖለቲካዊ ስራ ሰፊ ነው፡፡ መላው ህዝባችንን የማንቃት፣ ማደራጀት፣ ማሰማራትን መሰረት ያደረገ ንቅናቄ አቀጣጥለን ያልተቆራረጠ እና ተከታታይ ፖለቲካዊ ስራዎችን ሰርተናል፡፡ የልማት እና የምከታ ሰራዊት ግንባታ በሰፊው አነቃንቀን ተቀፍድዶ የነበረውን የመፈፀም አቅማችንን በመፍታት ትልቅ አቅም ፈጥረን ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብተናል፡፡ በዚህ ረገድ ለውጥ ማምጣት መጀመራችን ለሌሎች ዘላቂ/ ቀጣይ ስራዎች ትልቅ መነሻ እና አቅም ሆኖ ሊያገለግለን የሚችል ተሞክሮ ያገኘንበት ነው፡፡

እንደገለጽነው የትግል ልዩ ምዕራፍ ክስተቶችን/ እውነታዎችን መሰረት አድርጎ የተካሄደው መጠነ ሰፊ ኦረንቴሽን ስራ በዚህ መድረክ ባህሪያት እና ማንነት ላይ ግልጽነት ፈጥረናል፡፡ በአመራር፣ አባላችን እና ህዝባችን የተቀራረበ አመለካከት እንዲመጣም ጥረት ተደርጓል፡፡ የማንቃት እንቅስቃሴያችን/ ንቅናቄያችን የፈጠረው ምቹ ሁኔታን ተከትሎ ህዝባችን እንዲደራጅ ከማድረግ አኳያም መጠነ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የድርጅታችን መዋቅሮች/ አደረጃጀቶችም ተልዕኳቸውን መሰረት ያደረ አደረጃጀት እና ስምሪት ይዘው ወደ ተጨባጭ ተግባር እንዲገቡ፣ የተሻለ ጥንካሬ ይዘው እንዲወጡ ሰፊ መረባረብ ተደርጓል፡፡ እንደ ውጤቱም ባለፉት 5 ወራት በትግራይ ደረጃ እስከ 2.3ሚሊየን ገደማ ህዝብ መደራጀት ችሏል፡፡ ይህም በማንኛውም መስፈርት ታሪካዊ ስራ ነው፡፡ ባለፉት 2 እና 3 አመታት ፈጽመነው የማናውቀው ትልቅ ውጤት ነው፡፡ ከማደራጀት በኋላም ቢሆን ወደ ተጨባጭ የምከታ ተግባር እንዲሰማራ/ እንዲዘምት፣ እንቅስቃሴውን እያጠናከረ እና እያደላደለ እንዲሄድ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ምርጫ የአንድ መልክ/ገጽታ አንድ ተግባር ነው፡፡ በምርጫ ዙሪያ እንደ አሁኑ በአደረጃጀት በኩል ሞቢላይዝ አድርገን አናውቅም፡፡ በቁጠባ ምከታችን ረገድ የሚጠይቀውን ዝግጁነት ለማድረግ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችም ነበሩ፡፡ በመልካም አስተዳደርም ችግሩን ከማወቅ አንስቶ ለአመታት የቆየው የወረዳ ጥያቄ በህዝባችን ተሳትፎ እና ጽናት ላይ ተመስርተን ያደረግነው መፍትሄ አንድ ለውጥ ነው፡፡

በፖለቲካዊ ስራዎቻችን ሌላው ጠቃሚ ተግባር ሚዲያን የሚመለከት ነው፡፡ ሚዲያ ለትግራይም ይሁን በሀገር ደረጃ ለሚኖር ፖለቲካዊ ስራ የመፍካከሪያ/ የመዋጊያ ቁልፍ አቅማችን በመሆኑን ደጋግመን የተናገርነው ነው፡፡ በሚዲያ ዙሪያ የነበሩ ችግሮችን በዝርዝር እንዲገመገሙ የተቀመጠ አቅጣጫም ነበር፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ በየደረጃው የሚገኘውን ሚዲያ የሚመራ ኮሚቴም ሆነ በሚዲያ ተቋማት የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ተከታታይ እና ሰፋፊ ግምገማዎች ሲደረጉ ቆይቷል፡፡ ለወደፊቱም ስራውን በተሻለ መልኩ ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀት ተፈጥሮ ወደ እንቅስቃሴ እንዲገባ ጥረት ተደርጓል፡፡ የሚዲያ ኮሚቴ፣ በየቀኑ የሚመራ እና የሚያስተባብር የሚዲያ ቋሚ ኮሚቴ በይፋ እንዲቋቋም እና በአስቸኳይ ወደ ተግባር እንዲገባም ተደርጓል፡፡ ከግምገማ በኋላም ይሁን አደረጃጀቶች እንደተስተካከሉ ስራውን ጠበቅ በማድረግ መምራት ስለተጀመረ በሀገራዊ ትግል ትልቅ ሚና እየተጫወተ ቆይቷል፡፡ የትግራይ ሚዲያዎች የህዝብ ድምጽ መሆን ችለዋል፡፡ አጀንዳ ቀርፀን ወደ ማጥቃት ስለተሸጋገርን ጠላትን ወደ መከላከል እንዲገባ እና የሀሳብ የበላይነት ለመፍጠር አስችሎናል፡፡ በዋናነት ደግሞ ማንነቱን እና ባህሪውን እንዲጋለጥ በማድረግ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡ የትግራይ ምርጫ በዋናነት እንዲጎላ በማድረግም ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡

በሀገራዊ ፖለቲካዊ ስራዎቻችን ህዝቦች የአሀዳዊው እና አምባገነን ቡድን ማንነት እና ባህሪያት እንዲገነዘቡ፣ የብሔር ብሔረሰቦችን ሉአላዊ ስልጣን ረግጦ ኢ-ዲሞክራሲያዊ ስልጣን ይዞ እየዘለቀ መሆኑን፣ የመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠላት መሆኑን፣ ኢ-ህጋዊ በሆነ መንገድ ከያዘው ስልጣን በትግል መውረድ እንዳለበት፣ እርሱ የሚመራው ምርጫ መካሄድ እንደሌለበት፣ ከመስከረም በኋላ ህጋዊ ሀይል አለመሆኑን፣ የችግሩ መፍትሄም ይኸው ሀይል ከስልጣን ወርዶ አዲስ ሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ሁሉም ፖለቲካዊ ሀይሎች የሚሳተፉበት መድረክ እንዲፈጠር አጀንዳ ቀርፀን መላውን የኢትጵዮጵያ ህዝቦች የሚያሰባስብ ስልት እና መሪ ቃል ይዘን ስንቀሳቀስ ቆይተናል፡፡ እንደውጤቱም የህዝቦች ትግል እንዲጠናከር ትልቅ አቅም ሆኗል፡፡ በሀገር ደረጃ ከድርጅቶች እና ከህዝቦች ጋር የጀመርነውን መደጋገፍም ሆነ መተባበር እንዲሁም በውጪ ሀገር ተጽእኖ በማሳረፍ የተጀመረው እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ ነው፡፡ የግንባር ስራዎቻችን ይዘቱ በወታደራዊ እና በፀጥታ ስራዎች ዙሪያ ያተኮረ ነው፡፡ ለዚህም የተሻለ አደረጃጀት እንዲፈጠር፣ የተሻለ ብቃት ያላቸው አመራሮች እንዲመደቡ እና እንዲሰማሩ ጥረት እየተደረገ ቆይቷል፡፡ እነዚህን በሙሉ ስንደምር በሀገራዊ ትግል የተሻለ ዝግጁነት እንዲፈጠር ችሎታችንን እና አቅማችንን እንዲጎለብት የሚያደርግ ነው፡፡

በትግራይ ስለ ሰራናቸው ፖለቲካዊ ስራዎችም ሆነ በሀገር ደረጃ ስለ ነበረን ሚና በቅጥ ለመምራት ቀደም ሲል የነበረን አካሄድ እና ስምሪት አስተካክለን እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተን ቆይተናል፡፡ በየፊናው ተበታትኖ የነበረውን ስራ አንድ ላይ ተጣምሮ በተደራጀ መንገድ ለመምራትም ተሞክሯል፡፡ ከሚያዚያ ወር በኋላ ሁሉንም አቅማችንን ለማንቀሳቀስ በሚያመች የደጀን ስራዎችን የሚከታተል፣ ግንባር የሚመራ እና የሚያስተዳድር (ወታደራዊ እና ፀጥታ ሀይል አደረጃጀት እና ስምሪት) ቁጠባን እና መጠባበቂያን የሚከታተል፣ መልካም አስተዳደርን የሚከታተል፣ በሀገር ደረጃ ለሚደረገው ትግል እና የዲፐሎማሲ ስራዎቻችንን የሚያስተባብር ታስክ ፎርስ/ የልማት ሰራዊት ፈጥረን በእንቅስቃሴ ላይ ቆይተናል፡፡ ዘግይተን የገባንበት የነበረ ቢሆንም ባለፉት 4 ወራት ውስጥ እነዚህ አደረጃጀቶች ተቋቁመው ወደ ተግባር እንዲገቡ እና በየጊዜው የሚኖረውን ክስተት/ እውነታ እየታየ በስራ አስፈፃሚም ሆነ በየመስኩ እየተገመገመ እንዲሄድ እና በተደራጀ አኳኋን መምራት ጅምር አዎንታዊ እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡

ካካሄድነው ግምገማ በኋላ የተጀመሩ ስራዎች ስለመኖራቸው አመላክተናል፡፡ ይሁን እንጂ ስራው አጀማመሩ የተሻለ እንጂ በሙሉ አቅማችን ወደ ተግባር ተሻግረናል ማለት አይደለም፡፡ ሁሉም ስራዎቻችን በጥብቅ የተቆራኙ/በጣም የተያያዘ መሆን የሚገባው ደረጃ ላይ ደርሷል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ በትግራይ የምከታ ተግባራትን በሁሉም መስክ ወደ ተፈለገው ጥንካሬ እና መደላደል ላይ አልደረሰም፡፡ ከፖለቲካዊ እና ፀጥታዊ ስራዎቻችን ተሻግሮ ሌሎቹን የምከታ ተግባሮቻችንን ይዞ የወጣ አይደለም፡፡ በፖለቲካዊ ስራዎቻችንም ቢሆን በአመራርም ሆነ ህዝብ ዘንድ ስለ አደጋው ሁሉን አቀፍ ግንዛቤ እንዲኖረው የራሱን ሚና በአግባቡ እንዲገነዘብ እንዲሁም በቂ ዝግጅት በማድረግ ማንኛውንም አደጋ/ ሾክ/ የሚቋቋም እና ይህንን መክቶ መዝለቅ የሚችል ስነ-አዕምሮአዊ/ ስነ-ልቦናዊ ዝግጅት በማድረግ ረገድ ሙሉ በሙሉ እየተሻገርነው አይደለም፡፡ ምከታችንን አስመልክቶ በይዘቱ (ኮንቴክስት) በማየት ላይም ችግር አለ፡፡ በሁሉም ደረጃ የሚገኘው አመራር ይህንን ተገንዝቦ የያዘውን ስራ አድምቶ በመስራት ትርጉም/ ፋይዳ ያለው ውጤት ለማስገኘት አሁንም ከእነችግሩ ነው፡፡ ኢኮኖሚያዊ ዝግጁነት ሲባል አንዱ መደበኛ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ነው ሁለተኛው የሚገጥመንን ተግዳሮት የሚቋቋም የመጠባበቂያ እና ሌሎች ዝግጁነታችንን ለማለት ያህል ነው፡፡ ይህንን ሁለቱንም ግምት ውስጥ ያስገባ የተሳለጠ ለውጥ በማምጣት የተሻገርናቸው ችግሮች አይደሉም፡፡ ይህንን ችግር በማባባስ ኮቪድ-19 ያስከተለው ተጽእኖም ቀላል አይደለም፡፡ ገቢ ንግድ በእጅጉ ተጎድቷል፡፡ የውጪ ንግድ እንቅስቃሴያችንም የሚያስተማምን አይደለም፡፡

በመልካም አስተዳደርም ለውጥ አልመጣም፡፡ አንዱ ቁልፍ ችግር አገልግሎቱን ማሻሻል አልተቻለም፡፡ አድሎ፣ ወገንተኝነት፣ ሙስና አሁንም ቢሆን እየተፈታተነን ነው፡፡ የፍትህ ስርዓታችን በከባድ ችግር ውስጥ ገብቶ መሻሻል የማይታይበት ሆኗል፡፡ ሁለተኛው በስራ አጥነት ዙሪያ ያለው ችግር ገና ያልተፈታ ያልተሰበረ ችግር ሆኖ እየዘለቀ ነው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ረገድ መሰረታዊ ለውጥ አልመጣም፡፡ በአጭር አገላለጽ በመልካም አስተዳደር ዙሪያ ቋንጃችን እንደተያዘ ነው፡፡ በሌሎች ስራዎቻችን በተለይ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ አንፃር እንደ አጀማመራችን አጥብቀን እየመራነው አይደለም፡፡ በሽታው የሚያስከትለው አደጋ እና ከዚህ ጎን ለጎን ተንሰላስሎ እየሄደ ያለው ህገወጥ ስራም ቀላል ፈተና አይደለም፡፡ ይህንንም ከምከታ ተግባሮቻችን ነጥለን ልናየው የሚገባ አይደለም፡፡ በሚዲያ ስራዎቻችን አሁንም ቢሆን በአፈፃፀም እና ውጤታማነት ዙሪያ ችግሮች እንዳሉ ናቸው፡፡ የተቀመጠውን አቅጣጫ/ እቅድ በጥብቅ ይዞ በመሄድ/ በመጓዝ ችግር አለ፡፡ በትግራይ ለምከታ ተግባራት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በዋናነት ደግሞ ቅድሚያ በመስጠት በመስራት ላይ ችግር አለ፡፡ ህዝባችንን በማንቃት፣ በማደራጀት እና በማሰማራት አቅም ሆኖ አልወጣም፡፡ ሚዲያዎቻችን በሙሉ የህብረተሰቡ ክፍል የሚሳተፍባቸው በማድረግም ችግር እንዳለ ነው፡፡ በሚዲያ ተቋማት አሁንም ቢሆን የአመለካከት እና የወገንተኝነት ችግር፣ ችሎታ እና የጥራት ችግሮች አሉበት፡፡ በሀገር ደረጃ በሚደረገው ትግልም እነዚህ ችግሮቻችንን ቀላል አይሆኑም፡፡ እየጎለበተ የመጣውን አዲሱ ሀገራዊ ክስተት/ እውነታ በከፍተኛ ደረጃ ስበን/ አጉልተን ወደፊት አልወሰድነውም፡፡ በእርግጥ በቅርብ ጊዜያት የተጀመሩ ስራዎች ያሉ ቢሆንም አሁን ካለው በላይ ጠላትን የሚያዳክም ንቅናቄ/እንቅስቃሴ መዝምዘን በተፈለገው ደረጃ አልወሰድነውም፡፡ ከእኛ ጋር አብረው መስራት የጀመሩትን ድርጅቶችን ከጥቃት የሚከላከል/ የሚያድን የትግል አግባብ ቢያንስ ህቡዕ የትግል ስልት /አግባብ እንዲፈጠር በሁሉም ረገድ የሚያስፈልገውን ድጋፍ አድርገን እንቅስቃሴው/ ንቅናቄው እንዲጠናከር አላደረግንም፡፡ ካስቀመጥነው ስትራቴጂ እና ታክቲክ አንፃር ይህንኑ ነክሰን ይዘን በመሄድም ቢሆን ገና ከችግር አልወጣንም፡፡ በዋናነት የሚታየውን ቁልፍ ተግባር/ ተግባሮች በቅደም ተከተል አስቀምጠን ስምሪታችንም ሆነ እንደአቅማችን ያለን ሀብት ለዚህ ተገዢ ሆኖ በጥብቅ ዲሲፕሊን በመተግበር ረገድም መታየት ያለበት ነው፡፡ ይህንን ሀይል የማሰናበት ግልጽ የስራ አቅድ ይዘን በሙሉ አቅማችንም አልተገባንበትም፡፡ በፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ስራዎቻችንም ይህንን ከግምት ያስገባ ትስስርም ሆነ ለፖለቲካዊ ስትራቴጂያችን ተገዢ የሆነ ወታደራዊ ቅኝት እና ስምሪት መታየት የሚገባው ነው፡፡ ከዚህም አልፎ የተፈጠረውን ተፈላጊነታችንን ግምት ውስጥ ያስገባ ፈጣን እና ጊዜ እንደሌለን ተመልክተን እንቅስቃሴ በማድረግ ሂደትም ያለን ጉድለትም እንደ ቀላል መታየት የለበትም፡፡

## 1.3.2. ወደ አዲስ ፖለቲካዊ ምዕራፍ ያሸጋገረ የትግራይ ምርጫ

ያካሄድነው ምርጫ 6ኛ ክልላዊ ምርጫ ይባል እንጂ በይዘቱም ሆነ በውጤቱ የመጀመሪያ እና ታሪካዊ ነው፡ የትግራይ ህዝብ የታገለው ራሱ የሚያዘው፣ ራሱ የሚያወጣው እና የሚያወርደው መንግስት ለማቋቋም፣ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ሲል ነው። ለዚህ መብትም ሲባል ከማንም ህዝብ በላይ ታግሎ፣ መስዋትነት ከፍሎ ያረጋገጠው መብት ነው። ታግሎም ህገ-መንግስት እንዲሰፍር አድርጓል። ይሁን እንጂ ስልጣን ላይ ባለው ጠላት ሳቢያ መብቱ፣ ክብሩ እና ህልውናው አደጋ ውስጥ እንዲገባ ሆኗል። የትግራይ ህዝብ ይህንን አደጋ ለመመከት ላለፉት 2 አመት ከመንፈቅ ያህል ጊዜ በትግል እና ምከታ ሂደት ቆይቷል። በትግል ያረጋገጠውን መብት ጠላት ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት ተንቀሳቅሷል። ህ.ወ.ሓ.ት እና የትግራይ ህዝብ ግን የሆነው ቢሆንም ምርጫውን በወቅቱ እናደርጋለን፣ ስንፈልግ የምናደርገው፣ ሳንፈልግ የምንተወው አይደለም ብለን ወስነን በጽናት ገብተንበታል። ይህንን ስናደርግ ከሁሉም በፊት ድርጅታችን ከሚለይበት እምነት ይመነጫል። የህዝብ ውሳኔ ሰጪነት ከድርጅታችን መሰረታዊ ችካሎች አንዱ ነው፡ እዚህ ላይ ልንሳሳት አንችልም። ሁለተኛው ህገ መንግስታዊ ግዴታችንም ጭምር ነው። ሶስተኛው የገባንበትን ፈተና ለማለፍም አማራጭ አልነበረንም። ምርጫውን አድርገን ህጋዊ መንግስት ከማቋቋም ሌላ እድልም ሆነ አማራጭ አልነበረንም።

የትግራይ ምርጫ እንዳፉት ሁሉም ምርጫዎች አይደለም፤ የራስን እድል በራስ የመወሰን፣ ራስ ገዝ አስተዳደር ምርጫ እና የመመከት ምርጫ ነው። ያካሄድነው ምርጫ ፀረ-ጠላት የሚደረገው ትግል ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የደረሰበት፣ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ሌላ ፈተና በሆነበት እና ከጊዜ አንፃርም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሆነን ያካሄድነው ነው። ካለፉት ምርጫዎች የሚለየው በትግራይ - ትግራይን መስለን ያካሄድነው ምርጫ ነው። ይህ ለእኛ አዲስ ነው፤ እንዲህ ላለው ምርጫ እንደ ድርጅት ግልጽ ስትራቴጂ አስቀምጠን፣ ግቦቻችንን ለይተን አባሎቻችንን የሚገራ እና የሚመራ የስነ ምግባር ደንብ አወጥተን ወደ ተግባር ገብተናል። እንደ ድርጅት የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ለማስፋት ብለን ህገ-መንግስቱን እና የምርጫ ህጉን አሻሽለን ፖለቲካዊ ድርጅቶች እንዲወዳደሩ የሚያደርገውን እድል አስፍተን የ3 ወር እድሜ የሞላውም ሆነ 45 አመት የሆነው ለዛውም ስልጣን ይዞ የቆየውን 13 አባላት የያዘም ይሁን ከግማሽ ሚሊየን በላይ አባላት ያሉት ድርጅት እኩል ገንዘብ፣ እኩል የአየር ጊዜ፣ እኩል የውድድር እድል እንዲያገኙ የተቻለንን ጥረት አድርገናል። የምርጫ ውጤት ከታወቀ በኋላም ቢሆን የተለያዩ ሀሳቦችን/ አመለካከቶችን ለማስተናገድ በማሰብ ተፎካካሪ ድርጅቶች ካለ ድምጽ ሸንጎ ውስጥ ገብተው

እንዲሳተፉ የሚያደርግ ታሪካዊ ውሳኔ ወስነናል፡፡ በእውነቱ ትግራይ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ምህዳሩን ለማስፋት በተጣበበ ጊዜ ውስጥም ሆነን ቢሆን የተቻለንን ሁሉ አድርገናል፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ አንድ ላይ ተሰባስቦ እንደ ህዝብ አንድ አይነት ድምጽ፣ አንድ አይነት አቋም ይዞ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ የትግራይ ህዝብ አዲስ ታሪክ ሰርቷል፡፡ በሀገርም ሆነ በአለም ይህ ህዝብ ማን ነው የሚያሰኝ አስደማሚ ታሪክ ሰርቷል፡፡ ያካሄድነው ምርጫ ምከታችን የደረሰበትን ደረጃ በግልጽ አሳይቶናል፡፡ በአዲስ ምዕራፍ አዲስ ታሪክ እውን ያደረገ ፍፃሜ ነበር፡፡ የትግራይ ህዝብ ያመነበትን አድርጓል፡፡ የትግራይ ህዝብ መርጦ - ድል አድርጓል፡፡ የትግራይ ህዝብ እና ህ.ወ.ሓ.ትን መለየት፣ ስንጥቃት መፍጠር እንደማይቻል በተግባር አሳይቷል፡፡ በመላው ህዝባችን ዘንድ በራስ የመተማመን እና የድል አድራጊነት መንፈስ ተጨማሪ ጥንካሬ ፈጥሮለታል፡፡ ከራሱም አልፎ በሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ተምሳሌት ሆኖ ጽናትን አስተምሮ መንፈሳዊ ቅናትን ፈጥሯል፡፡ መላው አለም የትግራይ ምርጫን ተከታትሎታል፣ ጽናታችንን አይቶታል፣ ቀልብም ስበናል፡፡ በጠላት ጎራ ውስጥም ይህ ነው የማይባል መጠነ ሰፊ ሴራዎች እና ማስፈራሪያዎች ፈጥረው ካመንበት ወደኋላ እንዲመልሱን ጥረት ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም፡፡ አያደርጉትም ያሉንን እንግዲህ አድርገነዋል፡፡ ከማድረግም አልፎ ሳይወዱ ስለ ምርጫው እንዲነጋገሩ አድርገናል፡፡ ይህ ነው የነበረው የትግራይ የምርጫ ሂደት እና ውጤት፡፡

የትግራይ ምርጫ እንዲህ አይነቱን ድል ያስጨበጠን ቢሆንም ታግለን በጽናታችን ያመጣነውን ድል ፈተና ይዞ እንዲመጣ እና ፈተና እንዲወልድ አድርጓል፡፡ የትግራይ ህዝብ ከምርጫ በኋላ የሚጠብቀው ከግምትም በላይ ነው፡፡ ድርጅታችን እጃችንን ታጥበን በማለዳው ምርጫውን አድርገናል፡፡ አሁን ደግሞ እጁን ታጥባ ማልዳ በመነሳት ፍላጎታችንን፣ ጥያቄያችንን መመለስ አለባት፣ በአስቸኳይ ለውጥ እንድታመጡ፣ ከዚህ በኋላ ምክንያት መስማት አንፈልግም እያለን ነው፡፡ የህዝባችን ፍላጎት እንዲህ አይነት ሆኖ ሳለ በአንፃሩ አመራራችን ደግሞ ምርጫውን ድል ስላደረግን ዕረፍት እንዲያደርግ እና እፎይ ማለቱን እየተመኘ ነው፡፡ ለዛውም በመልካም አስተዳደር፣ ስራ አጥነት የሚታየውን የተዳፈነ እሳት እያየን ገና እየባነነ አይደለም፡፡ የትግራይ ህዝብ ካለው አስተዋይነት የተነሳ ሁኔታዎቹን አይቶ እና ተመልክቶ ሙሉ በሙሉ ድርጅታችንን መርጧል፡፡ ይህ ማለት ግን ቅሬታ ያለበት፣ አማራጭ ፈላጊ አልነበረም ማለት አይደለም፡፡ በተለመደው ነባራዊ ጊዜ ውስጥም ቢሆን ቀላል የማይባል ድምጽ ከእኛ ጋር ባልኖረ ነበር፡፡ ይህንንስ በተገቢው አኳኋን እየተገነዘብነው ነው ወይ የሚለው መታየት አለበት፡፡ ለማንኛውም

በመጣንበት አካሄድ በፍፁም ረጅም ልንጓዝ አንችልም አደጋው ከውስጣችን መምጣት የሚችል እና የህብረት/ የብዝሃ ሁከት እና አመጽ ምንጭ ሊሆን የሚችል ፈተና ነው፡፡ ካለ ምንም ጥርጥር አሁን በጋለ የእሳት እቶን ላይ ነው ተቀምጠን የምንገኘው፡፡

የምርጫው ሂደት በመሰረቱ ስኬታማ የነበረ ቢሆንም ልንማርባቸው የሚገባን ጉድለቶች ግን ነበሩበት፡፡ የዴሞክራሲያዊ ትግል ባህሪ በሁሉም መዋቅራችን በአግባቡ አልጎለበተም፡፡ ጤነኛም ሆነ የዛገ አመለካከት በምርጥ የሀሳብ ትግል መረታት/ መሸነፍ ገና አላሳደግነውም፡፡ በዚህ ረገድ የሚታይ ጉድለት የለም - አልነበረም ማለት አንችልም በተሻሻለው የምርጫ ህግ እና ውጤቱ ተገቢውን ማብራሪያ ስላልሰጠን የፈጠረው መደነጋገርም ቀላል አልነበረም፡፡ ከፊሉ ሆነ ብሎ ከፊሉ ደግሞ ሳይገነዘብ የፈጠረው መንጫጫት የህዝብ ውጤት እና ውሳኔ እንዲዛባ የሚያደርግ ዝንባሌዎቹም ታይተዋል፡፡ በከፊል ፖለቲካዊ ድርጅቶች ዘንድ እየታየ ያለው ገባ ወጣ ማለትም ሌላው በቀጣይ መታየት ያለበት ነው፡፡ ከመሰረታዊ ባህሪያቸው የሚታይ አመለካከትም አሁን እየጎላ እየመጣ ነው፡፡ የፈጠርናቸው እድሎች እልፍ የሆኑ እና ቅድመ ሁኔታዎችን እየደረደሩ ልጃገረድ መንገድ በማፈላለግ ይውላሉ፡፡ ይህም ሄዶ ሄዶ በምከታችን ላይ የሚፈጥረው እክል አሳንሰን ማየት የለብንም፡፡ ስለዚህም ሁኔታውን ከግምት በማስገባት ከእልህ ርቀን እንድናቀርባቸው፣ አብረን እንድንሰራ፣ ህዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ እና በተቻለ መጠን በምከታ ጉዞዋችን አቅም እንዲሆኑን መስራት አለብን፡፡

ምርጫ ቁልፍ እና ወሳኝ የግጥሚያው ነጥብ ነው ያልነውንም በተግባር እየሆነ ያለው ነው፡፡ ጠላት ህጋዊ ምርጫችንን ለማራከስ ብዙ እየጣረ ነው፡፡ የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድም እየሞከረ ነው፡፡ ለህልውናው ሲል እኛን መፈናፈኛ ለማሳጣት የሚችለውን ሁሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በእኛ በኩል ይህንን ተከትሎ የሚመጣ ማንኛውም አይነት ፈተና በፍፁም ልንቀበል አንችልም፡፡ በመሰረቱ ይህንን ሀይል ለማስወገድም ሁሉንም አይነት ርብርብ ወደ ማድረግ እንሸጋገራለን፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የሚኖር ፈተናም ሌላ ከምርጫችን ጋር ተዛምዶ መታየት አለበት፡፡

### 1.3.3. በትግራይ የምከታ እድል እና ፈተና ድምዳሜ

የጀመርነው ትግል እና ምከታ ከግብ እንደሚደርስ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ የእስካሁኑ ትግላችን የፈጠረልን አቅም አለ፡፡ የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ አንድ ላይ ሰምሮ ሁሉንም አይነት ተቃርኖ እና ፈተና መሻገር የሚያስችለውን ዝግጁነት እና የትግል ጽናት ተጎናጽፏል፡፡ እንሻገረዋለን የሚል

የአሸናፊነት እና የድል አድራጊነት መንፈስ በሁሉም ዘንድ አለ፡፡ በዚሁ ፈታኝ መድረክ እየተፈተነ እየመራው የሚገኘው ድርጅታችን እና አመራርም አለ፡፡ የተሟላ እንኳ ባይሆን በምክታችን ዙሪያ ምላሽ የተመጣጠነ አመለካከት ፈጥረን የተግባር ርብርቡን የሚያሳልጥ አደረጃጀት እና ስምሪት አስተካክለን መንገዱን ጀምረናል፡፡ ምክታችንን ወደ ከፍታ ለማድረስ የሚያስችለንን ስኬታማ ምርጫ አካሂደን ድርጅታችንን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አሸንፎ የወጣበትን ይህንን ተከትሎም ህጋዊ መንግስት አቋቁመናል፡፡ ስለዚህም የቀጣይ ትግላችን አንድ ቁልፍ መነሻ በዚህ ሁኔታ ዙሪያ ነው፡፡

በሀገር ደረጃ ህዝቦች እያካሄዱት የሚገኙት ትግል ተጨባጭ እና ነባራዊ ሁኔታ ለትግሉ ያለው አመቺነት እና ከእኛ ጋር አብሮ የመታገል እና የመደጋገፍ ፍላጎታቸውን እና ተነሳሽነታቸውን ብሎም ትግሉን በመደገፍ የጀመርናቸውን ስራዎች በሙሉ የቀጣይ ትግላችን ሌሎች ዕድሎች ናቸው፡፡ ከጥንካሬዎቻችን የሚነሳ በውጪ መፍጠር የጀመርነውን ተጽእኖ አማራጫችን እንዲሰማ በሀገራዊ ሁኔታዎች ሚናችን በአግባቡ እንዲረዱ እና ተፈላጊነታችን ይበልጥ እንዲጨምር እድል የሚሰጥ ሁኔታም አለ፡፡ ጠላት በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ዲፕሎማሲ ረገድ የደረሰበት መዛባት እና ኪሳራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሸነፍ እንደሚችል በግልጽ ገሀድ የወጣበት ምዕራፍ ላይ መድረሳችን ሌላው ጠቃሚ ክስተት/ እውነታ የድላችንን ጉዞ የሚያሳልጥ ነው፡፡ እድሎቻችንን በአግባቡ አስፍተን ፈተናዎችን በብቃት አሸንፈን ወደ ዘላቂ እና አስተማማኝ ድል መድረስ አለብን፡፡ ድላችንም ነባራዊ ሁኔታውን ከመሰረቱ ቀይሮ የሀይል ሚዛን ሙሉ በሙሉ ወደ እኛ እንደሚያጋድል የሚያጠራጥር አይደለም፤ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠርም በኢትዮጵያ ቁልፍ ሀይል እና አቅም እንሆናለን፡፡ ፍትህ፣ ርትዕ የሚገኘው መስመራችንን ይዘን በትግላችን እና በክንዳችን ነው፡፡ ችሎታዎቻችን እዚህ ላይ በሚደርሱበት ወቅት ሁሉም ሊከተለን እንደሚችልም የሚያጠራጥር ነገር የለውም፡፡ ይህ ስለሆነም ነው ስለ ዘላቂ ጥቅማችን ከወዲሁ ጀምረን መተንበይ እና ማሰብ አስፈላጊ የሚሆነም፡፡

ያለንበት መድረክ እድሎችን ብቻ ሳይሆን ለከባድ ፈተናዎችም የተጋለጠ ነው፡፡ ትግል በባህሪው ዳገት እና ቁልቁለት ያለው እልህ፣ ጽናት እና ብልሀት ይጠይቃል፡፡ ይህ ነባራዊ አደጋ ከሁሉም በላይ በትግራይ ህዝብ ላይ የተቃጣ ነው፡፡ ህ.ወ.ሓ.ትን ለማጥፋት ነው፡፡ ይህ አደጋ ከአንድ ወገን የመጣ አይደለም፡፡ ከአህዳዊያን ሀይሎች እና ከኢሳያስ ቡድን ጋር በአንድ ተጣምሮ የመጣ ነው፡፡ እነዚህ አንድ ላይ የገጠሙ/ የተቀናጁ የትግራይ ህዝብ ጠላቶች ህ.ወ.ሓ.ትን ለማጥፋት የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ ሙሉ በሙሉ ታግለን እስክናሸንፋቸው ድረስ የሚያጋጥመው

ፈተና ቀላል አይሆንም። እኛ ደግሞ ጠላቶቻችንን ለመደምሰስ እና ለማጥፋት ተገደንም ቢሆን መስማራት አለብን። ስለዚህም ጠላትን ለመደምሰስ የምናደርገው ትግል እና ከእነርሱ ሊመጣብን የሚችል ተቃርኖ ለመመከት የሚጠይቀን ትግል ከበድ እንደሚሆን ግልጽ ነው።

ስለዚህ በአንድ በኩል ጠላትን ለመደምሰስ የምናደርገው ትግል ጠላት ሊገጥመን የሚችለውን ፈተና በሌላ መልኩ ደግሞ ውስጣዊ የመፈጸም አቅማችን ያለው ውስንነት ቀላል አይደለም። እስከ አሁን ድረስ ባካሄድነው ምከታ ያሉብንን ጉድለቶች፣ በምከታችን ሁሉም አቅጣጫ ያለው ግንዛቤ እና ምከታችን የሚጠይቀው/ የሚፈልገው ጥረት እና ዝግጁነት እና ያለብን ችግር አንዱ ደርዝ ነው። ስኬታማ ምርጫችን ይዞት የመጣው ፈተናም አለ፤ አመራራችን ሁሉንም ተግባራቱን ከመስመራችን፣ ስትራቴጂያችን እና ፖሊሲያችን የተነሳ በጽኑ ዲሲፕሊን በመፈፀም አመራራችን የሰነቀውን ተልዕኮ በብቃት ጨብጦ በተጨባጭ ተግባር ውጤት የሚያስገኝ በመሆን ላይ ያሉብንን ችግሮች ግንኙነታችን እና ዝምድናችን በትግል እና ስራ ላይ እንዲንተራስ በማድረግ ላይ ያለብን ውስንነትም ገና ያልተሻገርነው ፈተና ነው። በዚሁ ቁርጥ ወቅት እንዝላልነት፣ ሀላፊነት የጎደለው አመራር እየታየ ነው፤ ለወደፊትም አይጠፋም። ለማጠቃለል አሁን ያለንበትን መድረክ በብቃት በመምራት ለመዝለቅ የአላማ ጽናት፣ ከብረት የጠነከረ አቋማዊ/ መርሃዊ አንድነት ሁኔታዎችን በብቃት መገንዘብ እና መምራት ነባራዊ አቅማችንን እስከ ጠብታ ድረስ በመጠቀም እና በማንቀሳቀስ ያሉብንን ክፍተቶች በመሙላት ለዚህ ሁሉ የሚሆን አቅም - አደረጃጀት ታታሪነት፣ ቅልጥፍና በሚጠይቀው የተለየ መድረክ ላይ ነን። ይህ ሁሉ ዞሮ ዞሮ የስትራቴጂካዊ አመራር ጥያቄ አሁንም ቁልፍ እየሆነ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

## ክፍል ሁለት: የቀጣይ ምከታ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎች

### 2.1. የስትራቴጂዎቻችን፣ ስልቶቻችን እና አቅጣጫዎቻችን ገዢ መነሻዎች

2. የተንገዳገደው ጠላት የመውደቅ መነሻ:- በዚሁ ጽሁፍ ክፍል አንድ ላይ እንደተተነተነው በትግራይ ህዝብ የተጋድሎ ታሪክ የትግራይ 6ኛ ዙር ምርጫ በአጠቃላይ ለወገን በተለይ ደግሞ ለትግራይ ህዝብ፣ ድርጅቱን እና መንግስቱን ወደ አዲስ የድል እና የትግል ምዕራፍ አሸጋግሮታል። የትግራይ ህዝብ የብሔራዊ ጠቅላይነት ፈተናን ዳግም መክቶ በጠቅላይ ሀይሎች በፍፁም እንደማይንበረከክ እና ጉዞው እንደማይደናቀፍ በአለም ህዝብ ፊት አሳይቶ ክንዶቹን አቀናጅቶ ወደ ተሻለ የምከታ ገዢ መሬት ከፍታ ላይ ወጥቷል። ጠላት ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥገኛ ውስጣዊ ግጭቶቹ እየተባባሱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ መገለሎች

እየሰሩ በተለይ ደግሞ ከብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በከፍተኛ ደረጃ እየተነጠለ ቁልቁል በመውረድ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ ወቅት ጠላት ተንገዳግዷል፡፡ ይህ ነው የሚባል ደጀን የለውም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቁልቁል እየወረደ ጀምበር እንዳትጠልቅበት የሚያደርገው የቀቢፀ ተስፋ ቅዠት እና ጭፍን እና እውነታን ያላገናዘበ ሁሉን አቀፍ እርምጃዎችን እና መተናነቆች የሚያሳይበት ወቅት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጊዜ በራሱ ለወገን ቁልፍ መመዘኛ መስፈርት ሆኖ እየወጣ ነው፡፡ በጠላት ላይ የሚወሰደው የማፈራረስ እርምጃ የወገን መረባረብ በተዘናጋ ቁጥር የመበታተን አደጋ ጥላውን እያጠላ ጠላት ተነፃፃሪ እና ጊዜያዊ ህይወት መዝራቱ የሚያስከፍለው አደጋ ሊመጣ ይችላል፡፡ ስለሆነም አሁን የተንገዳገደው ጠላትን አቅም በማሳጣት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመጣል እና ለማስናበት ወደ የጋራ ስትራቴጂያዊ ጥቃት የተሻገረበት ወቅት ብቻ ሳይሆን ሰዓቱ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ከዚህ አንፃር እስካሁን ድረስ ሁኔታዎችን ገምግመን በአጥር ውስጥ የቆዩትን እውነታዎች/ ሁኔታዎች ስንታገልላቸው የቆየናቸው ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎች አሁን ላይ ከተከሰተው/ ከሚታየው ታሪካዊ ድል እና እድል፣ ጥንካሬ እና ድክመት ጠላትን ካስወገድን/ ካሰናበትን በኋላ የሚኖረውን ሽግግር እና አቅጣጫዎቹን አጣጥመን የምከታችን ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎችን ማደስ፣ ማጎልበት እና የሁሉም ርብርቦሽ ቅኝት በዚሁ የሚካተት እና ይህንንም የሚያገለግል አድርገን የመቃኘቱ ጉዳይ ወቅቱ እና ሰዓቱ እየሆነ ነው፡፡ ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ማረጋገጥ እንችል ዘንድ ለሁኔታዎች ተገዢ ሆነው ወደ ድል የሚያደርሱንን ግቦች፣ ስራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቀጣጫዎችን ማስቀመጥ አንድ ገዢ እና መነሻ ነጥብ እየሆነ ነው፡፡

3. አሁንስ ወዴት? ከአላማችን አንፃር በትግራይ ህዝብ እና በትግራዊያን ሊህቃን ዘንድ ያለው ጥያቄ ምርጫችን ለታሪክ በሚተርፍ እና ጉዞዋችንን በሚያረጋግጥ መልኩ አጠናቀን የትግራይ ህዝብም ድርጅቱን ህ.ወ.ሓ.ትን በሙሉ እምነት መርጧል፡፡ ህ.ወ.ሓ.ት አሁንስ ወዴት ነው የሚወስደን ? ወዴት የሚል የቀጣይ ጉዞ ፍኖተ ካርታ ወይም ሮድ ማፕ ጥያቄ ጎልቶ የሚነሳበት ወቅት ላይ ነን፡፡ የሚቀጥለው ጉዞዋችን ወዴት ነው? ዘላቂ እና አስተማማኝ የትግራይ ህዝብ ጥቅም እንዴት ነው የሚረጋገጠው ? ድል እያደረግን ወደፊት ከመራመድ ይልቅ ወደ ኋላ የምንልበት ወይም የምንልመጠመጥበት ጉዞ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ሰብረን የምንወጣበት አዲሱ ምዕራፍ ምንድን ነው? በምን መልኩ ነው የምንራመደው? ካለፈው ታሪካችን እና ነባራዊ እውነታዎች/ ሁኔታዎች ምንድን ነው የምንማረው ? ወ.ዘ.ተ.... የሚሉ

መጪው አዲስ ጉዞ የትግራይ ህዝብ የሚተማመንበት ስትራቴጂ፣ ስልት እና አቅጣጫ በአስቸኳይ የማውጣት/ የማስቀመጥ እና የማየት ጉዳይ ለነገ የማይባል ኮርኳሪ ጥያቄ ሆኖ መጥቷል። በመሆኑም ቀጣይ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎች የዚሁ ነጥብ ሌላው ገዢ መነሻ መሆናቸውን ነው።

4. የእድገት/ ብልጽግና አመት 2013ዓ.ም - በብዙ መልኩ የእድገት አመት አድርገን እንድንረባረብ የሚያደርጉን ጥንካሬዎች እና ድክመቶች፣ እድሎች እና ሽንፈቶች/ ተግዳሮቶች ጎልተው የወጡበት አመት ነው። የመጀመሪያው እስካሁን ድረስ በተደረጉ የምከታ እንቅስቃሴዎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በተሞክሯቸው በመማራቸው እና መብታቸውን ለማስከበር ወደ ህዝባዊ አመጽ እና ተቃውሞ እየተሸጋገሩ የሚገኙበት እና ቃላት በውጫዊ እና ውስጣዊ ሁኔታዎች ከባድ ውጥረት ውስጥ በገባበት ወቅት በሁሉም መልኩ የተጠረነፈ/ የተማከለ እና ውህድ ህዝባዊ - ሀገራዊ ንቅናቄን በማቀጣጠል ጠላት የሚሰናበትበትን በር እና አዲስ ምዕራፍ የሚከፈትበት አመት የመሆን እድሉ የገዘፈ ነው። በሀገራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ እና የትግራይን ህዝብ ጥቅም በማረጋገጥ ረገድ የእድገት/ ብልጽግና ምዕራፍ አድርገን ልንረባረብበት የሚገባ ልዩ አመት ነው።

የዚሁ አመት ሁለተኛው እና በጣም ወሳኝ ጉዳይ የእድገት/ ብልጽግና አመት ለማድረግ የሚያስችለን ደግሞ በአጠቃላይ የህዝባችን ጥያቄዎች በተለይ ደግሞ በ6ኛው ታሪካዊ ምርጫችን ማግስት የትግራይ ህዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ እንደ አንድ ሰው የገለፀው ‹‹ድርጅቴ ህ.ወ.ሓ.ት ጎህ ሲቀድ ማልጄ ተነስቼ እጄን ታጥቤ - መድህን እንድትሆነኝ መርጩሀለሁ፤ ድርጅታችንም ካለ ምንም ማመንታት እጇን ታጥባ ህዝቧን ታገልግል›› ብሏል። የዘሩ እና አዳዲስ ብዙ እና የተወሳሰቡ የህዝባችን ችግሮችን በአስቸኳይ እና በሚያረካ መልኩ እንዲፈቱለት ከማንኛውም ጊዜ በላይ ከድርጅታችን የሚጠብቅ እና የሚተማመን ሆኗል። ይህ መጠነ ሰፊ የህዝባችን ለውጥ መሻት በትናንሽ ነገሮች፣ ጠቃቅን እና ተልካሻ ተግባራት ማርካት በፍፁም አይቻልም። መርጠን እና ለይተን አስቀምጠን ህዝባችን በወሳኝ ጉዳዮች ረክቶ ምስክርነቱን የሚሰጥበት ተአምራዊ ለውጥ ማረጋገጥ ብቻ ነው አማራጫችን። እንዲህ አይነት ለውጥ ካለ ምንም ዋል እደር በምርጫው ማግስት ጥያቄውን አንስቶታል። እየጠበቀንም ነው። የ5 አመት የለውጥ ፍጥነት በዘንድሮ አመት መጀመሪያ (2013) እንደውም በመጀመሪያው መንፈቅ አመት ማየቱን ይፈልጋል። ይህ ለውጥ እድገትን/ ብልጽግናን ከማረጋገጥ ውጪ አይታሰብም። የሚመጣው እድገት/ ብልጽግና ደግሞ ሁሉን አቀፍ ውስጣዊ አቅማችንን

አጠናክሮ ከውስጥም ሆነ ከውጪ የአደጋ ተጋላጭነታችንን የሚያስወግድ ወሳኝ እርምጃ ይሆናል፡፡

ሶስተኛው በ2012ዓ.ም የየካቲት በዓል ህዝባዊ ማዕበል ንቅናቄ ከፊል እቅዶቻችን እና ቀጥሎ የተሳለጡ ሰፋፊ የሪ-ኦረንቴሽን ስራዎቻችን በተለይ ደግሞ በ6ኛ ዙር ምርጫ ስራዎች ህዝባችንን በማንቃት እና በማደራጀት በአጠቃላይ በፀጥታ ስራዎቻችንን ዙሪያ ሰንቀነው የተሰማራንበትን እጅግ የበዛ እቅድ ነበር፡፡ በእነዚህ ስራዎች ሁላችንም ከገመትነው በላይ ስኬታማ ስራዎችን መፈፀም ተችሏል፡፡ በይዘቱ ደግሞ በምከታ እና ልማት ሰራዊት የተፈጸመ ነበር፡፡ ይህ ተግባር እና አካሄድ/ ሂደት አጠቃላይ የሞቢላይዜሽን አቅማችንን የቀየረ ፍፃሜ ሆኖ ጎልቶ ወጥቷል፡፡ ይህ በሁሉን አቀፍ ለውጥ የሚተውን ሰራዊት የእድገት/ ብልጽግና ሰራዊት በፍጥነት መፍጠር እንደምንችል በቂ ምልክት አግኝተንበታል፡፡ ወደ እድገት/ ብልጽግና ምዕራፍ መሸጋገር እንደሚገባንም እንደ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ካየነው ሁለቱም ተአማራዊ አፈፃፀም ረገድ ተኮራምቶ የቆየው ግዙፍ ሀይላችን እንደፈታነው የታየ እውነታ ሆኗል፡፡ ለአመታት መፈፀም ሲያቅቱን የነበሩ የተለያዩ የሞቢላይዜሽን ስራዎች ዛሬ በወራት ለዛውም በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ትልልቅ ፍፃሜዎች ተሰቷል፡፡ በአንድ ጀምበር የመራጮች ምዝገባ 51% ፣ በሶስት ቀናት ውስጥ ደግሞ 91% መራጭ ህዝባችንን መዝግበናል፡፡ ባለፉት 4 አመታት ማህበራዊ መሰረታችንን እናደራጃለን ብለን ተንቀሳቅሰን ያደራጀነውን እና ከሰኔ-ነሐሴ 2012ዓ.ም ባለው ጊዜ ያደራጀነው መጠን ልዩነቱ የሰማይ እና መሬት ያህል ነው፡፡ የምርጫ ሞቢላይዜሽንም ተአምር ነው፤ የፀጥታ ሀይልም በመቀስቀስ/ በማነቃነቅ እና ማሰማራትም እንደዚሁ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተኮራምቶ የቆየውን ግዙፍ የመመከት አቅማችንን ፈተን ካንቀሳቀስነው ብዙ መስክ ላይ ግዙፍ እድገት/ ብልጽግና ማረጋገጥ እንደምንችል ተምረንበታል፡፡ በመሆኑም በዘንድሮ አመት እድገትን/ ብልጽግናን የማረጋገጥ ጥያቄ ስናነሳ ህልም ሳይሆን እድገቱ/ ብልጽግናው ገሀድ የሚሆንበት የራሳችን ወርቃማ ተሞክሮ ህያው ምስክር በመጨበጥ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ግን ግዙፍ እድገትን/ ብልጽግናን የመፈፀም አቅም እና መሰረት እንዳለን የተመለከትን ቢሆንም አሁን ላይ እየታየ ያለው የሞቢላይዜሽን አቅም ግን በምርጫ፣ ህዝብ ማደራጀት እና ፀጥታ ስራዎች ላይ እንደታጠረ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ እግር ብቻ ነው መፍጠር የቻልነው፡፡ የህዝባችን መልካም አስተዳደር፣ ቁጠባ እና የምከታ ቁጠባ፣ የወጣቶች ተጠቃሚነት እና ግንባታ እንዲሁም ማህበራዊ ልማት ወዘተ... ማረጋገጥን የመሳሰሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚመልስባቸው እቅዶቻችን እና አቅጣጫዎቻችን የተፈጠረውን ግዙፍ

አቅማችንን ተጠቅመን አገላብጠን ወደ መጠቀም ከፍታ አልተሸጋገርንም፡፡ ስለሆነም በአንድ እግር ከመንዝ ያልተሻገረ ነገር ግን ትልቅ የእድገት/ ብልጽግና ምልክት ተደርጎ የሚወሰድ ውጤት ማረጋገጣችንን አውቀን በሁለት እግር የሚረግጥ/ የሚራመድ እድገት/ ብልጽግና ለማረጋገጥ አልመን ከመስራት ውጪ አማራጭ የለም፡፡ ስለሆነም የዘንድሮ አመት 2013ዓ.ም የተፈለገው እድገት/ ብልጽግና አይነት እና ደረጃ እንደፈለገ የህዝባችን ተስፋ እና የምከታው መነሳሳት/ መነቃቃት ሙሉ በሙሉ የሚጠብቅ የማለም አቅማችንን አጎልብተን ልንገምት/ ልንተነብይ፣ ልናስብ የሚያስችለንን አስገራሚ አሰራር ሁሉ አስቀምጠን እስከ ጠብታ ድረስ ለመረባረብ የምንዘምትበት፣ የምስማራበት አመት ነው፡፡ ሌላው ገዢ መነሻችን ይኸው ነው፡፡

5. ዳግማዊ ራ-ኦረንቴሽን፡- የማያቋርጥ የሁኔታዎች ለውጥን በፍጥነት ማስተካከል እና መተጣጠፍ በሚጠይቅ ሁኔታ ውስጥ የተለወጠውን እና የተከሰተውን ሁኔታ/ እውነታ መሰረት ያደረጉ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች እና አቅጣጫዎች እንዲሁም የሰው ሃይል የአደረጃጀት እና ስምሪት ማስፈፀሚያ የፋይናንስ ምደባ እና ስምሪት አቅማችንን በሙሉ ከዚሁ ምከታ መነጽር ተቀናጅቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠላት የሚሰናበትበትን ቅኝት ማዕከል እንዲያደርግ እና የትግራይ ህዝብ ወደ አስተማማኝ ጉዞ እንዲሸጋገር እና ለዚህም ሲባል ሁኔታዎቹ/ እውነታዎቹ የሚጠይቁት ትግል እና ታታሪነት፣ በድርጅታችን፣ መንግስታችን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መዋቅር ከላይ እስከ ታች ሙሉ ግልጽነት የሚፈጥር ዋናው ተዋናይ እና ፈፃሚ የሆነው ህዝባችን የተቀናጀ የዳግማዊ ራ-ኦረንቴሽን ስራዎችን መልሶ/ በድጋሚ የሚያቀጣጥል እና ወደ ማያዳግም ደረጃ የሚያሸጋግር፣ በዚህ በኩልም ውስጣዊ ሁሉን አቀፍ አቅማችንን ሚያስተማምን መልኩ ጎልብቶ እንዲወጣ ብርቱ ማዕበል መፍጠር ሌላው ገዢ መነሻ ነው፡፡

## 2.2. የትግራይ የምከታ አቅም ወደ ማያዳግም ደረጃ ማሸጋገር

### 2.2.1. የትግራይ የምከታ አቅም የሚያጎለብት ስትራቴጂ

I. ውስጣዊ አቅማችንን (ብቃታችንን) የማጠናከር ስትራቴጂ፡- በአጠቃላይ ድርጅታችንን ካዳነው/ ከታገደው ተሀድሶ በኋላ በተለይ ደግሞ ፀረ-አሀዳዊነት እና አምባገነን አካላት ትግል ካቀጣጠልንበት ገዜ ጀምሮ የስራዎቻችን ቅኝት በሙሉ ትግራይን ማዕከል አድርገን የትግራይ ህዝብ ህልውና እና ደህንነት ማረጋገጥ የሚል ቁልፍ መሪ ቃል ይዘን የትግራይ የምከታ አቅም ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ስንረባረብ ቆይተናል፡፡ እንዲህም በማድረጋችን እኛ ላይ የተቃጣውን ጥቃት በሙሉ ባሉበት እንዲቀሩ እንዲገቱ በማድረግ እንደ ህዝብ ደህንነታችንን አረጋግጠናል፡፡ አሁንም ይህንን የሚያረጋግጠውን ስትራቴጂያችንን ነክሰን ይዘን እንቀጥላለን፡፡ በዚህ መሰረት

በማንኛውም ሁኔታ ስር የትግራይ የምከታ ውስጣዊ አቅም ወሳኙ ስትራቴጂያችን በሁሉም በማያዳግም መልኩ ለመመከት ወደ ሚያስችለው ደረጃ ለማሸጋገር እንረባረባለን፡፡ የውስጣችን ሁሉንም አይነት ተቃርኖ እየመከትን ስልጣን ላይ ያለውን ቡድን ለመገርሰስ፣ ከአብይ ቡድን በኋላ የሚኖረው ሂደት በተጽእኖዋችን ስር እንዲመራ እና በዋናነት ደግሞ የምናምንበትን የትግራይ ህዝብ ዘላቂ መፍትሔ የምናረጋግጥበትን በአጠቃላይ ሁሉም ነገር በፈለግነው እና በተነበይነው/ ባቀድነው/ ልክ እንዲጓዝ ወሳኙ ጉዳይ የመደራደር አቅማችንን ጫፍ ማድረስ ነው፡፡ በፍፁም የማንሳሳትበት እና የማንወድቅበት ስትራቴጂ ካለ ውስጣዊ አቅማችንን የማጠናከር ስትራቴጂ ይሆናል፡፡

II. የውስጥ ስጋታችንን እና አደጋ ተጋላጭነታችንን ለይቶ የሚፈታ ስትራቴጂ፡- ከላይ እንደ ወሳኝ ስትራቴጂ የተቀመጠው ውስጣዊ አቅማችንን ወደ ማያዳግም ደረጃ የማሸጋገር ስትራቴጂ ውስጣዊ ብቻ ሳይሆን አማራጭ የሌለው የምከታችን ስትራቴጂ ነው፡፡ በመሆኑም በዚሁ የምከታ ሂደት የሚገሰግሱ አቅሞች በሙሉ በሚመጋገብበት መልኩ በማቀናጀት ጥቅም ላይ ለማዋል ይሰራበታል፡፡ የመመከት ወሳኙ አቅማችን ህዝባችን ነው፡፡ መላው ህዝባችንን የገጠር እና የከተማ፣ ወጣቶችን፣ ሴቶችን፣ ምሁራንን፣ ባለሀብቶችን በሙሉ እናነቃለን፣ እናደራጃለን፣ እናሰማራለን፡፡ ለህዝባችን በአጠቃላይ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ በተለይ የሚመደቡ የሰፊው ህዝብ ማህበራት፣ ሲቪክ - ሙያ ማህበራት፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ የመተጋገዝ አደረጃጀቶች እንዲሁም ነባር አቅሞቻችንን አንጠፍጥፈን ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ እንመራለን፡፡ በምከታ የተሰባሰቡ ፖለቲካዊ ረድፈኞች በሚያስማማን ሁሉ በጋራ ለመረባረብ እንሰራለን፡፡

ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስታችን ከላይ እስከ ታች ድምጽ በሆነው የስራ ክፍፍል እና ስምሪት እንዲራመድ ሁሉንም አቅሞች እነ ትእምት፣ ማረት እና ማልት አስተባብሮ እንደ አንድ ቡድን /ጋንታ/ የሚመራ እንዲሆን ይሰራበታል፡፡ ድርጅታችን የምከታ እንቅስቃሴውን በስትራቴጂዎቹ፣ ስልቶቹ እና አቅጣጫዎቹ በኩል ይመራዋል፡፡ የክልላችን ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እና ድርጅታዊ ስራዎቻችን አንዱ በአንዱ ላይ ሳይደረብ እና ሳይደጋገፍ ይልቁኑ ከእየ አቅጣጫው/ ከየአለበት መጥቶ የሚፈስ የሲነርጂ /የመደመር/ ውጤትን በሚፈጥር ለዚህም ሲባል እያንዳንዱ የአመራር አደረጃጀት ደረጃ እና ኮሚቴ የየራሱ ስራ እየሰራ ቁልፍ የስራ እቅድ የሚያሳካበትን አቅጣጫ ተከትለን ነባራዊ ሁኔታ/ እውነታ የሚጠይቀውን የስራ እቅድ ቅደም ተከተል ላይ ማስተካከያ እያደረግን አቅሞቻችንን ውጤታማ ለማድረግ

እንረባረባለን፡፡ አራቱም ስትራቴጂዎች አንዱ ከአንዱ ጋር እየተመጋገቡ የትግራይን የመመከት አቅም ወደ ማያዳግም ደረጃ የሚያሸጋግሩ ናቸው፡፡

### 2.2.2. የማስፈፀሚያ ስልቶችን እና አቅጣጫዎችን ለይቶ መረባረብ

#### 2.2.2.1. ፖለቲካዊ ስልቶችን እና አቅጣጫዎችን ለይቶ መረባረብ

##### I. ድርጅታችንን ለመድረካዊ ተልዕኮ ማብቃት

ሀ. ከሁሉም በፊት እና ከሁሉም በላይ ድርጅታችን ህ.ወ.ሓ.ት ይህንን ነባራዊ መድረክ እና ችግሩን በብቃት እያቀደ የያዘውን/ የሰነቀውን አላማ የሚተገብር እና ሽግግርን (ትራንስፎርሜሽን) የሚያረጋገጥ ድርጅት ሆኖ እንዲወጣ በድርጅታችን ውስጥ በሁሉም አኳኋን ትግል እና ንቅናቄ ላይ በቀደምትነት መረባረብ፡፡ ከላይ እስከ መላው አባላቱ ድረስ የአመለካከት እና የተግባር አንድነት ተደላድሎ እንዲወጣ ለዚህም ሲባል የዴሞክራሲ ውስጠ ደንብ አቅም እና የማያቋርጥ የመደብ ትግል ማቀጣጠል፤ የወትሮው የማይንገዳገድ የድርጅታችን መለያ ባህሪ ሆኖ እንዲቀጥል ተጨባጭ/ ነባራዊ የስራ እቅዶችን ይዞ መታገል፤ በድርጅታችን ከላይ እስከ ታች ተቋማዊ ግንባታውን ጥልቀት በመስጠት እና በማስፋት የድርጅታችን እና የህዝባችን የአደረጃጀት ብቃት፣ በተግባር የመምራት እና የማንቀሳቀስ/ የማነቃነቅ እንዲሁም የማንቃት ችሎታችንን ማሳደግ፤ አቅሞቻችንን አንጠፍጥፈን ለማንቀሳቀስ እና ለመጠቀም ጣምራ አመራር (ኮሌክቲቭ ሊደርሺፕ) በየደረጃው በጥብቅ ዲሲፕሊን መተግበር እና ማሳደግ፤

ለ. የአላማ መስመር ግንዛቤ/ እውቀት፣ የአላማ ጽናት እና ለአላማ መውደቅ፣ አሰላለፍን ለይቶ በመግለጽ ከወገንህ ጋር መራመድ/ መገስገስ ሁሉንም ነገር ከህዝብ ጥቅም እና አላማ አንፃር ማየት እና መተግበር፤ እውቀቱን፣ ችሎታውን የሚያሳድግ ተማሪ ካድሬ እና አባል፣ ከህዝብ ጋር የሚኖር ማህበራዊ መሰረቱን በጥብቅ የሚገነባ፣ የሚያበቃ፣ በህዝብ መጠነ ሰፊ ባህሪያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብቶ እየጠራ እና እየበቃ ብሎም አዲስ ሀይል በሰፊው የሚፈጥር የመመከት አቅሙን አጎልብቶ/ አጠናክሮ የሚወጣ የግንባታ የአሰራር መርህ የመሳሰሉትን በድርጅቱ ውስጥ ማፋፋም፤ በዚሁ አጠቃላይ ግንባታ አጥር ውስጥ ሆነን አሁን ላይ ያለው ምከታ በሙሉ ድምጽነት፣ ታታሪነት እና ጽናት እንዲሁም በራስ የመተማመን እና ሞራላዊ ልዕልና እና ብቃት ከላይ እስከታች የተቀናጀ/ የተንሰላሰለ የምከታ አመራር ለመገንባት ከወትሮው በተለየ መልኩ መስራት፡

ሐ. ድርጅታችን የሚተውንበት መድረክ እና የተሸከመውን ከባድ ታሪካዊ ተልዕኮ እና ሙሉ እምነት እና አመለካከት ጨብጦ የሩቁን አቅዶ ለተልዕኮው ፍፃሜ የሚዘልቅ/ የሚሰርጽ አጠቃላይ የአባላት ግንባታ በጥልቀት እና በስፋት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በመድረካዊ ተልዕኮው መረዳትን/መገንዘብን፣ ብቃት እና ተግባር ያለው ግዙፍ ተሻጋሪ ድርጅት ልናደርገው ይገባል፡፡ ድርጅታችን ህ.ወ.ሓ.ት የሁለት ትውልድ ባልሞላ ጉዞው የትግራይን ህዝብ ወደ በለፀገ የህብረተሰብ ደረጃ ካላሸጋገረው በትግራይ ህዝብ ህልውና ላይ ታሪካዊ ጥፋት ይሆናል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ አሁን ላይ የገጠመንን ፈተና መክተን መውጣት አለብን፡፡ ይሁን እንጂ የአሁኑን ፈተና ማሸነፍ እና የዘላቂውን ጉዞ የሚያስተማምን / የሚያረጋገጥ የሽግግር አጀንዳ ጋር አጣምረን ተቀናጅቶ እና ተመዳድቦ ድል አድርገን መውጣት አለብን፡፡ ጉዞዋችን የግንባታ ስርዓታችንን ይህንን አቅጣጫ በአግባቡ ማየት አለበት፡፡ የአሁኑ ምከታም ሆነ ዘላቂው ጉዞዋችን የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመራችን ወሳኝ ነው፡፡ ይህ መስመር እንዳይሸረሸር በውስጣችን መላው አባላቶቻችን በሰፊው ደግሞ በምሁራን ተጋሩ እና ወጣቶች በዚሁ መስመር ጥላ ስር መጠለል የሚችሉበት መጠነ ሰፊ የስራ እቅዶች ወጥተው ርብርብ ሊደረግበት ይገባል፡፡

መ. የድርጅታችን አቅም እና ችሎታ እንዲሆን እና የታሪካዊ አሰራር መርህ ሊደርስበት የሚገባው ወሰን/ ድንበር ባስቀመጠለት ፍላጎት ነው መመለስ ያለበት፡፡ የነባራዊው/ ተጨባጭ ታሪካዊ ፍላጎት ደግሞ የትግራይ ህብረተሰብ ትንሳኤ በአጭር ጊዜ ማብሰር፣ ለዘለቄታውም በአካባቢያችን በአፍሪካ ቀንድ እና ቀይ ባህር አባካቢ ጂኦፖለቲካዊ ተጽእኖዎችን የሚያጎለብት ሀያሉ ቀያጅ ድርጅታችን የሚመራው የትግራይ ህዝብ እና መንግስት ለመፍጠር አሁን ላይ ያለውን ነባራዊ ፍላጎት ለማሟላት ድርጅታችን ተልእኮዎቹ ለቅሞ እና ቆጥሮ በመያዝ ይህንን ለመፈፀም የሚያስችል ግዙፍ አቅም እየገነባው ነው ወይ? ብሎ መጠየቅ እና መፈጸም አለበት፡፡ እንዲህ አይነቱ ግዙፍ አቅም ለመፍጠር አቅዶ መረባረብ ለነገ ሳይሆን ለአሁኑ ምከታ ራሱ ወሳኝ መሰረት ነው፡፡ ለአሁንም ይሁን ለዘለቄታው ሲባል ደግሞ እየተቀባበለ የሚዘልቅ አመራር መገንባት የሁሉንም ስራዎቻችን አውራ አድርገን ልንረባረብበት ይገባል፡፡ የድርጅታችን የውስጥ የአመራር ማዕከላት (ሴንተርስ) ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ ፖሊት ቢሮ፣ ጽ/ቤቶች እና ኮሚቴዎች በመንግስት ቁልፍ ተቋማትን ለይቶ ተቋማዊ ግንባታን የሚያረጋገጥ ህዝብን፣ ቁጠባን፣ ፀጥታን፣ አካባቢያዊ እና አለምአቀፋዊ ተቋማትን ወዘተ… የሚመራ በታችኛው እርከንም ማህበራዊ መሰረታችንን የሚመራ የገጠር እና የከተማ ሞዴል በድምሩ መጠነ ሰፊ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ሀይል የሆነውን ወጣት እና ምሁር ማፍራት ነው፡፡

ይህንን በስፋት እና በጥራት የሚያግዙ የቻይና እና ሲንጋፖር ጥናቶች እና ሌሎች ተሞክሮዎችን አይቶ በአጠቃላይ የድርጅታችን የአቅም ግንባታ ስትራቴጂ በተለይ ደግሞ የፖለቲካዊ አመራር እና ተቋማት የምልመላ እና ግንባታ ዶክመንት /ሰነድ/ ማዘጋጀት፡፡

## II. ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስታችንን ለተልዕኮው ማብቃት

ሀ. አሁን በያዝነው የመንግስታችን መሰረታዊ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ተልዕኮ መንግስት የተልዕኮው እንደ ቁልፍ አስፈፃሚ እና ደጋፊ፣ የውጤት እና ሽግግር (ትራንስፎርሜሽን) መሳሪያ ሆኖ እንዲወጣ በሁሉም ረገድ መስራት ነው፡፡ ይህ ማለት የሽግግር ሪፎርሞች በየጊዜው እየተዘጋጀ የሚተገብር እና ውጤቱን የሚያረጋገጥ በየጊዜው በሚዘጋጁት አሰራር ህጎች፣ ስርዓቶች እና በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራ፣ የሚወስን፣ የህዝብ ጥያቄዎች እና ችግሮች ግልጽ ከሆነ ህዝባዊነት እና አቋም/ መርህ በመነሳት ፈጣን እና ፍትሐዊ ምላሽ የሚሰጥ፣ ብቃት እና ቁርጠኝነት ያለው ሆኖ እንዲወጣ መገንባት፡፡

ለ. በህገ-መንግስታዊ ስርዓት እና ህገመንግስት ከላይ እስከ ታች ህግ አውጪ፣ ህግ ተርጓሚ እና ህግ አስፈፃሚ፤ በህገ መንግስታዊ ተልዕኖዎቻቸው ተንተርሰው አንዱ ሌላኛውን ሳይሽፍን/ ሳይገድብ ይልቁንም አንዱ ሌላኛውን በቁጥጥር እና ድጋፍ ሚዛን የሚገነባቡበት ከሁሉም በላይ ደግሞ በስርዓቱ እና መዋቅሩ ዙሪያ ሙሉ ግልጽነት እና ተጠያቂነት - ተጨባጭ/ ነባራዊ የጋራ እና የግል አሰራርን የሚያረጋገጥ መጠነ ሰፊ ያልተማከለ ስልጣን ሙሉ ተጠያቂነትን የሚያጎለብት ሁሉም አቅሞች በየድርሻቸው የሚያነቃንቅ፣ የምከታ ሀይሎችን የሚያሰባስብ በራሱ ቅኝት የሚገነባ እና የሚያሰማራ ጠንካራ መንግስት መገንባት፡፡

ሐ. ለፈጣን ሽግግር እና እድገት በመልካም አስተዳደር፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ልማት፣ ጸጥታ እና ደህንነት ወዘተ... ዙሪያ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አመለካከቶችን ተጠቅሞ ነገር ግን በችሎታው እና ሙያው ብቃት ተወዳድሮ ባለበት ቦታ ውጤትን ያመጣ/ ያስገኘ የሚቀጥለበትን ያላስገኘ ደግሞ የድጋፍ አጥር ተበጅቶለት በዚህ ድጋፍ ወደ ውጤት ያልተሸጋገረ እንደሆነ ካለ ምንም ዋል እደር ለይቶ የሚያወጣ፣ የነፃነት እና ተጠያቂነት - አዲስ የኮንትራት ስርዓት ተፈጥሮ በተነፃፃሪ ውጤታማ ቢሮክራሲ - ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስታችን የሚገነባበት ሪፎርም በፍጥነት ተግባራዊ ማድረግ፡፡ ከአጭር ጊዜ እቅድ አንፃር ደግሞ በምከታ ቅኝት ታታሪ/ ብቁ ተዋናይ ለማድረግ በምከታው እንቅስቃሴ ላይ ትንሽም ይሁን ትልቅ እንቅፋት የፈጠረ እንደ ወንጀለኛ የሚቆጥር አዲስ ፖለቲካዊ ምህዳር ቶሎ ብለን በመፍጠር የምከታ ቢሮክራሲ በአስቸኳይ መፍጠር፡፡

መ. ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስታችን መዋቅሩ እና ተቋማቱ ለመድረካዊ ተልዕኮው ማብቃት እና ጉዳዩ ዞሮ ዞሮ ከነባራዊው ፖለቲካል ኢኮኖሚ ተነጥሎ በፍፁም ሊታይ አይችልም፡፡ ቢሞከርም ወደነበረው አዙሪት መግባት እና ውድቀት ካልሆነ በስተቀር የትም አይደርስም በመሆኑም ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይነቱ በተግባር እስከሚረጋገጥ ድረስ ባሉት ጊዜያት ውስጥ ከሁሉም በፊት እና ከምንም ነገር በላይ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስታችን ነባራዊ አቅም ግንባታ ፖለቲካዊ ስራዎች፣ የፖለቲካ ትግል እና የአመለካከት ጥራት የግንባታ አቅጣጫ ወሳኝ ጉዳይ አድርጎ የሚረባረብ ማድረግ፡፡ ትግሉ የሚመራበት ቅኝትም ከፖሊሲ እና ስትራቴጂ ጀምሮ ወደ ፓኬጅ ስራዎች ተሻግሮም ነባራዊ/ተጨባጭ የስራ መደብ እና እቅድ የመዘርዘር፣ የመረዳቱ/ የመገንዘብ እና የመተግበር ጉዳይን በዋናነት የፖለቲካ አመራር እና ትግል ጉዳይ አድርጎ የሚመለከት፤

ስለሆነም ዋነኛው የግንባታ አቅም ወደ ፊት እንዳይራመድ እንቅፋት የሆኑ አመለካከቶችን ነቅሶ በማውጣት እነዚህን ማስወገድ የሚችል የውይይት፣ ስልጠና እና ግምገማ ሂደቶችን በትክክለኛው ስልት የተመራ ተግባር እንዲሁም ይህንን የተንተራሰ ግንባታ ብሎም ተልዕኮውን ማስፈፀም የሚችል አደረጃጀት እና ስምሪት ለዚሁ ግንባታ አስኳል አድርጎ የሚፈጽም፤ ይህ በእንዲህ እያለ ግን የፖለቲካዊ ትግል እና ግንባታ ወሳኝ ድርሻን ተቀብሎ የችሎታ፣ ሙያ፣ እውቀት እና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ወደ ጎን ሳይተው በአጠቃላይ አመለካከት እውቀትን፣ ችሎታን ያጣመረ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አቅም ግንባታ ቢሮ ክራሲያዊ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ በሁሉም ረገድ የግንባታ ጠቀሜታን ያገናዘበ የየድርሻውን በመለየት ነገር ግን በጥብቅ ትስስር/ ቅንጅት የሚፈፀም የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማዕከል ያደርጋል፡፡

## III. ህዝባችንን ማንቃት፣ ማደራጀት እና ማሰማራት

### ሀ. ህዝባችንን በከፍተኛ ደረጃ ማንቃት

በትግራይ ህዝብ ላይ አሁን ላይ የተቃጣውን አደጋ ካልመከትነው እኛን ለማድቀቅ ማለትም እንደ ህዝብ ዳግም እንዳንነሳ አድርገው ሊያጠፉን ካለሙት ጠላቶች ጋር በመተናነቅ ላይ ነን፡፡ በዚህ መሰረት የትግራይ ህዝብ አደጋውን መክቶ በጠላቶቹ መቃብር ላይ ብቻ ነው ህልውናውን ማረጋገጥ የሚችለው፡፡ ጠላቶቹን ለመመከት ወሳኙ ጉዳይ ህዝባችን ሙሉ ንቃት እንዲኖረው በሁሉም መስክ በህብረተሰቡ ክፍል መጠነ ሰፊ የማንቃት/ የማንቀሳቀስ ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡ ይህ ደጀን በአስተማማኝ ደረጃ ዝግጁ የማድረግ ስራም ወሳኙ ጉዳይ ህዝባችንን ማንቃት

ነው፡፡ በዚህ መሰረት እኛ ላይ የተቃጣውን አደጋ ምንነት/ ማንነት ወታደራዊ ጦርነትም እንደማይቀር እና የጦርነቱ አይነት እና ይዘት፣ ይህንን አደጋ የምንመክትበትን እና የምናሸንፍበት መውጫ መንገዳችን እና የህዝባችን ወሳኙ ሚና ላይ በአግባቡ የተሟላ መግባባት/ ግንዛቤ እንዲፈጠር ሊሰራበት የሚገባ ነው፡፡

ጦርነቱ በተለያዩ መልኮች እና አኳኋኖች የሚመጣ በመሆኑ ጠላት የሚመጣበትን መንገድ መክተን የምንወጣ ቢሆንም እንኳ በሁሉም ረገድ ሊኖር የሚችል የጠላት ተቃርኖ ግን ሙሉ በሙሉ መፍትሄ ሊቀመጥለት እንደማይችል እና በጦርነቱ የሚመጣውን መከራ የመቋቋም ችሎታውን/አቅሙን ለማሳደግ - እንዲዘጋጅበት እና መብራት ቢጠፋም በሻማ እና ፋኖስ ለመመከት መዘጋጀት አለበት እንደማለት ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ጠላት በዚህም ይምጣ በዚያ ከላይ፣ ከታች፣ በቀኝም ሆነ በግራ፣ ከኋላም ሆነ ፊትለፊት ራሳችንን በራሳችን ለማስተዳደር የሚካሄድ ምከታ ነው እና የፈለገ ነገር ቢፈጠር እንኳን አሸናፊው የትግራይ ህዝብ መሆኑ፤ ስለሆነም ህዝባችን የሞራል እና ወኔ ልዕልና፣ ጽናት እና ኩራት ያለው ሆኖ መቆም እንዲችል በሁሉም ረገድ አቅማችን የቻለውን ያህል ርብርብ ማካሄድ እንደሚገባን ነው፡፡ በዚሁ የማንቃትም ሆነ የማደራጀት ስምሪት/ ዘመቻ እና ልዩ ዘመቻ ሁሉም እንደየ አቅሙ ቅንጣት የሚያክል አቅምም ቢሆን ትንሽ ነው ተብሎ ሳይናቅ ለማንቃት የሚሰራ ሲሆን የምከታው አስኳል የሆኑ ወጣቶች እና ሴቶች እንዲሁም ምሁራን የትግራይ ተወላጆች ግን በተለያዩ የስራ እቅዶች እና ዘመቻ ወይም ስምሪት በኩል ሊሰሩበት የሚገባ ነው፡፡

የትግራይ ህዝብ ፖለቲካዊ አንድነት መገለጫው በተጨባጭ ንቃት ወደ ከፍተኛው ደረጃ እንዳያሸጋግረው የሚጠልፉ/ የሚያደናቅፉ ኢ-ልማታዊ እና ዲሞክራሲያዊ ኋላ ቀር አመለካከቶች በአጠቃላይ ከሁሉም በተለይ ከወጣቱ ላይ ፍቀን ሙሉ በሙሉ ለምከታ ተልዕኮ ዝግጁ እንዲሆን ይበልጥ ሊሰራበት የሚገባ ነው፡፡ በዚሁ የምከታ ስምሪት/ ዘመቻ በእምነት፣ ታታሪነት እና ተሞክሮ የላቀ አስተዋጽኦ ያላቸው ነባር ታጋይ አቅሞቻችንም በልዩ የስራ እቅድ/ መደብ እንዲሰማሩ/ እንዲዘምቱ ሊሰራበት ይገባል፡፡ አሁን ያሉት የአባላት እና የሰፊው ህዝብ ማህበራት መጠነ ሰፊ መሰረት የምከታችን የጀርባ አጥንት ናቸው፡፡ በእነዚህ ላይም መጠነ ሰፊ የምከታ ስራዎችን መስራት አለብን፡፡ ሌሎች በዚሁ ምከታ አጋዥ የሚሆኑ ፖለቲካዊ አሰላለፎች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ቻምበሮች ወዘተ… በምከታ ዙሪያ ተመሳሳይ ንቃት በመጨበጥ በጋራ ለመስራት እንዲቻል ሊሰራበት የሚገባ ነው፡፡ እነዚህ ስራዎች በመፈጸም የህዝባችን ፖለቲካዊ ዝግጁነትን

አሚልተን /አንጠፍጥፈን እና አጥርተን መጨረሻ ላይ እንዲደርስ ማድረግን አማራጭ የሌለው አድርገን ልንሰራበት የሚገባ ነው።

### ለ. አሚልተን ማደራጀት

ማንኛውም አይነት ፖለቲካዊ ንቃት እና ዝግጁነት ተፈጥሮ አደረጃጀት ውስጥ ካልተገባ እና ካልተቀናጀ/ ካልተጣመረ ቀልህ ነው የሚሆነው። የነቃ ህዝብ ወደ ሀያል ሀገራዊ ሀይል እና ነባራዊ/ ተጨባጭ የምከታ አቅም የሚያሸጋግረው አደረጃጀት/ ድርጅት ብቻ ነው። በመሆኑም መላው ህዝባችን በነቂስ የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክትበት በሚሰማራበት የምከታ አደረጃጀት በአንዱ ወይም በሌላኛው ተደራጅቶ እንዲመክት ልንረባረብበት ይገባል። ህዝባችን በሚሊየኖች የተደራጀባቸውን የልማት ቡድኖች እና የ1ለ5 ወይም ለ7 መረቦች እንዲሁም የፀጥታ አደረጃጀት/ አወቃቀር ያቀፈ ህዝባችን በተለየ ትኩረት ሰጥተን ጥልቀት እና ስፋት እንዲኖረው ልንሰራበት የሚገባ ነው። ከዚህም አልፎ የነባር አቅሞቻችን አደረጃጀት፣ የተለያዩ የሲቪክ እና ሙያ ማህበራት አደረጃጀቶች፣ የሐይማኖት ተቋማት አደረጃጀቶች ወዘተ… ሁሉንም አቀናጅቶ እና አሚልቶ ለምከታው እንዲውሉ ማድረግን ለይተን በማስቀመጥ እቅዱን እንሰራበታለን።

### ሐ. አሚልተን ማሰማራት

ንቃተ ህሊና ካለ አደረጃጀት ዋጋ እንደሌለው ሁሉም አደረጃጀትም ከነባራዊ/ ተጨባጭ ተልዕኮ እና ስምሪት ውጪ የሚደርስበት ነገር የለውም። በመሆኑም በግልጽ ተልዕኮዎች ላይ የተንተራሰ/ መሰረት ያደረገ ዘመቻ ጉድለቱ እየታረመ ወደ ተጨባጭ ውጤት እና ድል የሚያሸጋግር ወሳኝ ተግባር ነው። መላው ህዝባችንን ለማሰማራት ቁልፍ የስምሪት ማዕከሎቻችንን ለይተን ለማስቀመጥ መረባረብ። የድርጅታችን የመሪነት/ የአመራር ስምሪት ወይም ዘመቻ መሰረታዊ አደረጃጀት እና ሴል፣ የህዝባችን ዘመቻ/ ስምሪት ደግሞ የልማት ቡድን፣ መረብ እንዲሁም የፀጥታ እና የሰላም አደረጃጀቶች ናቸው። የእነዚህ አደረጃጀቶች ተልዕኮም በየጊዜው ከሚኖሩ ሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥ እና የሚያድግ/ የሚጠናከር ሆኖ በጥቅሉ በምከታ ቁልፍ ጉዳዮች (ፖለቲካዊ፣ መልካም አስተዳደር፣ ሰላም እና ደህንነት፣ በኮሮና፣ ምጣኔ ሀብታ/ ቁጠባዊ እና ማህበራዊ ልማት) ደጀን ራሱ የሚጠናከርባቸው፣ ከደጀን ወደ ግንባር ማጠናከሪያ ወዘተ… የሚሆኑ ተልዕኮዎችን መሰረት ያደረገ ሰፋፊ ስምሪቶችን መምራት፣ ማስተባበር እና ስራዎችን ማስፈጸም፤ አሚልተን/ አንጠፍጥፈን መሰማራት እንችል ዘንድ የታችኛው እርከን አደረጃጀት የማያቋርጥ ተቋማዊ ግንባታ ማለትም ሙሉ በሙሉ በድጋፍ እና ቁጥጥር ስር በማስገባት በጥብቅ

ዲሲፕሊን የሚመራ ሁሉን አካታች የልማት እና የምከታ ሰራዊት ግንባታ እና ስምሪት እንዲሆን ማድረግ፡፡

## IV. የትግራይን አቅም ለማጎልበት ዴሞክራትነትን ማጠናከር

ሀ. የትግራይ ዴሞክራትነት ማስፋፋት እና ማጠናከር በአጠቃላይ ለትግራይ አዲሱ የትንሳኤ ጉዞ እጅጉን መሰረታዊ ነው፡፡ በአላማ/ ፕሮግራም/ ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ እምነት ድርጅታችን የሚታገልበት በሁሉም ረገድ ህዝብ ወሳኝ ነው የሚል እምነት ነው፡፡ ይህንን መሰረታዊ መርህ ይዘን የትግራይን ዴሞክራታይዜሽን ጥልቅ እና ሰፊ የምናደርግበትን ሁኔታ እንዲፈጠር እንደ ገዢ እና መሪ ድርጅት ግልጽ አቅጣጫ ይዘን ከላይ እስከ ታች ተናበን ልንሰራበት ይገባል፡፡ በትግራይ አሁንም ሆነ ለወደፊቱ በርከት ያሉ ፖለቲካዊ አሰላለፎች እንዲሁም የተለያዩ የህዝብ አደረጀቶች እና ሲቪክ ማህበራት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡ በመሰለው ተደራጅቶ የሚታገልበት ዴሞክራታይዜሽን በትግራይ ደረጃ አስተዋጽኦ እንደፈለገ ቢሆንም ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስ ባለ አቅም ነው፡፡ እነዚህ አቅሞችም የትግራይ ህዝብ አቅም የሚሆንበትን ተጨባጭ/ ነባራዊ አቅጣጫ ይዘን መስራት አለብን፡፡ የፍትህ፣ ሰብዓዊ መብት እና ዲሞክራሲ ተቋማት - ተቋማዊ ግንባታቸውን ለማጠናከር ሚዲያ በትግራይ ዴሞክራሲ ግንባታ ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ በከፍተኛ ደረጃ የሚጫወት እና የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያንፀባርቅ መሳሪያ ለማድረግ ብሎም የትግራይ አቅምን እና ብቃትን ለማጠናከር እንረባረባለን፡፡

ለ. የአቅጣጫችን ማዕከል የትግራይ ፖለቲካዊ ማህደር እንዲሰፋ / ጥልቀት እንዲኖረው የትግራይ ህዝብ እና ትግራይ የሀሳብ እና ክርክር ሜዳውን በማስፋት የትግራይ ህዝብ የምከታ እና የትንሳኤው ንፁህ መስመር/ አቋም ላይ መግባባት/ ኮንሰንሰስ/ የፈጠረ ህዝብ በማድረግ በፍጥነት ወደ ምከታ እና እድገት/ ብልጽግና ጫፍ እንዲሸጋገር ማድረግ ነው፡፡ ሁላችንንም የሚገዛ የትግራይ ዴሞክራታይዜሽን/ ዴሞክራትነት መርህ/ አቋም እያስቀመጥን ነው፡፡ ጥላቻ፣ ቂም እና መቃቃር እየጠበበ የተሳለጠ እና ዴሞክራሲያዊ የሀሳብ ክርክር፣ የልዩነት እና የአንድነት ህዝባዊ ባህል፣ የፖለቲካ ገበያ እና ሽቀጥ የሚገድል በዚህ ፋንታ መርህም፣ ሀሳብን እና ክርክርን ያሸነፈ አስተሳሰብ መሪ የሚሆንበት ለትልቁ ጥቅም ልዩነትን ይዞ በአንድነት መዝመት/ መሰማራት ወዘተ የመሳሰሉትን እሴቶች ለማስፋት እና ጥልቀት እንዲኖራቸው በማድረግ በዚህም ብለን የትግራይ ህዝባዊ እና ዴሞክራሲያዊ ባህል ከኒዮሊነራል ዴሞክራሲያዊ ባህል የተሻለ - ጥልቀት እና ዘለቄታ ያለው ለማድረግ በሰፊው

ልንሰራበት የሚህባ ነው፡፡ በዚህ የሚፈጠረው የትግራይ አቅም ሁላችንም ከምንገምተው በላይ ነው፡፡ ይህ አቅም ለአሁኑ የምከታችን ለወደፊቱም ደግሞ የትንሳኤያችን አቅም ነው፡፡

ሐ. በድርጅታችን ውስጥም አዲስ የትግል አቅም በሚፈጠርበት መልኩ በሰፊፊው ልንሰራበት ይገባል፡፡ ይህንን አቅጣጫ ነክሰን/ አጥብቀን ይዘን ተፈፃሚ ለማድረግ እንደ ገዢ ድርጅት መጠን ካድሬዎቻችንን፣ አባላቶቻችንን እና ደጋፊ ህዝባችንን ልናስገነዝብ እና ልናስተምር ይገባናል፡፡ ከአስተሳሰብ እና ክርክር አለም ውጪ አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ የሚደረገው ጉዳት እንደ ጥፋት እየታየ ከላይ እስከ ታች ሀሳብን በሀሳብ የማሸነፍ ምህዳር እየጎለበተ ሲመጣ ተወደደም ተጠላ አመራራችን እና አባላችን አላማውን ዝርዝር ስትራቴጂዎቹን እና ፖሊሲዎቹን ታጥቆ ወደ ሀሳብ አውደ ውጊያ እንዲገባ እና እንዲያሸንፍ የሚያስገድድ አዲስ የድርጅት ውስጥ ዴሞክራታይዜሽን እና ንቃትን ይፈጥራል፡፡ በዚህም ያልነበረውን አቅም በድርጅታችን ውስጥ ለማጎልበት/ እንዲያቆጠቁጥ ለማድረግ ብቸኛው ምርጫችን አድርገን ልንሰራበት ይገባል፡፡

መ. ከፖለቲካዊ ሰልፎች እና የተለያዩ አደረጃጀቶች ጋር ግልጽ በሆኑ ውይይቶች ዙሪያ በጋራ የሚያገናኙንን ለይተን እና ተገንዝበን ለመስራት እንረባረባለን፡፡ አሁን ላይ በትልቁ ምከታ አለ፡፡ በምጣኔ ሀብት፣ ቁጠባ፣ መልካም አስተዳደር እንዲሁም በሚያገናኙን ነጥቦች እና በትግራይ የዴሞክራታይዜሽን እና ፖለቲካ ጉዳዮች ወዘተ… በምከታ ፎረም፣ በፖለቲካዊ ሰልፎች ፎረም፣ በባይቶ ትግራይና (የትግራይ ሸንጎ) ተሳትፎ ወዘተ… አብረን ለመስራት አልመን እንቀሳቀስበታለን፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉተ  እዚያም ሆነ እዚህ የሚያስተሳስር/ የሚያጋምድ ገመድ የሌላቸው ይልቁንም የጥፋት መሰረት የሆኑ ሰልፎች/ ሰልፈኞችም ይሁን ሌላ መልክ እና አደረጃጀት ያላቸው መልሰው ወደ ባርነት እና ኋላ ቀርነት የሚመልሱን ብልጽግና እና አገልጋይ ባንዳዎች (5ኛ ረድፍ) አንድም ደጋፊ እንዳያገኙ የማጋለጥ እና ማግለል አቅጣጫን ነክሰን እንረባረባለን፡፡ በዚህም አቅሞቻችንን ለማሰባሰብ / ለማከማቸት እንሰራለን፡፡

ሰ. የትግራይ ዴሞክራታይዜሽን በትልቁ የሚመሰረተው በህዝባችን ቀጥተኛ እና የተደራጀ ተሳትፎ እና ትግል ላይ ነው፡፡ በዚህ ረገድም ሁለት እና ሶስት የሚሆኑ መሰረታዊ አቅጣጫዎችን ይዘን ልንረባረብበት ይገባናል፡፡ የመጀመሪያው ህዝባችን ቀጥተኛ ተሳትፎውን የሚያሰፋበት እና ጥልቀት እንዲኖረው የሚያደርግበት አቅጣጫ፣ አሰራር እና ስርዓት ለመዘርጋት ሊሰራበት የሚገባ ነው፡፡ ከህገ-መንግስታችን ጀምሮ ሌሎች ህግጋቶችንም በማሻሻል የህዝባችን ቀጥተኛ

ተሳትፎ የሚያረጋግጡ መብቶች ተጠናክረው እንዲወጡ እንሰራበታለን፡፡ በተጨማሪም አሁን የተጀመረው የምርጫ ስርዓታችንን ማጠናከር በመጪው ምርጫ የታችኛው መዋቅሮች በተለይ የጣቢያ/ ቀበሌ ምክር ቤቶች ምርጫ የፓርላመንታል ስርዓት የሚጠይቀው በድርጅቶች የሚቀርቡ እጩዎችን የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ተጣጥሞ ህዝባችን በቅርብ አስተዳዳሪዎቹ ተሳትፎ እና ተጽእኖ የሚሰፋበት አሰራር መታየት ያለበት ነው፡፡ ሹመትን በመስጠት እና በማጽደቅም እንዲሁ፡፡

ሁለተኛው የአባላቶቻቸው ጥቅም መከበር የሚቆሙ (ቫይብራንት) ማህበራትን የመፍጠር እና የማጠናከር ጉዳይ ነው፡፡ የህዝብ ማህበራት ነፃ እና ጠንካራ ማህበራት ድርጅት እና መንግስት ሲበላሹም ተቀጥላ የማይሆኑ ይልቁንም ከጥቅማቸው እየተነሱ የሚቃወሙ እና የሚደግፉ እንዲሆኑ ለማድረግ ከዚህ በፊት የተቀመጡት አቅጣጫዎቻችን እንደተጠበቁ ሆነው በመጠኑ/ በትንሽ ጀምረን የቆየነውን የማህበራት አመራር የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት እንዳይሆኑ ማድረግ የሚለውን አስፍተን ከላይ እስከ ታች ድረስ ያሉት የማህበራት አመራር እና ቦርድ የውሳኔ ድምጽ (60-70%) የየደረጃው አመራር አባል ያልሆነ እንዲሆን በማድረግ ነው፡፡ የሚገባው የፓርቲ አባል በአስተሳሰብ ተጽእኖ ከማሳደር እና ለማሳመን አልፎ የመወሰን ድምጽ እንዳይኖረው የሚያደርግ አሰራር እንከተላለን፡፡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠረው አባላችን ሆነ ካድሬያችን ግን የማህበር አባል ሆኖ በአባልነቱ እቅዱን እየያዘ በማሳመን ብቻ የሚመራ እንዲሆን አድርገን አዲስ የትግል አቅም እና ብቃት ማጠናከር አለብን፡፡ 30 አመት ሙሉ ተናግረን ትርጉም ያለው ለውጥ አላመጣንም፡፡ የሰፊው ህዝብ ማህበራት ነፃ አቅም ፈጥረው የማይተቹት/ የማይነቅፉት እና የማይቆጣጠሩት ድርጅት እና መንግስት ህዝባዊ ባህሪውን ጠብቆ ሊቀጥል አይችልም፡፡ ሶስተኛው ህዝብ በመሰለው እንዲደራጅ የማበረታታት እና በጋራ እየተደጋገፉ መስራት እቅድ የወጣለት አቅም ማሳደግ/ ማጎልበት የመሳሰሉትን ጉዳዮች በማጠናከር የህዝባችንን ተሳትፎ እናሳድግ፣ የትግራይ ዴሞክራታይዜሽን ጥልቀት እና ስፋት እንዲኖረው በማድረግ አስገራሚ አቅም እንፍጠር፡፡

## V. ሚዲያችንን ወደ ሙሉ አጀንዳ ቀራጭነት እና አጥቂነት ማሸጋገር

በሚዲያ ስራዎቻችን ኦን ላይን ሚዲያን ጨምሮ ተጀምሮ የቆየው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ወደ ሙሉ አጀንዳ ቀራጭነት እና አጥቂነት ደረጃ እንዲሻገር ሁሉም የውስጥ እና የውጪ የምከታ ሚዲያዎች በመተባበር በ4ኛው ረገድ (ትግራይ፣ ሀገረ ኤርትራ እና ዲፕሎማሲ) ተጠናክሮ እንዲወጣ በሁሉም መስክ ርብርብ ሊደረግበት ይገባል፡፡

ሀ. በትግራይ የሚዲያ ስራዎች - ሚዲያዎቻችን ከምንም በላይ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩበት የሚገባው ትግራይ ላይ ነው። በትግራይ ህዝብ ወሳኝ ግጥሚያ ዙሪያ ከፊት ስላለ በዚህም መሰረት የምከታ ፖለቲካዊ፣ ፀጥታ፣ ሰላም፣ ቁጠባዊ እና ማህበራዊ ሂደት በጽሁፍ በተለይ ደግሞ በማንቃት፣ ማደራጀት እና ማሰማራት በአጠቃላይ ደግሞ በትግራይ እንዲሰሩ የተቀመጡት ስልቶቹን እና አቅጣጫዎቹን መሰረት ያደረገ ዝርዝር አቅድ በሚዲያ ኮሚቴ እና ቋሚ የሚዲያ ኮሚቴ ወጥቶ እና ፀድቆ መጠነ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ እና የቅስቀሳ ስራዎች ሊሰሩበት ይገባል። በአካል በየመድረኩ የሚፈፀሙ ሰፋፊ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማለት ነው።

ለ. በሀገራችን - ሚዲያዎቻችን በሀገራዊ ፖለቲካዊ መድረክ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ አድርጎ በመውሰድ የተንገዳገደውን ጠላት ማሰናበትን ማዕከል ያደረገ በሁሉም ጫፍ በሁሉም ቋንቋዎች የአጀንዳ ቀረፃ እና ጥቃት የተሟላ ልዕልና/ የበላይነት እንዲኖረው ማድረግ። በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፣ የፌደራሊስት ሰልፈኞች፣ ሲቪክ ማህበራት እና የተለያዩ አደረጃጀቶች ጠላትን በማሰናበት ቅኝት እንዲነሱ ከተሞክሯቸው አስተማሪ፣ የችግሩ ምንጭ እና መፍትሄም ይኸው ቡድን ሲጠራረግ ብቻ መሆኑ፣ ስለሆነም ደግሞ ጠላትን ለመጣል መነሳት እንደሚገባቸው፣ ጠላት ጊዜ ባገኘ ቁጥር በዚህች ሀገር ህዝቦች ላይ የሚያደርሰው ጥፋት እና ውድመት ስፍር ቁጥር እንደሌለው፣ ይህ ቡድን ከተሰናበተ በኋላ የሚኖር መፍትሄዎች እና ጥቅሞች፣ የሰላም እና ደህንነት ጥሪ እና አስፈላጊነት ወዘተ ዝርዝሩን በመያዝ በከፍተኛ ደረጃ መረባረብ። በሌላ መልኩ ደግሞ ጠላት ያጎደፈው የትግራይ ህዝብ እና ህ.ወ.ሓ.ት ምስልን የሚያጠራ በትግራይ ህዝብ ላይ እየደረሱ ያሉ በደሎች፣ ግፍ እና ውርደቶች ሁሉም ህዝብ እንዲገነዘቡት የሚያደርግ ወዘተ… ዝርዝር እቅድ ወጥቶለት ሊሰራበት ይገባል።

ሐ. በኤርትራ - ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያቀራርብ መተማመን እና መግባባት የሚፈጥር በተለይ በእኛ በኩል ያለውን አመለካከት እና ስሜት የሚገልጽ እና የሚያስረዳ ካለፈው የትጥቅ ትግል ጋር በማያያዝ የኢሳያስ ቡድን ያልቃ ገብነት፣ ፀረ ሰላም እና ፀረ ዲሞክራሲ እንቅስቃሴው ለትግራይ ህዝብ እና አካባቢው ብቻ ሳይሆን ይልቁንም የከፋው ገጽታው ለኤርትራ ህዝብ እንደሚተርፍ በመሆኑም ደግሞ የኤርትራ ህዝብ በኢሳያስ ቡድን ላይ በተቃራኒው መቆም እንዳለበት እና የትግራይ ህዝብ ከጎኑ እንደሆነ የኤርትራን ሰራዊትንም ጨምሮ በሰፊው መስራት።

መ. በአለም ማህበረሰብ - ሀገርን ለማዳን የያዝነው አቋም/ መርህ፣ ያስቀመጥናቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች በሰፊው መገንዘብ፣ ጠላት እየሄደበት ያለው መንገድ ሀገርን እየበተነ መሆኑን እና እነሱንም ጭምር አደጋ ላይ እንደሚጥል በመሆኑም ደግሞ ይህንን በማዳን አቅማቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በአጠቃላይ ሚዲያችን በኦን ላይን ሚዲያ ያለንን ጉድለት አርሞ በተደራጀ እና በተቀናጀ አኳኋን በየምዕራፉ ግልጽ እና ዝርዝር እቅድ እየወጣለት፣ በጥብቅ እየተገመገመ፣ ከውስጥ በሰፋፊ የአቅም ግንባታ ስራዎች እየታጀበ ውጤታማ ስራዎችን እንዲሰራ ማድረግ፡፡

2.2.2. **የፀጥታ እና ደህንነት ስልቶችን እና አቅጣጫዎችን ለይቶ መረባረብ**

I. **ህዝባዊ ምከታን ለማረጋገጥ ፀጥታ እና ደህንነት**

ሀ. ምከታችን ህዝባዊ ምከታ፣ ህዝባዊ ጦርነት ስለሆነም ለጦርነቱ ስኬት/ ጦርነቱን በድል ለመወጣት ደጀን ነው፡፡ ወሳኝ ነው ሲባል ሌላው ቁልፍ ገጽታው መላውን ህዝብ ተንተርሶ ፀጥታ እና ደህንነት የሚረጋገጡበትን ስራዎች ሲሳለጡ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ረገድ ተጀምሮ የቆየው ህዝባዊ የፀጥታ እና ደህነት ስራዎች ጎልብተው ካሉት የተልዕኮ እና አደረጃጀት ሁኔታ ጋር ጥልቀት እና ስፋት እንዲኖረው ከመላው ህዝብ/ ደጀን ለሚመነጨው ዝግጁነት መነሻ የሚሆኑ ውይይቶች እና ግምገማዎች፣ ተሞክሮዎች በድጋሚ ተጠናክረው እንዲወጡ መስራት፡፡ ነፍስወከፍ ጣቢያ /ቀበሌ/ መንደር እና ጎጥ የየአካባቢያቸው ጥበቃ እና ቁጥጥር፣ የአስተማማኝ ሰላም ቀጠና እንዲሆን በሌላው መልኩ ደግሞ የታጠቀው አጥቂው ሀይላችን /ግንባር/ ጋር የተሟላ ድጋፍ እና ትስስር በመፍጠር ደጀን እና ግንባር በማይለይ የምከታ እንቅስቃሴ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል የተሟላ ዝግጁነት እንዲኖር መስራት፡፡

ለ. የጦርነቱ ገጽታ/ መልክ የተለያየ ስለሚሆን ጠላት እኛን ለማጥቃት ሊጠቀምባቸው ከሚችላቸው ብዙ አውዶች ከራሱ እና የኢሳያስ ቡድን ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ህቡዕ ስለላ፣ የገዳይ ስኳድ/ ቡድን/ ሽብር እና የፖለቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ማዕከሎችን የሚያወድም ወዘተ… ቡድኖች ከተቀናጀው የባንዳዎች እና አገልጋዮች የትብብር አመፆች ጋር በመቀናጀት በህቡዕ በከተሞች የጦር መሳሪያ ዝውውር እና ጥቃት ሊያጋጥም የሚችለውን ተዛማጅ ውስብሰብ ተግባራትን ለመከላከልም ይሁን ለማጥቃት የህዝባዊ ምከታችን ፀጥታ እና ደህንነት አንድ አካል ተደርጎ መላው ህዝብ በየአደረጃጀቱ እንዲከታተለው፣ እንዲመክተው በሚያስችል ሁኔታ ተለይቶ ሊሰራበት ይገባል፡፡

ሐ. ከላይ የተቀመጡ የጠላት ተቃርኖዎች መሰረት የሚፈጥርበት አጠቃላይ ውስጣዊ የፀጥታ ሁኔታዎቻችን ባለበት ደረጃ የሚወሰን ነው። የውስጥ ሰላም እና ፀጥታ የሁከት/ አመጽ እና ግርግር፣ የተደራጀ ሌብነት፣ ስርቆት አመጽ እና ግድያ፣ የከተማ ሽፍታነት ወዘተ… ለዚህም መሰረት የሚሆን ሰፊ ስራ አጥነት እና ቦዘኔነት ተይዘው ፀጥታን እና ሰላምን ለማረጋገጥ የጠላቶቹን ተቃርኖ መመከት አይቻልም። ስለሆነም ህዝባዊ ምከታ ውስጣዊ ፀጥታ እና ደህንነት ማረጋገጥ ላይ በከፍተኛ ትኩረት ሊሰራበት እና በሙሉ ቁጥጥር ስር እንዲገባ ተደርጎ በሰፊው ሊሰራበት የሚገባ ዋናው አውድ ይሆናል። በአጠቃላይ በህዝባዊ እንቅስቃሴ/ ንቅናቂ የሚረጋገጥ የፀጥታ እና ደህንነት ስራ ነባር አቅሞቻችን የሆኑትን ወጣቶች እና የፀጥታ ሀይሎችን እንደ አስተባባሪ አድርጎ አሁን የተጀመረውን ብርቱ ንቅናቄ/ እንቅስቃሴ ከእነ ተሞክሮዎች ተገምግመው እና ተጠናክረው እንዲወጡ ማድረግ።

**II. ግንባር**

የህዝባዊ ምከታችን ጫፉ የሰላ መቺው/ አጥቂው ሀይል ለመከላከልም ሆነ ለማጥቃት መተኪያ የሌለው ሀይል ነው። በዛሬው የውጊያ ባህሪያት ደጀን እና ግንባር በማይለይ መልኩ የተቀላቀለ ሲሆን በምከታው ተልዕኮዎች ላይ ግን ግልጽ ልዩነት ይዞ ባለ ስለት ተልዕኮውን የሚሸከም ሀይል ለይቶ በራሱ ስትራቴጂ፣ ስልት እና አቅጣጫ እንዲሁም ወታደራዊ ሳይንስ እና ጥበብ ለመገንባት መዘጋጀት ያለበት ነው። በዚህ አቅጣጫም ሁኔታዎችን ከግምት እያስገባ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መጥቷል። አሁን ላይ ሁኔታዎች የደረሱበት እድገት እና ለወደፊቱም የግጥሚያ ሁኔታ እና ሊደርስበት የሚችለውን ደረጃ ታሳቢ በማድረግ መገምገም እና መዘርዘር የሚገባቸውን ጉድዮች በጥንቀት እና በስፋት እንዲታዩ እና የራሱን ስትራቴጂካዊ እና ኦፕሬሽናል አቅዶችን አዘጋጅቶ እንዲመራ ማድረግ ነው።

### 2.2.2.3. አስቸኳይ እና ህዝባችንን የሚያረካ የመልካም አስተዳደር ለውጥ

**I. ፈጣን ስኬት (ኲውክ - ዊን) ፈጣን ፍቱን መድሃኒት (ኲውክ - አክቲንግ)**

ሀ. ከስኬታማው ታሪካዊ ምርጫችን በኋላ የትግራይ ህዝብ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ ለውጥ ለማየት በጉጉት ከሚጠብቃቸው ጉዳዮች የመጀመሪያው እና የሁሉም ራስ የሆነው መልካም አስተዳደር ነው። ከዚህም የፈጣን አገልግሎት እና ውሳኔ እንዲሁም ምክክር እና የተሳትፎ ጉዳዮች ናቸው። በእነዚህ መስኮችም እስከ መጀመሪያው መንፈቅ አመት ህዝብ የሚመሰክርበት ፈጣን ድል እና የመጪው ጊዜ ተስፋ የሚያለመልም ወሳኝ እርምጃዎች የግድ መውሰድ ይገባናል። በዚህ መሰረት ለፈጣን ድል የመጀመሪያው እርምጃ በትግራይ ደረጃ ነገር

ግን በሁሉም እርከኖች/ ደረጃዎች ላለመርካት ወሳኝ የሆኑ ችግሮች በሙሉ የህዝብ እና አመራር ተሳትፎ ከሞላ ጎደል መለየት፤ በዚህ ሂደት መለየት የሚቻለውን እና የማይቻለውን ማለትም ሊቆዩ እና አሁን ሊፈፀሙ የሚገባቸው ጉዳዮች ከህዝባችን ጋር ለመነጋገር እድል ከማግኘታችን በላይ የችግሮቹን ቅደም ተከተል ማለትም በከተማም ይሁን በገጠር ያሉትን ለይተን እነዚህ ላይ ተመስርተን በክልል፣ ዞን እና ወረዳ እንዲሁም ጣቢያ/ቀበሌ ደረጃ ካለ መወላወል ፈተን መልሰን ለህዝቡ እናቀርባለን እናውጃለን፡፡ በእነዚህ ድርጊቶች ወደ ኂላ የሚያፈገፍግ አመራር እና ሲቪል ሰርቫንት ላይ ካለ ምህረት እርምጃ መውሰድ፤ ፈጣን ድል የለመለመ ተስፋ፡፡

ለ. የሚወሰኑ ጉዳዮች አዳዲስም ይሁኑ ነባር ጉዳዮች በየአይነታቸው እና ባህሪያቸው ተለይተው ጉዳዩ ይሆናል አይሆንም የሚወሰንበትን ከፍተኛው ጊዜ ለይቶ ማስቀመጥ እና ለህዝቡ ማሳወቅ ከተቀመጠለት ጊዜ የዘለለ/ ያለፈ ውሳኔ ያልሰጠ አመራር እና ሲቪል ሰርቫንት በተጨባጭ እርምጃ የሚወሰድበትን የአሰራር መመሪያ ወጥቶ ሁሉም አውቆት አሰራሩን ተመስርቶ እርምጃ መውሰድ፡፡ እንደየ ባህሪያቸው ጉዳዮቹ ከቀረቡበት ከሰዓታት እስከ ቀናት ሳንምንት እና ሳምንታት ተለይተው በማስቀመጥ ወደ ተጨባጭ ትግል እና ለውጥ በመግባት በአገልግሎት አወሳሰን ላይ የሚታይ/ የሚዳሰስ ለውጥ ማረጋገጥ፤ በዚህ ረገድም ፈጣን ድል - የለመለመ ተስፋ፤

ሐ. በእነዚህ እርምጃዎች ለእንቅፋትም ለድልም ወሳኙ ፖለቲካዊ አመራሩ ነው፡፡ በሚያስተባብረው አካል ወይም ምድብ ሴክተር ዝርዝር እቅድ ወጥቶ ተቆጥረው ለሚመለከተው አመራር በግልጽ ውይይት እና ሙሉ ተጠያቂነት ይሰጣል፡፡ በዚህ ዙሪያ እንቅፋት የፈጠረ አመራር ምንም መወላወል የሌለበትን ተጠያቂ ማድረግ፣ ቀጥሎ በእንቅፋትም ሆነ ድል ድርሻ ያለው ሲቪል ሰርቫንቱ ነው፡፡ ሲቪል ሰርቫንቱ በዚህ እንቅስቃሴ ዙሪያ ግልጽ ውይይት እና ቅስቀሳ ተደርጎበት የመልካም አስተዳደር ችግር በአስቸኳይ ባለመፈታቱ በምከታ ሂደት ላይ የሚኖረውን ፋይዳ/ ትርጉም በማየት እንቅፋት መሆን ‹‹ፀረ-ምከታ›› ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ከፍ በማድረግ በማስረዳት በእምነት እና ተነሳሽነት ግዴታ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ በዚህ እንቅፋት የሆነውንም ካለምንም መወላወል ተጠያቂ ማድረግ፤ ከወሰንክ ነው የምትጠየቀው ብሎ እጅ እና እግሩን አጣምሮ ወንበር ላይ ተቀምጦ ህዝብን አለአግባብ የሚያንገላታ እና ይህንንም ያልተገባ ድርጊት ቅቡልነት እንዳለው የሚወሰድበት ሁኔታ ግልባጩ ሳይወስኑ እና ምላሽ ሳይሰጡ ወንበር ላይ መቀመጥ እንደማይኖር በገሀድ ማሳየት፡፡

**II. አማካይ ጊዜ**

አማካይ ጊዜ እየተባለ ያለው ረጅሙን ጊዜ በመገመት አይደለም፡፡ ከሁለተኛው መንፈቅ አመት ጀምሮ በሚቀጥሉት አመታት ውስጥ የሚሸፈን መሰረቱም በተቋማዊ ስርዓት እና ግንባታ በፈጣን ድል (ኲዊክ ዊን) የተገኙትን ድሎች ወደ ተቋማዊ ስርዓት የሚሻገሩትን በማሻገር ወደ ዘላቂው እና ሁሉን አቀፍ የመልካም አስተዳደር ስራዎችን የማረጋገጥ ስራ የሚሸጋገር አቅጣጫ ነው፡፡ ከዚህ የተቋማዊ ስርዓት እና ግንባታ ጎል ለጎን የፈጣን ድል ስራዎች እየተሳለጡ ቆይተው የሚቀጥሉበት መሰረታዊ መፍትሄ ይሆናል፡፡ ዘላቂ ተቋማዊ መፍትሄ ከ 2037ዓ.ም ራዕይ እና ግብ ተሸርፎ በተቀመጠው የ5 አመት የስራ እቅድ ለእያንዳንዱ አመት በተዘረዘረው እቅድ ላይ የሚመሰረት ይሆናል፡፡

### 2.2.2.4. ምክታውን እና ከምክታ ባሻገር ፈጣን ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ልማትን የሚመለከት

**I.** ፈጣን ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ልማትን ማረጋገጥ በሁለቱም ነገር ግን በጥብቅ የተያያዙ አቅጣጫዎችን በመንከስ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በአንድ በኩል በቀጥታ ከምክታው ጋር የተያያዙ ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ስራዎች አሉ፡፡ ምክታው የሚጠይቀው የራሱ ምጣኔ ሀብት አለ፤ ምክታው የሚጠይቀው ግዙፍ መጠባበቂያ አለ፡፡ በቀጥታ ለምክታው የሚያስፈልግ ግዙፍ ሎጂስቲካዊ አቅም አለ፡፡ በዚህ ላይ የጠላት እንቅፋት እና ውስብስብነት አሁንም እየታየ ነው፡፡ ይህም እስካልተሰናበተ ድረስ የሚቀጥል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተጀመሩ የመፍትሄ አቅጣጫዎቻችን ግን ጎልብተው ያልወጡ አሁን ካለው ስህተት/ እድገት እንደገና ተከልሶ ወደ ተለያየ ርብርብ መግባት የግድ ይላል፡፡ ጠላት እኛን ለማጥቃት - ጥቃት የሚፈጽምባቸውን አውዶች እና የተጀመሩ መፍትሄዎቻቸው ብሎም ካሉበት ደረጃ ጋር በመገምገም ማስተካከል እና በተጨባጭ ትግብረ የሚፈልግ ይሆናል፡፡ ጦርነት ለማካሄድ የሚጠይቀው ግዙፍ ሎጂስቲክስ እና ሌሎች የፋይናንስ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጮች በሙሉ ተፈትሸው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ተመሳሳይ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ አማራጮችን አካቶ የተለየ ነገር ግን የተለያዩ የሀብት ሞቢላይዜሽን ስራዎች በታቀደ እና በተተለመ መንገድ መታየት ያለበት ነው፡፡

**II.** በምክታ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት እንብርት ላይ ሆነን በምክታው ትርጉም ያላቸውን የወጣቶች የስራ ፈጠራ ልክ እንደ መልካም አስተዳደር ፈጣን ድል የሚያረጋግጥበት አውድ ተፈትሾ የሚጀመርበት ሁኔታ መፍጠር፡፡ በመሰረቱ ግን የወጣቶች የዘላቂ የስራ እድል ከአጠቃላይ የሽግግር እቅዶች ማለትም የግብርና እና ኢንዱስትሪ ሽግግር የስራ መደብ ጋር ተያይዞ ነገር ግን

ራሱን የቻለ አዲስ ፓኬጅ መቅረጽ እና ለተግባራዊነቱም መረባረብ እና ማየትም የሚያስፈልገው ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ከምከታው ምጣኔ ሀብታዊ እና ትራንስፎርሜሽን በእርሻ/ ግብርና እና የእንስሳት ሀብት ጨምሮ ለዘንድሮ አመት ካጋጠመው የአንበጣ መንጋ ጋር የወደፊታችን ክረምት ድርቅ የሚከሰትበት ትንበያን ግምት ውስጥ ያስገባ መጠነ ሰፊ የመስኖ እና ውሃ ማቆር እንዲሁም ሞቢላይዜሽን ስራዎች ላይ በተለየ ትኩረት የምንረባረብበት መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ባሻገር ጉልበት፣ መሬት፣ ገበያ እና ምርታማነት፣ የገጠር ፋይናንስ እና ኢንደስትራላይዜሽን ወዘተ… ከራዕይ 2037ዓ/ም በመነሳት በአጠቃላይ በቀጣይ 5 አመታት በተለይ የመጀመሪያዎቹ 2 አመታት ላይ የምንጀምረውን ሽግግር ለይተን ማንጠሪያ የሚሆን ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በከተሞች ኢንዱስትሪ በተለይ ጥቃቅን እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ፣ የፋይናንስ ስርዓት፣ ባንክ እና ኢንሹራንስ ዙሪያ በተለየ ትኩረት መረባረብ፡፡ በአጠቃላይ ለኢንቨስትመንት ትልቁ የኢንደስትሪ ኢንቨስትመንት ጥላ የሆነው ትእምት እንዲሁም ማረት ከትግራይ የምከታ ትራንስፎርሜሽን ጋር የተያያዘ/ የተቆራኘ የጋራ እቅድ ማውጣት ሊያስፈልግ ነው፡፡ በከተማ ልማት የፕላን፣ መሰረተ ልማት እንዲሁም ቤቶች ግንባታ በተለይ መከተም እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባውን የልማት ፓኬጅ ወዘተ… በትምህርት ማህበራዊ ልማት ጉዳይ በተለያዩ መንገዶች የትግራይ የትምህርትን ስርዓት የሚቀይር አቅጣጫ እንዲታይ ማድረግ፤ የፊላንድ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ሌሎች ሀገሮች ተሞክሮን ለመቅሰም በጤና ረገድ ኮቪድ 19 ጨምሮ በመከላከል ፓኬጅ (የቤት ውስጥ መውለድ፣ የግል እና አካባቢያዊ ጽዳት፣ የጤና መድን እና ወዘተ… የመሳሰሉትን) የጤና ጉዳይ ወሳኝ ትራንስፎርሜሽኖች ተደርገው ርብርብ እንዲደረግባቸው ማድረግ፡፡ በአጠቃላይ በተመረጡት የሽግግር እና እድገት መስኮች ተለይተው ማዕከላዊ ኮሚው አጽድቋቸው የተጠናከረ ጉዞ የሚጀመርበትን ሁኔታ መፍጠር፡፡

### 2.2.3. ሁሉን አቀፍ ተቋማዊ አቅም የገነባች ትግራይ (ዲፋክቶ ትግራይ)

**I.** ባለፉት ሁለት እና ሶስት አመታት ህገ-መንግስታዊ ስርዓትን ለማፍረስ የክልሎች ሉአላዊ ስልጣን ነጥቆ ሀገርን እያተራመሰ የሚገኘውን የአብይን ቡድን በጽናት እና ጥንካሬ በመመከት የራስን እድል በራስ የመወሰን እና አስተዳደር መብቶችን ለማንኛውም ሀይል አሳልፈን እንደማንሰጥ፣ ከጠላት ጋር ግንባር ለግንባር የሚያተናንን የምርጫ ጉድይም ቢሆን ይህንን መክተን ምርጫውን አካሂደን ህጋዊ ህዝባዊ መንግስታችንን መስርተን ብቸኛው ህገ-መንግታዊ ክልል ሆነን በከፊል ሀገራዊነት (ዲፋክቶ) ክልል ውስጥ ነው ያለነው፡፡ በዚህ መሰረት የክልላችን የተለያዩ ተቋማዊ አቅሞችን ብዙዎቹን ጉዳዮች ራሱን ችሎ እያሳለጠ ቆይቷል፡፡ በትግራይ ካስቀመጥናቸው እቅዶች/ ትንቢቶችን የዲፋክቶ ስቴት ሂደቱ ተጠናክሮ መጥቷል፡፡

በዚህ መሰረት የትግራይ መሰረታዊ ተቋማዊ አቅሞችን በዚህ ቅኝት እየተመራ ጎልብቶ እንዲወጣ በተጨባጭ ጥናት እና ዝርዝር የስራ እቅድ ተንተርሰን መስራት አለብን። ከላይ እስከ ታች የሚኖረን አደረጃጀትም ከዚሁ የሚመነጭ እና ይህንን እንዲያገለግል ማድረግ፤ በተለይ በፀጥታ እና ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳይ ዙሪያ ከቀረጥ እና ግብር መሰብሰብ፣ ሶስተኛ ወገን ግንኙነት እንዲሁም ንግድ እና ኢንቨስትመንት፣ መገናኛ ብዙሃን እና የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን እያሟላን የምንሄድበትን እነዚህን በሙሉ ግምት ውስጥ ያስገባ የትግራይ ህገ መንግስት በሙሉ ጥናት እና እውቀት በመመስረት የሚስተካከልበትን ሁኔታ መፍጠር። ይህ ማስተካከያ ሁለት መንገድ ሊኖረው ይችላል። በቀጣይ የሚፈጠረው አስተማማኝ ዘላቂ ጉዞ ጋር ሊያያዝ/ ሊቆራኝ ይችላል ወይም ደግሞ አሁን ባለው ፌደሬሽን ስር በመሆን የቀደመውን ማስተካከልም ይቻላል። ወጣም ወረደ በኢ-ሀገራዊነት አጥር ውስጥ ሆነን ነገር ግን የሀገራዊነት (ዲፋክቶ) ግንባታ የሚሳለጥበትን ተቋማዊ ግንባታ ላይ ጠንክረን/ ነክሰን መፈፀም ይገባናል

## 2.3. ለትግራይ ጥቅም ጠላትን መጣል እና የሀገሪቱ አዲስ ማስተካከያ

### 2.3.5. ጠላትን የመጣል ዘመቻ

#### 2.3.5.1. የእድገት እቅዶች እና ጠላትን የመጣል ግቦች

I. ከዛሬ 5 እና 6 ወራት በፊት ገደማ ሀገራዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ የትግል ልዩ ምዕራፍ እና ቀጣይ አቅጣጫ ክስተቶች/ እድገቶች ጽሁፍን አስመልክቶ ሶስት እቅዶችን ለይተን በማስቀመጥ ተንቀሳቅሰናል። አሀዳዊውን እና አምባገነን ቡድንን ማስወገድ፣ የባለ አደራ መንግስት መፍጠር/ መመስረት እና ሀገር የመበታተን አደጋ የሚሉ ናቸው። በወቅቱ እያንዳንዱ አቅድ እና የሚኖረው ችሎታንም ጭምር ወስደን ሀገር ከመበታተን ድና ጠላትም ተገርስሶ የሽግግር ባለ አደራ መንግስት ተመስርቶ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ የሚቀጥልበትን እድል ለማስፋት የሚያስችል ተጨባጭ የትግል አቅጣጫዎችን ገልፀን በመረባረብ ላይ ቆይተናል። አሁን በግምገማው እንደቀረበው ትልልቅ ክስተቶች/ እድገቶች ወደፊት ተራምደዋል። አሁን ያለውን ክስተት/ እድገት መሰረት ያደረገ እቅድ እና ግብ ዳግም መፈተሽ እና የላቀ የመሆን አቅም ያለው እቅድ ግን አደጋን የሚያስወግድ ሀገር አድኖ የትግራይን ህዝብ ጥቅም የሚያረጋግጥ እቅድ እና ግብ ለይተን ለመረባረብ በምንገደድበት ታሪካዊ ወቅት ላይ እንገኛለን።

II. እነዚህ እቅዶች/ ሴናሪዎዎች/ አሁንም መጠነኛ መስተካከያ በማድረግ መሰረታቸውም እነርሱ ናቸው። በመሆን ችሎታ / አቅም ላይ ግን ግዙፍ ለውጥ አለ። የአብይ ቡድን ሊወድቅ

የሚችልበት በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሰላም እና ደህንነት ማጣት፣ ዲፕሎማሲያዊ ሁኔታዎችም በመሰረቱ ከቦታው ተንገዳግዷል፡፡ ይህ በስልጣን ላይ ያለው ሀይል በሀገራዊ የአመራር ክፍተት (ሊደርሺፕ ጋፕ) ምክንያት በተወሰነ የሰራዊት ገመድ ካልሆነ በስተቀር መቆም የሚችልበት ነገር የለም፡፡ በማንኛውም ወቅት የመውደቅ እድሉ እየጎላ እየወጣ ነው፡፡ የዚህ ቡድን መውደቅን ተከትሎ ምን አይነት የሽግግር መንግስት ይኖራል - ሀገር ሳትፈርስ ህዝቦችም ወደ ግጭት እና መጠፋፋት ሳይገቡ በምን መልኩ ማዳን ይቻላል የሚሉ ጥያቄዎች እና መፍትሄዎቻቸው ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው እቅድ/ ሴናሪዎ በዋናነት በወገን ድክመት እና ችግር በተወሰነ መልኩ ደግሞ በምጣኔ ሀብታዊ መስክ የሚፈለገው ለውጥ እና ፖለቲካዊ መነሳሳት እና አመጽ ህዝብ የሚመራው አጥቶ በእጅጉ ከተቀዛቀዘ፣ እስረኞች ከፈታ እና ምርጫውን የማካሄድ አጀንዳ ወደራሱ ጥቅም ከተሻገረ እኛ እና ጠላት ማዶ ለማዶ (ዱዋል ፎርስስ) ሆነን በተነፃፃሪ ለአጭር ጊዜ የሚኖር ክስተት / ሴናሪዎ ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ሀገራዊ ንቅናቄው መሪ አልባ ሆኖ ሀገራዊ ድብደባ ተዳክሞ ነገር ግን የየአካባቢው ጎበዝ አበር በመሰለው የሚንዝበት፣ የአብይ ቡድንን ሀገርን የሚመራበት እና የሚቆጣጠረው አጥቶ በሚኖረው የብተና እና እያንዳንዱ ጦርነት የመከሰት ክስተት መካከል ሆኖ ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

III. በእነዚህ በተነሱት ሊኖሩ በሚችሉት ክስተቶች/ ሴናሪዎች ውስጥ ሆነን የትኛው ክስተት/ ሴናሪዎ ነው የሚበልጠው - የትኛው ነው ብዙ ፋይዳ የሚኖረው - የትኛው ነው እንደ ዋነኛ ግብ አድርገን የምንታገልበት የሚል መታየት አለበት፡፡ ይህም በሁለተኛው ሊኖር ይችላል የተባለው ክስተት / ሴናሪዎ እንደ ክስተት/ ሴናሪዎ ዝግ አይደለም፡፡ ማዶ ለማዶ ነገር ግን በተነፃፃሪ አጭር ጊዜ እንጂ ረጅም ጊዜ መቆየት አይቻልም፡፡ አንዱ በሌላኛው ላይ የበላይነት ሊኖረው ይገባል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ይህ ክስተት/ ሴናሪዎ መሆን ከቻለ ለወገን/ ለጠላት እፎይታ የሚሰጥ እና የሚጠቅም ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ ክንዋኔ እንዳይታይ ነው መታገል ያለብን፡፡ በዚህ መካከል ከተፋጠጥን ደግሞ እኛን በሚጠቅም የድርድር ጉዳይ ሊታይ ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ጦርነት እና ሀገር የመበታተን አደጋ ዘወትር ገደል አፋፍ ላይ ያለ አደጋ ነው፡፡ ይህንን አደጋ ለማቃለል ነው የምንታገለው፤ በመሰረቱ ካልተመራ ሀገር ብተና የምናገኘው ጥቅም ስለሌለ፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ክስተት / ሴናሪዎ እንዳይታይ የሚያደርግ መጀመሪያ ላይ የተቀመጠውን ክስተት/ ሴናሪዎ ግን እንዲሳካ ምርጥ አማራጭ አድርጎ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡

IV. የአብይ ቡድን በተነፃፃሪ አጭር ጊዜ (በ2013) የመውደቅ ክስተት/ ሴናሪዎ ፖለቲካዊ አውድ ጠላት አሁን የደረሰበት ከህዝብ የመነጠል / የመገለል ሁኔታ በእጅጉ ተጠናክሮ ህዝባዊ አመፆች

እና ሁከቶች በተለይ ደግሞ አሁን እየመራ ያለው የኦሮሞ ህዝብ እና ሌሎች ፍጥነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ከመስከረም 25 በኋላ ቡድኑን እንደ መንግስት ያለመቀበል ሂደት በሁሉም ፖለቲካዊ አሰላለፎች / ሰልፎች፣ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች እንዲሁም ሲቪክ አደረጃጀት ዘንድ ተጠናክሮ እንደወጣ እና እነዚህን እያስተባበረ የሚመራ ጠንካራ ሀገራዊ አመራር ባይፈጠርም ቅሉ በትንሹም ቢሆን የጠነከረው የትግራይ ህዝብ እና ህወሃት እያስተባበረ ይህንን አመጽ እና ሁከት የድርጅቶቹ ነው ወይስ ማህበራት የሚለው እንደፈለገ ቢሆንም ይህንን የሚመራ ሀገራዊ አደረጃጀት በፍጥነት እንደሚፈጠር ኢኮኖሚያዊ፣ ፀጥታዊ ችግሮች እየተጠናከሩ ከአለም ማህበረሰብ በኩል የሚኖሩ ተጽእኖዎች እየተጠናከሩ እንደሚቀጥሉ፣ የጠላት ውስጣዊ ግጭቶች እና መናከስም እንደሚቀጥሉ ብሎም እየተጠናከረ እያፍረከረከው ስለሆነ እና በዚህም ስለሚቀጥል ጠላት የሚወድቅበት ነባራዊ ሁኔታ ተሟልቷል፡፡ የአመራር እጥረት ክፍተት ደግሞ በዚሁ ላይ በማለም በአጭር ጊዜ ውስጥ በመፍታት ጠላት የሚሰናበትበት ሁኔታ እየተሟላ ነው፡፡ እንደውም ጊዜ መስጠት አያስፈልግም፡፡ የመንተት ወቅት/ ጊዜ እኛን አይጠቅመንም ባንልም እንኳ በዋናነት ግን የሚጠቅመው ጠላትን ነው፡፡ ስለሆነም ግጥሚያው በጠላት እና በትግራይ ህዝብ መካከል ሳይሆን (ከመሆኑ በፊት) በትግራይ ፀረ-ጥቃት ትግል የታጀበ ሀገራዊ ግጥሚያ አድርገን የተንገዳገደውን ጠላት የመገርሰስ፣ የመጣል ተጨባጭ ግብ ይዘን እንመክታለን - እንታገላለን፡፡ ይህ ግብ ሁኔታዎች እንደፈቀዱ የኢሳያስን ቡድንንም የሚጨምር ይሆናል፡፡

### 2.3.5.2. ግቦቻችንን የምናስፈጽምባቸው ስትራቴጂዎች

**ስትራቴጂ አንድ፡** የተቀናጀ ፖለቲካዊ ጥቃት እንደ ቁልፍ ስትራቴጂ

ጠላትን ለማሰናበት/ ለመጣል አንዱ ቁልፍ ስትራቴጂ ፖለቲካሊ ሙሉ በሙሉ ከህዝብ የሚነጥል/ የሚያገል እና ጠላትን ለመጣል ከህዝቡ የሚፈለገው ሁሉም አይነት መስዋትነት፣ የትግል እና አደረጃጀት አግባብ ጠላትን ከመጣል ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ይፋዊ የተቀናጀ ፖለቲካዊ ጥቃቶችን በማጎልበት/ በማጠናከር የጠላትን ደጀን ማፈራረስ፣ ወደ ንቁ/ፈጣን ተቃውሞ እና አመጽ መሸጋገር፣ የወገን ወዳጅነታዊ መደጋገፍን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ማድረስ፣ የመከላከያ ሀይልም ቢሆን በእነዚህ ሁኔታዎች/ እውነታዎች ከህገ-መንግስት እና ከህዝብ ጎን እንዲሆን ካልሆነ ደግሞ የጠላትን ንቁ መሳሪያ እንዳይሆን፣ ጠላትን ውስጥ ለውስጥ የሚገዘግዝ ፖለቲካዊ ስራዎችን ያካተተ ርብርብ በማካሄድ ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሸጋግሩ ፖለቲካዊ ጥቃቶችን በማፋፋም የህይወት እና ንብረት ውድመት / ጥፋት የሌለበት በዚህም ከሄደ ደግሞ በተወሰነ ኪሳራ ድልን ለመጎናፀፍ የሚያስችል አደረጃጀት፣ የሰው ሃይል እና ሀብት ስምሪት ማስተካከያዎችን በማድረግ

ተገዶ ከስልጣን እንዲወርድ እና ወደ ድርድር እንዲቀርብ የሚያደርጉ ሁሉን አቀፍ ፖለቲካዊ ጥቃቶችን የሚያስፈጽም ስትራቴጂ፡፡

**ስትራቴጂ ሁለት፡** በትጥቅ የታገዘ ህዝባዊ አመጽ እና ሁከት/ ብጥብጥ

ጠላት ተገዶ ስልጣኑን አስረክቦ ወደ ድርድር ካልመጣ አሁን እየሄድንበት ባለው መንገድ ያለውን እና የሌለውን የፀጥታ ሀይሎችን እያሰማራ ለልዩ ሀይሉ እና ለወታደሩ ይፋዊ ትዕዛዝ ሰጥቶ በማስፈራራት፣ በማሰር፣ በመግደል፣ ህዝባዊ ተቃውሞዎችን በሀይል አፍኖ ለማስተኛት በእያንዳንዱ ጫፍ እና ቤት ተሰማርቶ ነው ለሰላማዊ ተቃውሞ የወጣውን ህዝብ ካለ ምህረት ለመገመት በሚያዳግት ጭካኔ (ከደርግም በባሰ መልኩ) እየቀጨው የሚገኘው፡፡ በዚህም ምክንያት ሰላማዊ ህጋዊ ትግል እየተዘጋ ነው እየሄደ ያለው፡፡ ጀሌ እና ጠመንጃ ያዥ፣ ስጋ እና በረት እየተጋጠሙ መርገጥ አይገባም፡፡ የህዝባዊ አመፆች እና ሁከቶች / ብጥብጦች መቀየሪያ ነጥብ እንከን አልባ እና የተቀናጀ፣ የተናበበ የትጥቅ ድጋፍ የሚያገኝበትን የጠላት ፖለቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ማዕከሎች፣ መስመሮች የሚዘጉበትን፣ ወገን ሞራሉን የሚጠብቅበት - ጠላት ግብረ እኩይ የሚጨማተርበት ብሎም የሚሽነፍበት፣ የይፋዊ እና ህቡዕ አደረጃጀቶች ስምሪት እና አመራር ሌላው መተግበር ያለበት ስትራቴጂ ነው፡፡

**ስትራቴጂ ሶስት፡** ድርድር እንደ ጠላት ማሰናበቻ ስትራቴጂ

ተጋጣሚ ሀይሎች የአንዱ መድከም የሌላኛው መበርታት ወይም ደግሞ ለጊዜውም ቢሆን የሁለቱም የሀይል ሚዛን የሚተያይ/ የሚመጣጠን ሲሆንም ተመሳሳይ ድክመት ሲኖርም ወይም ደግሚ የተሻለ የመደራደር አቅም ያጎለበተ ሀይል አጀንዳዎችን የቀረፀ ፖለቲካዊ እና ሰላማዊ ልእልናን ለማረጋገጥ ወይም ከውጪ ከተለያዩ ጥቅሞች በመነሳት የድርድር አጀንዳዎችን ይዞ ስለሚመጡ አሁንም ከውስጥ እና ከውጪ በግልጽ እየታየ ያለው ወዘተ... ዞሮ ዞሮ ድርድር/ Negotiation / አንዱ ጠቃሚ የትግል ገጽታ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በበኩላችን ይህንን የትግል አግባብ ተጠቅመንም ቢሆን ጠላትን የምናንበረክክበት ጠቃሚ መሳሪያ አድርገን በስፋት ልንሰራበት የሚገባን ነው፡፡ ይህም አስቀድመንም ቢሆን የሰላም እና ሀገር የማዳን ጥሪ በሚል በይፋ ጀምረነዋል፡፡ ይህም እንደየ ሁኔታው መቀጠል ስላለበት ድርድር ደግሞ ራሱን የቻለ ሳይንስ፣ ጥበብ እና ውግንና ስላለው በየጊዜው ይህንን የሚያስተባብር ማኒፌስቶዎችን የሚያዘጋጅ፣ ስትራቴጂ የሚያዘጋጅ ወዘተ... የየራሱ ኮሚቴ ሊቋቋምለት የሚገባ ነው፡፡ በስትራቴጂ ደረጃ የጠላትን ውድቀት የሚያሳልጥ የትግራይ ህዝብ እስካሁን የተጓዘበትን ለድርድር የማይቀርብበት፣

ዘላቂ ዋስትናችንን እና ጥቅማችንን የማይነካ ውሳኔ እና የራስ ገዝ አስተዳደር የራሳችን የሚሆንበትን፣ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች (መብትን) የማይሸራረፍ ወዘተ.... በመሰረታዊ ጉዳዮች ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን ከሁኔታዎች ጋር የሚተጣጠፍ የድርድር ስትራቴጂ መታገያችን ነው፡፡

## ስትራቴጂ አራት፡ ተነሳሽነትን ጨምሮ የጠላትን ወታደራዊ ሚዛን አንገዳግዶ/አዛብቶ የሚንድ ስትራቴጂ

አሁን እየገጠምነው ያለነው ጦርነት የተለያዩ ባህሪያት እና መልኮች/ ገጽታዎች ያሉት ነው፡፡ ጦርነት ከጀመረ ቆይቶ እስካሁን በነበረው መለኪያ ጦርነቱ ተጠናክሮ ነው የሚቀጥለው፤ ከባድ የማዳከም ጦርነት (ዋር ኦፍ አትሬሽን) በለስላሳ መሳሪያዎች (ሶፍት ኢንስትሩመንት) ወታደራዊ ወረራ በሁሉም ገጽታዎች /መልኮች/ የማይቀር ነው፡፡ በወታደራዊ ጦርነት ለማጠናቀቅ / ለማገባደድ የሚገፉ ነገሮች በርካታ ናቸው፡፡ ውትድርናን የያካተተ ጦርነት ከፊታችን አለ፡፡ በመሰረቱ ይህንን ጦርነት በንቃት እና በብቃት የመከላከል ስትራቴጂ - የመመከት ተልዕኮ ነው የሚኖረን፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ጉዞ በዚሁ ይመራል ማለት አይደለም፡፡ ጠላት የተጠናከረ አቅሙን አሰባስቦ ሀይል/ ጉልበት አግኝቶ እኛን ለማጥፋት እስከሚመጣ ድረስ በመከላከል ስም፣ ጦርነትን በሩቁ ማስቀረት (ዲተረንስ) እኛ የምንጠፋበትን፣ የምንዳከምበትን እድል መፍጠር የለብንም፡፡ ተልዕኮው ዲተረንስ ብቻ አይደለም፤ ጠላትን ማሰናበትም ጭምር እንጂ፡፡

ስለሆነም ጠላትን ለማሰናበት/ለማጥፋት በሚደረገው ርብርብ ተነሳሽነትን ያካተተ ወታደራዊ ስትራቴጂያዊ ማዛባትን /ማንገዳገድን እና ማጥቃትን (ስትራቴጂክ ኦፌንሲቭ) እንዲሁ እንደ ጠቃሚ ስትራቴጂ መውሰድም የግድ ይሆናል፡፡ ይህ የጠላትን ወታደራዊ ሚዛን በማናጋት/ በማንገዳገድ ወደ ጥቃት የመሸጋገር ስትራቴጂ በዋናነት መምራትን እና ማስተባበርን ሆኖ የራሳችንን የመከላከል አቅምን በማይጎዳ በውትድርናም ወደ ሀገራዊ ጥቃት መግባትም ይገባናል፡፡ ስለሌቹም አይደለም በዋናነት ስለ ራሳችን ነው፡፡ ጠላት አቅም እና ስትንፋስ ካገኘ የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ አላማው የትግራይ ህዝብ ዳግም እንዳያንሰራራ ማጥፋትን ስለሆነ፤ አሁን ጠላት ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታው/ መስኩ ነው የተናጋው/የተንገዳገደው፡፡ ወታደራዊ ገጽታው ደግሞ መንገዳገድ / መናጋት አለበት፡፡ ወደ ስትራቴጂካዊ ጥቃት በመሸጋገር መፈፀም ያለበት ነው፤ እንደውም በጊዜው በመፈፀም፡፡

እንግዲህ ጠላትን እየጠበቅን ከመጣብን በኋላ እንገጥመዋለን ብለን እጅ እና እግራችንን አስረን ለጎራችን/ አካባቢያችን ብቻ የሚል አመለካከት በባሰ መልኩ ተጠቂ እንድንሆን ጠላት ተጠናክሮ በራሱ ስልት፣ ወቅት እና ስምሪት ውስጥ አስገብቶ እንዲያጠቃን እድል የሚሰጥ ውስብስብነት ውስጥ ላለመግባት የሚያስጠነቅቀን ስትራቴጂ ይህ ነው። በወታደራዊ ሳይንስም ቢሆን በአንድ አንድ ሁኔታዎች ማለትም ተቃራኒው ሀይል ከቀደመ ወገን ላይ የሚያደርሰው አደጋ ከባድ እና ለመሸከምም የሚያዳግት (የሚያጠፋህን) ሁኔታ በሚኖርበት ወቅት አስቀድሞ በተነሳሽነት ጠላትን ለማጥፋት የሚወሰዱ እርምጃዎችን መሰረት ያደረገ የጦርነት ክስተት (አምር - ፕሪ ኢምፕቲቭ ዋር) ሳይንሳዊ ይዘት ያለው ተግባር ነው። ይህ ስትራቴጂ መቼ ይተገበራል? እንዴት እና በማን? እምን ላይ ይፈፀማል? የሚል በስትራቴጂካዊ የማናጋት/ ማንገዳገድ እና ማፍረስ፣ የጦርነት ፕላን/ እቅድ የሚመለስ ነው የሚሆነው።

## 2.3.5.3. ጠላትን የመገርሰስ ስትራቴጂዎች እና የማስፈፀሚያ ስልቶች እና አቅጣጫዎች

I. ትግራይን አንጠፍጥፎ ማዘጋጀት፦ ከሁሉም በፊት እና ከሁሉም በላይ ቀደም ሲል በትግራይ የአቅም ግንባታ ላይ በተቀመጠው መሰረት የትግራይ ህዝብ ለዚሁ ጦርነት መዘጋጀት አለበት። ከሁሉም በፊት ፖለቲካዊ ዝግጁነቱን አንጠፍጥፎ ማገባደድ አለበት። ይህ ፖለቲካዊ ተነሳሽነት እና ውሳኔ ሳይንጠፈጠፍ ወደ ጦርነት መሸጋገር በርካታ እንቅፋቶችን ያስከትላል። ጠላት አላደርግም እያለ አሳንሶ/ ዝቅ አድርጎ እየተመለከተ በግዴታ የጦርነቱ መኖር የሞት ሽረት መሆኑን፣ የሚከተለውን መከራ ለመሸከም የሚጠይቀውን ዋጋ የመክፈል ዝግጁነት በጠቅላላው ህዝብ፣ የወጣት፣ ምሁር .... ወዘተ ሙሉ መተማመን እንዲፈጠር ማድረግ በውትድርና ረገድም በተመሳሳይ አቅማችን የፈቀደውን ሁሉ አድርገን በዋናነት በሰው ሃይላችን አመለካከት፣ አደረጃጀት እና ክህሎት ተመስርተን ሙሉ ዝግጁነትን ያረጋገጠ ሐይል እንዲኖር ማድረግ። ከዚህም ባሻገር ደጀን እና ግንባር በጥብቅ የመቆራኘት / የመተሳሰር ሁኔታ እንደ አንድ ጣምራ አቅም ዘብ እንዲቆም እና መጠነ ሰፊ የፕሮፖጋንዳ የቅስቀሳ ስራዎችን መፈፀም። በተጨማሪም የሚጠራ እና የሚጨመር አደረጃጀት፣ የሰው ሃይል እና ሀብት ስምሪትን በዚሁ መቃኘት።

II. ሀገራዊ ተነሳሽነት እና ዝግጁነት፦ ዞሮ ዞሮ አጠቃላይ ጦርነቱ እና ጠላትን የማሰናበት/ የማጥፋት ጥቃቶች ሀገራዊ ይዘት ሊኖራቸው የግድ ይላል። ስለሆነም እዚህም እዚያም ተበታትኖ የሚገኘው ሀገራዊ አቅሞቹን በሙሉ ማሰባሰብ እና ማቀናጀት/ ማጣመር የግድ ይላል። በሀገራዊ ዝግጁነት አንዱ ቁልፍ ጉዳይ ብሔር ብሔረሰቦችን እና ህዝቦችን በመጠነ ሰፊ የፕሮፖጋንዳ እና ቅስቀሳ ስራዎች ማነሳሳትን፣ ሙሉ በሙሉ ከተሞክሮ መማር ላይ ተመስርቶ ይህ ሀይል እያለ የራስን እድል በራስ የመወሰን እና የራስ ገዝ አስተዳደር መብት እንደማይኖር፣ ሰላም እና ፀጥታ የሚባል

እንደሌለ፣ እስከ ወዲያኛውም እንደማይኖር፣ ኢኮኖሚው ጠቅልሎ እየሞተ እንደሚገኝ፣ ህዝቦች እርስ በእርሳቸው እየተናከሱ እንደሚገኙ፣ ሀገርም በክህደት ሉአላዊነቷ ተጥሶ እየተበተነች መሆኑን፣ ብቸኛው መፍትሄም ይህንን ቡድን መጥረግ እና ማስናበት/ ማጥፋት መሆኑን ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው፤ የመውጫ መንገዶቹን በመደራጀት በየአካባቢው ሀገራዊ ጥምረት ፈጥሮ ጠላትን በአጭር ጊዜ መጣል፣ መደምሰስ እንደሚቻል እንዲወስን፤ የየአካባቢው አቅሞቹን በሙሉ እንዲያቀናጅ/ እንዲያጣምር፣ እንዲንቀሳቀስ፣ የተቀናጀ የሚዲያ፣ መደበኛ ሚዲያ፣ ኦን ላይን ሚዲያ፣ የህትመት ሚዲያ ከተቻለም በአካል (ገጽ-ለገጽ) መድረኮች ወዘተ… በማድረግ ወደ ውሳኔ እንዲመጣ ማድረግ። በተለይ እዚህ ላይ የኦሮሞ ህዝብ የንቅናቄው ኮር/አስኳል ሆኖ እንዲወጣ በሁሉም መልኩ መረባረብ።

III. የሀገራዊ አመራር ክፍተትን በአስቸኳይ ማቃለል፡- ጠላት በብዙ መልኩ ተሸርሽሮ ሳለ እድል ያገኘው በሀገራዊ አመራር ክፍተት (ግዙፍ የጠቅላይነት ጉድለት) ሊፈታ አለመቻሉ ነው። ይህ ችግር ከመሰረቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍታትም ያስቸግራል። ከሆነም የአሁኑን ሀገራዊ ንቅናቄ መምራትን እና ማስተባበር የሚያስችል በተወሰኑ መሪ ቃሎች እና አጀንዳዎች ‹‹መንግስት የለም፣ ምርጫውን የሚመራም የለም፣ ተሰባስበን ወደ ድርድር /ዲያሎግ/ ለመምጣትም የማይቀበለውን ሀይል እንጥረግ›› በሚል የሚሰባሰብ ፖለቲካዊ ሰልፍ ቶሎ መሰብሰብ፣ ብሄራዊ ድርጅቶችም በየብሔራቸው ጥምረት ፈጥረው እንዲነሳሱ፣ ከዚህ ባሻገር የወጣቶች  ንቅናቄዎች እና አመራሮች፣ አክቲቪስቶች፣ ምሁራን በግልም በቡድንም የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት (ባህላዊ አደረጃጀቶች)… ወዘተ በውስጥ በውጪም መረባረብ። የቅርብ ጊዜ የሱዳንን አመጽ የመራው ሀይል እና አደረጃጀት - ተሞክሮውን መቅሰም /ማምጣት። ይህንን መሰረት በማስያዝ በአስቸኳይ ሀገራዊ የጋራ ኮሚቴ፣ የጋራ ኮማንድ እስከ ታችኛው ድረስ በአስቸኳይ መፍጠር። ይህንን በመጠቀምም ወደ መደበኛ የፖለቲካዊ ሰልፎች / ሀይሎች ጥምረት መሸጋገር። አሁን ላይ ከእኛ ጋር ያለው የፌደራሊስት ሀይሎች ጥምረትን በዚህ አላማ የሚቃኝ ተሀድሶ መስጠት።

IV. የተደራጁ ሀገራዊ አመፆችን ማቀጣጠል፡- ጠላትን ለማስናበት / ለማጥፋት ትልቅ መሳሪያ ሊሆን የሚችለው በትጥቅ የታገዙ አመፆች እና ድርድር ነው። በግልጽ እየታየ እንደሚገኘው ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል በሀይል አፈና ትርጉም ወደ ሌለበት ደረጃ አውርዶታል። ስለሆነም የትግሉ መልክ / ገጽታም ሀይል የታከለበት የተደራጁ አመፆችን እና ብጥብጦችን ማዕከል ማድረግ አለበት። የተደራጁ አመፆች ወደ ወታደራዊ ጦርነት መሸጋገር እንደሚችል ታሳቢ ያደረገ ዝግጁነት እና ያሉትን የአመጽ እንቅስቃሴዎች/ ንቅናቄዎች የሚቀጣጠሉበት፣ ይህንን የሚፈጽም ግልጽ እና ህቡዕ አደረጃጀት እና ተልዕኮውን በመግለጽ ሊሰራበት የሚገባ ነው። የሚያስፈልግ

የሰው ሃይል፣ ሀብት እና የተለያዩ አደረጃጀቶችም ያስፈልጋሉ፡፡ ይህም በጎረቤቶቻችን ዘንድ መጠነ ሰፊ ባፈር ዞን በመፍጠር ከዚህም ተሻግሮ የሚዘልቅ እና ራሱን የቻለ የተለየ ዝርዝር እቅድ የሚኖረው እንቅስቃሴ / ንቅናቄ በመደገፍ ጭምር የሚሰራበት ነው፡፡

V. ባፈር ዞን ማስፋት እና ማጠናከር፦ የምከታ እንቅስቃሴው በሁሉም አቅጣጋርጫ ለማጠናከር በአጠቃላይ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የተደራጁ የፌደራሊስት ሀይሎች ጋር በጋራ የሚካሄድ ምከታ እያጠናከርን በተለያየ ትኩረት እና ዝርዝር የስራ እቅድ ደግሞ ከጫፍ እስከ ጫፍ አጎራባቾቻችን ከሆኑት ህዘቦች አፋር፣ አገው፣ ቅማንት እና የአማራ አካባቢዎች የምከታውን አቅሞች ለማድረግ ልንረባረብበት የሚገባን ነው፡፡ ይህ ስራ እስካሁን ድረስ የሄደበትን ርቀት አሁን ያለው የሰው ሃይል አደረጃጀት እና ስምሪት ተገምግሞ በሁሉም መልኩ ተጠናክሮ እንዲራመድ / እንዲገሰግስ የሚሰራበት ይሆናል፡፡ ህዝብ ለህዝብ፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የጎሳ መሪዎች፣ የምሁራን፣ የወጣቶች እና ሴቶች ወዘተ… ድርጅት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ጥምረት እና ሁሉን አቀፍ መደጋገፍ መሰረት ያደረገ የጋራ ትግል በማጎልበት ጠንካራ የምከታ ባፈር ዞን ለመፍጠር አልመን በፍጥነት/ በአስቸኳይ ልንዘምትበት/ ልንሰማራበት ይገባል፡፡

VI. የሀገር አቀፍ ምርጫ አጀንዳ ለጠላት ፋታ እንዳይሰጥ ማድረግ፦ ጠላት ከባህሪው የሚመነጭ ምርጫን ያለማድረግ ፀረ-ዴሞክራሲ አመለካከቱን የሚተገብርበት ሽፋን አጥቶ ተጠቦ በነበረበት ወቅት እንደ አጋጥሚ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ (ዊንድ ፎል) ሲመጣለት የሽክና ከበሮን ሲደልቅ የቆየ ቢሆንም የትግራይ ህዝብ ምርጫ በሀገርም ይሁን በአለም ደረጃ ከባድ ተጽእኖ ስለፈጠረ እና የጠላት አጠቃላይ ማሽቆልቆል መሬት ስለረገጠ የግዱን ተገዶ ምርጫውን አካሂዳለሁ ብሏል፡፡ ጠላትን ከባድ ሽንፈትን እና ሀፍረትን ያላበሰ ፍፃሜ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚሁ የምርጫ አጀንዳ በኩል ትንሽም ፋታ ለማግኘት እና ህልውናውን ለአፍታም ማቆያ እንዲሆን በማሰብ ተጠቃሚ ለመሆን ስራውን ጀምሯል፡፡ የውድድሩ ሁኔታ በአጠቃላይ በፀረ-ዴሞክራሲ አጥር በማጠር የሚታሰረውን አስሮ፣ የሚገዛውን ገዝቶ እና አስፈራርቶ እንዲሁም ከከፊሉም እየተሸማገለ ከሰነበተ ሙሉ በሙሉ ምርጫውን በማጭበርበር የሚያስቀጥለውን ስልጣን ለመያዝ ግራ እና ቀኝ እያለ ነው፡፡

በሀሰት አጀንዳ የጠላት ምርጫ ማንኛውም አይነት ፋታ እንዳያገኝ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ጠላትን ለመጣል ወይም ለማሰናበት አንድ እርምጃ የሚያራምድ ቁልፍ መሪ ቃል ሆኖ ስልጣን የለህም ውረድ ከሚለው መሪ ቃል ጋር ተቀናጅቶ የፖለቲካዊ ስራችን ማዕከል እንዲሆን ማድረግ፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ሀይል ወንጀለኛ እና በሀገር ክህደት (ትሪሰን) ተጠያቂ መሆኑን በሀገር ውስጥ እየፈፀመው የሚገኝ ፋሺስታዊ ጭፍጨፋ (ኦሮሞ፣ ደቡብ፣ ሶማሌ እና ቅማንት ወዘተ…)

በንፁህን ዜጎች ደም የተነከረ ወንጀለኛ መሆኑን፣ ከኢሳያስ ቡድን እና ሌሎች ሀገሮች ጋር ሀገርን የመሸጥ ግንባር ፈጥሮ የዚህች ሀገር ጥቅምን እና ሉአላዊነትን ያጠፋ ካሀዲ፣ ምርጫውን የሚያካሂድ እና የሚመራ ሳይሆን በሀገር ክህደት እና ዜጎችን በመጨፍጨፍ ወንጀል ህግ ፊት መቅረብ ያለበት፣ በህግ መጠየቅ የሚገባው ቡድን መሆኑን፤ ይህ ፍፁም ፀረ-ዲሞክራሲ እና ከሀዲ ቡድን ከእነ ተቋማቱ ምርጫውን መምራት እና ማካሄድ አይችሉም፤ የአብይ ካቡኔ፣ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ፌደሬሽን ምክር ቤት፣ የምርጫ ቦርድ ፀረ ህገ መንግስት ናቸው፡፡ ስለሆነም ምርጫውን የሚመሩ ተቋማትም አዳዲስ እና አዲስ ማስተካከያ ሲካሄድ ብቻ መሆኑን፣ ከዚህም አልፎ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ እና ወንጀለኛ የአብይ ቡድን ለህግ እንዲቀርቡ - ሰፊ የድርድር ቅድመ ሁኔታ እየሆነ እንዲቀርብ በማድረግ የምርጫ አጀንዳን የጠላትን ማጥፊያ/ ማሰናበቻ ማድረግ፡፡

### 2.3.6. የጊዜያዊ መንግስት ምስረታ እና ዘላቂ ጉዞ መሰረት መጣል

I. መነሻ፡- የጠላት (የአብይ ቡድን) መሰናበትን ወይም መውደቅን ተከትሎ ወዴት እና እንዴት እንደሚሄድ በከፍተኛ ብቃት እና ትንቃቄ በመመለስ ከወዲሁ (ተጀምሮም ስለቆየ) የኢትዮጵያ ህዝቦች - ሀይሎችን ማሰባሰብ በአጠቃላይ የትግራይ ህዝብ ደግሞ በተለይ በድርጅት ውስጥ፣ መንግስት እና ህዝብ ሙሉ መግባባት ተፈጥሮ ግልጽ በሆነ አቅጣጫ ላይ ሆነን ከወዲሁ የዘላቂ ዋስትናችንን መሰረት በሚያረጋጥ ባቡር ላይ ተሳፍረን መንዝ መጀመር አለብን፡፡ ከጠላት ውድቀት በኋላ ምን አይነት ተልዕኮዎች ወይም ግቦችን የሚሸከም መንግስት ይኑር ተብሎ በድጋሚ /መልስህ/ ለተግባራዊነቱ መረባረብ በጠላት መውደቅ ዋዜማ ላይ ተኩኖ ውግንና መያዝ እና በዚህ መሰረት ሰፊ ዘመቻ መጀመር የሚገባ ነው፡፡

II. ምን አይነት የሽግግር መርህ / አሰራር ?

በሀገራችን አሁን በተፈጠረው ቀውስ እና ከባድ ጥርጣሬ በአንድ በኩል፣ የተደራጁ የፖለቲካ ሰልፎች /ሰልፈኞች ግንባር ወይም ጥምረት/ በሀገር ደረጃ ያለመኖር እና የተበታተነ መሆን፣ እነዚህን ተከትሎ ተጠቃሚ የውጪ ዜጎች ሂደቱን ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል እያደረጉት የሚገኘውን መረባረብ እና ጣልቃ ገብነት በሌላ መልኩ፣ እንዲህ አይነቱ መዝረክረክ የጅምላ እና ትርቻሮ እንካ - በእንካ ሰፊ እድል የሚከፍት ፖለቲካዊ ገበያ ገኘ በሆነበት ወቅት የሽግግሩ አሰራር / መርህ ወይም የጊዜያዊ መንግስት መቋቋም በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ብቃት መታየት እንደሚገባው ያስገነዝበናል፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ የጊዜያዊ መንግስት አሰራር መርህ ወይም መቋቋም የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆኑትን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በሚጠቅም የሚቋቋሙበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ ይህንን ጊዜያዊ መንግስት ለማቋቋም ቁልፍ መነሻው

ይህንን ማድረግ እና በዚሁ መተግበር ለጊዜው ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር እንዴት እንቀጥል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አንድ ሁለት እርምጃ ወደ ፊት የሚወስደን ይሆናል፡፡

በዚህ መሰረት የጊዜያዊ መንግስት መቋቋም ከእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ በእኩል የሚወከሉ አብላጫ ድምጽ የሚይዝ ቁጥራቸው እንደተጠበቀ ሁሉም በዚህች ሀገር የሚገኙ ፖለቲካዊ ስልፎች/ አሰላለፎች፣ ትርጉም ያለው የአባላት መሰረት ያላቸው የሰፊው ህዝብ ማህበራት እና ሲቪክ ማህበራት የተወከሉበት ሀገራዊ ሸንጎ፣ ምርጫ በማያደርጉ ክልሎችም ክልላዊ ሸንጎ ይመሰረታል/ ይቋቋማል፡፡ የሸንጎ አባላት ብዛት የፈለገ ቁጥር ቢኖረው ይገባሉ በተባሉት አካላት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ይህ ሸንጎ የተወካዮች ሸንጎን ተመሳሳይ አላማ/ ግብ የሚያራምድ እንደ ቋሚ አካል የሚሆን ነው፡፡ ይህ ሸንጎ የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር (ከፓርቲ ውጪ የሆነ) ከስራ ቡድኖች ሸንጎ (ወርኪንግ ግሩፕስ) ወይም ሌላ አማራጭ ካለም ጥቆማ ቀርቦ በመግባባት ወይም በአብላጫ ድምጽ ከተሰየመ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ - የስራ ባልደረባ ካቢኔ አባላት የፓርቲ አባላት ያልሆኑትን አቅርቦ በሸንጎው ያፀድቃል፡፡ ባለአደራ መንግስት ይቋቋማል፡፡ በተቀመጠለት አላማ / እቅድ/ ግብ መሰረት ሀገርን ይመራል፡፡ በክልሎችም ተመሳሳይ፡፡ ሀገር ወደ አዲስ መረጋጋት እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ትመለሳለች - የስልታዊ መድረካችን ትግል ድል ያደርጋል፡፡ አዲስ ጉዞ ይጀመራል፡፡

III. የሸንጎ እና ባለ አደራ መንግስት አላማ / እቅድ/ ግብ እና ተልዕኮ፡- የባለ አደራ መንግስት በሸንጎ ከተሾመ በኋላ የሀገር እለታዊ አስተዳዳሪነቱን ያካሂዳል፡፡ የሚያወጣው አዲስ ህግ የለም፣ በቆየው ህግ እና ህገ-መንግስት ያስተዳድራል፣ አዲስ ምጣኔ ሀብታዊም ሆነ ማህበራዊ ፖሊሲ አያወጣም፣ የሚያቋቁመው ወይም የሚያፈርሰው ተቋም (በልዩ የሚወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ) አይኖርም፣ የዜጎች ሰላም እና ደህንነት መከበር የመሳሰሉ ግቦች /አላማዎች የሚኖሩት ይሆናል፡፡ ሸንጎውን በሚመለከት ሶስት  መሰረታዊ ግቦች / ተግባራት ይኖሩታል፡፡ ሸንጎው በተለያዩ የስራ ቡድኖች ተከፋፍሎ የሚሰራ ዋና አቅሞችን እየፈጠረ የሚራመድ ይሆናል፡፡ የስራ ተግባራቱ/ ግቦቹ ከቆይታ በኋላ በዝርዝር የሚታይ ሆኖ የመጀመሪያው ተግባሩ የባለ አደራ መንግስት ማቋቋም እና በቀጣይም ዘገባዎችን እና በጀቱን መከታተል ይሆናል፡፡ የሸንጎው ሁለተኛው እና ትልቁ ተግባር ግን ይህች ሀገር እንዴት ትቀጥል፣ ስር የሰደደው ችግራችንን እንዴት እንፍታ? ለ132 ዓመታት ያህል በጦርነት እና ተቃርኖ ውስጥ ነን፣ አሁን ብሄር ብሄረሰቦቹ እንዴት እንቀጥል? የሚል አጀንዳ ዝርዝሩ በኋላ ላይ ይቀርባል፡፡ የዚህች ሀገር መሰረታዊ ማስተካከያ የሚያመጣ ሁሉም አማራጮች ቀርበው በሸንጎ እና መላው ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ውስጥ መጠነ ሰፊ እና ጥልቅ ውይይቶች እንዲካሄዱባቸው ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

መግባባት በተደረሰባቸው ጉዳዮች መሰረት ሀገሪቱን እንደ አዲስ በሚፈጥራት እንዲስተካከል የህገ-መንግስት ኮሚሽን ያቋቁማል፣ መጨረሻ ላይም የህገ-መንግስት አጽዳቂ ጉባኤ ተቋቁሞ የዚህች ሀገር የብዝሀነት አስተዳደር ስርዓት ችግርን ከመሰረቱ የሚፈታ ህገ-መንግስት ይፀድቃል። ከዚሁ ህገ-መንግስት የማጽደቅ ሂደት ጋር የሚጠበቅ ክልሎችን እንደ ሀገር ሙሉ ሉአላዊ ስልጣን አጎናጽፎ የተወሰኑ የጋራ ስምምነት የሚደረግባቸውን ጉዳዮች በጋራ የሚመራ የቃል ኪዳን የፌደራል መንግስት (ሉዝ አሬንጅመንት) በጣም ልል ስለሆነ እያንዳንዱ ሉአላዊ ስቴት /መንግስት/ ክልላዊ አደረጃጀቱን በሪፈረንደም ይወስናል። ሶስተኛው የሽንጎው ተግባር እነዚህን ተግባራት ስኬታማ በሆነ መንገድ አሳልጦ ምርጫ ያልተካሄደበትን ሀገራዊ እና ክልላዊ ምርጫዎችን አስፈጽሞ ያጠቃልላል። እነዚህ ተግባራት ጠንካራ ሀገራዊ መሪ / አውራ ፓርቲ በሌለበት ከባድ ነው። የትምክህት እና ጠባብ ሀይሎች በተለይ የትምክህት ሀይል ይህንን ጉዞ ለማደናቀፍ የሞት ሽረተቱን ይሰራል፤ ከውጪም ብዙ ፈተናዎች ይከሰታሉ/ ይመጣሉ። ነገር ግን የራስን እድል በራስ መወሰን እና ማስተዳደር ፍትህ/ ርትዕ ያሸንፋል። ሌላ አማራጭም የለም። ይህ ሂደት አጠር ቢል በ2 አመት ካልሆነ ደግሞ 3 አመት ያህል ሊፈጅ ይችላል።

### 2.3.7. **ከኋላችንን የሚወጋንንም እንጠንቀቅ**

I. በአጠቃላይ የኤርትራ ጉዳይ በተለይ ደግሞ የኢሳያስ ቡድን በቀጥታ ከምከታችን ጋር እና ከፍላጎታችን ባሻገር የሚዛመድ ነው። የዚህ ቡድን ፖለቲካዊ፣ ጸጥታዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ወዘተ… እንቅስቃሴዎቹ እኛ ላይ በተዘዋዋሪ ሳይሆን ቀጥተኛ እና ከባድ ተጽእኖ ይኖረዋል። እጅግ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ የኢሳያስ ቡድን እና የአብይ ቡድን ተቀናጅተው በትግራይ ህዝብ ህ.ወ.ሓ.ት ጉዳይ ስር የሰደደ ጥላቻ ይዞ ዳግም እንዳናንሰራራ ሊያጠፉን የሚያልሙ እና እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ መሆን ነው። ይህም የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም። ሁለቱም ስልጣናቸውን ማስቀጠል እና ብዛታቸውን ማስፋት ካለባቸው ይህ ድርጅት እና ህዝብ መጥፋት አለባቸው ብለው አቅደው እና ተመካክረው የጋራ እቅድ አውጥተው ነው በእኛ ተቃራኒ ቆመው እየገጠሙን የሚገኙት። ስለሆነም ይህ ስለታም የጥፋት ጫፍ ከአሀዳዊው እና ፍፁም ፀረ-ዲሞክራሲ ቡድን ብቻ ሳይሆን ከኢሳያስ ቡድንም ጭምር እንጂ። አንድ አንድ ጊዜ ለብቻው አንድ አንዴ ደግሞ ከደመኞቻችን / ጠላቶቻችን ጋር ተሻርኮ ፍላጎቱን እና አመለካከቱን የሚተገብርበት ክህሎት/ ችሎታ አጥቶ እንጂ እኛን ከዛሬ ነገ ለማጥፋት እንደተመኘ - እንደፎከረ ነው። በመሆኑም ሁለቱም ሀይሎች በተጨባጭ ህልውናችንን የሚፈታተኑ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ በመሆን ነው እየሰሩ የሚገኙት። የአብይ ቡድን ወድቆ የኢሳያስ ቡድን መዝለቅ/

መቀጠል ድላችንን ከንቱ የሚያደርግ በተለመደው አዙሪት ከመዳከርም አንወጣም፡፡ ስለሆነም የኢሳያስ ቡድን እድል እና እጣ እንዲሁ ከአብይ ቡድን እጣ ጋር አብሮ እንዲጓዝ የኢሳያስን ቡድን የሚያዳክም፣ የሚያፈራርስ ፈጣን፣ ተጨባጭ እና መጠነ ሰፊ እቅድ ይዘን እንስራ፡፡ አካሄዳችንን እንቀይር፡፡

II. የኢሳያስን ቡድን ከሞላ ጎደል ለማዳከም እና ለማፈራረስ የሚያስችል አሁንም ልክ እንደ ሀገራችን በሳል ነባራዊ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህ ቡድን ሙሉ በሙሉ ከኤርትራ ህዝብ ተነጥሏል ሊባል ይችላል፡፡ ውስህ በሰላም ግባ የሚለው ህዝብ የለም፤ ተስፋ ቆርጠውበታል፡፡ በዚሁ ገዢ መደብ ውስጥም ግዙፍ ስንጥቃት ነው ያለው፡፡ በሰራዊት ውስጥም ከባታሊዮን አመራር በታች የሚገኙ የሰራዊቱ መኮንኖች እና ተራው አ.ጋር/ እግረኛ እና ሰፊው ህዝብ በፀረ-ስርዓቱ አንድ አይነት አቋም አላቸው፡፡ ከብርጌድ አመራር በላይ የሚገኙትን በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች፣ እጥረቶች/ ድክመቶች እና በስለላ ጭምር እያስታመመ ለመያዝ እየሞከረ እንደሆነ ነው የሚገለፀው፡፡ የኤርትራ ህዝብ ወታደር ሆኖ መኖር አንገፍግፎት አህዱዎቹን ከጠቅላላ መጠናቸው ሲሶ በማይበልጥ የሰው ሃይል ነው እየተጓዙ የሚገኙት፡፡ ይህንን ትልቅ ጉድለቱን ቋሚ/ነባር ሰራዊትን በማደራጀት ነው ለመሸፈን እየሞከረ የሚገኘው፡፡

እንደ አቅሙ ከ65 ዓመት በታች እድሜ ያላቸውን የመንግስት ሰራተኞችን ጨምሮ የቋሚ/የነባር ሰራዊት አባል በማድረግ ነው ህልውናውን ለማሳየት እየሞከረ የሚገኘው፡፡ የኢሳያስ ቡድን የማቆያ ክር ሆኖ እያገለገለ የሚገኘው የሰራዊቱ ከፍተኛ አዛዦች፣ ሀገራዊ ደህንነት እና ስለላ እንዲሁም የሚከተለው አሰራር እና አደረጃጀት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሁሉም 65 አመት እና ከዚያ በታች እድሜ ያላቸው ቋሚ/ነባር ሰራዊት ብሎ በመስመር እና ጋንታ ውስጥ አስገብቶ - በሰራዊት ስም በንቁ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ/ ንቅናቄ እንዳይገባ አፍኖ ይዞታል፡፡ ከፍተኛ ጀነራሎችን እና የሀገር ደህንነት ስለላ አካላት ደግሞ በሙስና እና ጎጠኝነት እርስ በእርሳቸው እንዲጠባበቁ እና ኢሳያስን እንደ አዳኛቸው እንዲመለከቱት አድርጎ በፈጠረው ወጥመድ ነው እኩል በእኩል እያራመደው የሚገኘው፡፡ በዋናነት ደግሞ በሀገራችን የባሰውን የአመራር ክፍተት (ሁሉንም በራሴ የሚያስከትለውን ችግር/ሁኔታ) እንደ እድል ተጠቅሞ የኤርትራን ህዝብ በባርነት ቀንበር ስር አስገብቶ እኛን ለማጥፋት ሌት ተቀን እየባዘነ ይገኛል፡፡

III. ይህንን አጭር ጠቋሚ/ አመላካች ሁኔታን/ እውነታን መሰረት በማድረግ የኢሳያስን ቡድን ለማፈራረስ የሚያስችል እድል ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም ሁለት በጥብቅ የተያያዙ/ የተሳሰሩ የስራ እቅድ አቅጣጫዎችን ይዘን እንሰራበታለን፡፡ አንዱ በኤርትራ የውስጥ አቅሞች ላይ ተመርኩዘን ኢሳያስን የሚገረስስ ተጨባጭ እና የተደራጀ እገዛ፣ ሁለተኛው የኢሳያስ ቡድን የዚሁ ይፋዊ

ውረራ አካል ሆኖ በእኛ ላይ ጦርነት ካካሄደ ደግሞ በጦርነት የሚደመስስ ወታደራዊ ዝግጁነት እና ስትራቴጂን ይዘን ለመመከት መዘጋጀት፡፡ በኤርትራ የውስጥ አቅሞች ላይ ተመርኩዘን ማድረግ የሚገባን ተጨባጭ ድጋፍ በአንድ በኩል የጠላትን ድክመቶች ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያሸጋግር እና በሌላ በኩል ደግሞ የለውጥ ሀይሎች ተደራጅተው እንዳይነቃነቁ፣ እንዳይመክቱ ከባድ ክፍተት/ ጉድጓድ ሆኖ የሚገኘው የአመራር ችግር እንዲሁ ለመፍታት የሚያግዝ ወጥመዶችን የሚበጣጥስ እንዲሆን ማድረግ፡፡

ወጣም ወረደ ግን የኢሳያስን ቡድን ማፈራረስ ማዕከል ያደረገ ውሳኔን ይዘን ራሱን የቻለ ስትራቴጂ እና አቅም እንዲዘጋጅለት፣ ይህንን የሚመራ እና የሚያስተዳድር አደረጃጀት እንዲፈጠር፣ አካባቢውን እና ስራውን የሚያውቅ በቂ የሰው ሃይል እንዲመደብ፣ አቅማችን የፈቀደውን ያህል የፋይናንስ እና ማቴሪያል ከፍ ለማድረግ / ለመጨመር በሁሉም ረገድ በህዝብ፣ በድርጅቶች፣ በሰራዊት፣ ሚዲያ እና አክቲቪስቶች እንዲሁም በውስጥም ሆነ በውጪ (የይብቃ/ ይአክል/ ህዝባዊ ንቅናቄ) ወዘተ… አስተባብረን የኢሳያስን ቡድንንም እንገረስሳለን፡፡ ከፊት ከፊታችንም ከኋላችንም (ጀርባችንን) ነፃ እናወጣለን፣ ምከታችንን መጪው / የወደፊት ጊዜ ጉዞ ዋስትናው የተረጋገጠ እንዲሆን ሁኔታዎችን ማስተካከል፡፡ እንችላለን ጎበዝ ደል ንሳ መሪ ድርጅታችን ህ.ወ.ሓ.ት ምን ይሳነዋል !!

### 2.3.8. የመህል ሀገር ተጋሩ ደህንነት እና የሶስተኛ ወገን ግንኙነት አጠናክሮ መቀጠል

I. በመሀል ሀገር የሚኖር ትግራዋይ በሙሉ ጠላትን የመጣል/ የመገርሰስ ትግል እንደ አንድ አካል ደህንነቱን ማረጋገጥ ሆኖ ተጠናክሮ እንዲወጣ በበቂ ትኩረት መመራት አለበት፡፡ ይህንን ትግል እና ደህንነት የማረጋገጥ ጉዳይ የጠላትን ተጨባጭ እንቅስቃሴ እና ፈተና እና እድል እንዲሁም በመሀል ሀገር የሚኖሩ ተጋሩን ሁኔታዎች በደንብ ያገናዘበ ማለትም ከጠላት የሚመጣውን ጥቃት ለማስወገድ በሚያስችል መልኩ ጠላትን ለማዳከም ያሉትን እድሎች እስከ እንጥፍጣፊ የሚጠቀሙ እና የትግሉን አግባብ የሚከተል መሆን ስላለበት ነው፡፡ ትልቁ ስጋት ጠላት በመሀል ሀገር የሚኖሩ ተጋሩ ላይ በተለያዩ አግባቦች ሰፋፊ ጥቃቶችን እየፈፀመባቸው ነው፡፡ ስለሆነም ለጥቃት የማያጋልጥ አቅጣጫን ለይተን በመያዝ በጥብቅ የምንሰራበትን በሌላ መልኩ ደግሞ የህዝባችን ፀረ-ጠላት ትግል ቆራጥነት እና ወኔ ተጠናክሮ እና ጎልብቶ እየወጣ ነው፡፡ ይህንንም የሚጠብቅ መሆን አለበት፡፡ በዚህ መሰረት ይህንን መተግበር የምንችልበትን የትግል አግባብ ስብጥር የህቡዕ እና ግልጽ አካሄድ በሰፊው ተጠቅመን ህዝባችንን የትግል እና ደህንነት አካል እንዲሆን የሚያደርግ አደረጃጀቶች፣ ተልዕኮዎች እና አሰራሮችን በሚያመች መልኩ አድሰን

(አሳድሰን) እንረባረባለን፡፡ በውጪ የሚኖሩ ተጋሩ ባለፈው ባስቀመጥነው የስራ እቅድ አቅጣጫ እና አሁን በተጀመረው ሂደት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መስራት ነው፡፡

II. በሶስተኛ ወገን የግንኙነት መስክ በኩል እየሰሩ የቆዩ የተሻለ እውቀት እና በሳል ተሞክሮ ያላቸው አመራሮቻችንን በበይነ መንግስታት ጽ/ቤት እየተመራ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ አሁን ያስቀመጥነው የምንገኘውን መሰረታዊ ተግባራትን እና ተልዕኮዎችን ለመፈፀም በሚያግዝ/ በሚደግፍ ቅኝት ተጣጥሞ/ ተስተካክሎ ከውጪ ማግኘት የሚገባን የፍትሐዊ ጥያቄያችን እና አካሄዳችን ደጋፊ በጠላቶች ላይ ተጽእኖዎቹን የሚፈጥር መሰባሰብ፣ ጥያቄያችን እና አካሄዳችን ግልጽ ያልሆነላቸውን ማብራራት፣ የጠነከረ ተቃውሞ ያላቸውንም ወደ መግባባት እንዲመጡ ማድረግ ወዘተ… ስራዎቹን በተጠናከረ ትኩረት መቀጠል፡፡ እስካሁን ድረስ የተካሄዱ የግንኙነት ስራዎች እና ጉድለቶቻቸው በዝርዝር ተገምግመው በዚሁ አዲስ አቅጣጫ ዝርዝር የስራ እቅድ ማውጣት፡፡

III. የመጀመሪያ እና ከፍተኛ ትኩረታችን ጎረቤት ሀገሮች ወደ ጥሩ መግባባት እና ግንኙነት፣ ጥሩ የሚባል መደጋገፍ እርከን እንዲሻገር መሆን አለበት፡፡ የኤርትራን ጉዳይ የተቀመጠውን ወስደን ለምክታውም ሆነ ለዘላቂ ጉዞው በሚያግዝ መልኩ በሱዳን እና ጅቡቲ (በሰፊው ታጁራ) በተለየ/ በልዩ አደረጃጀት፣ የሰው ሃይል ወደ ተጨባጭ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፀጥታዊ እና ፖለቲካዊ መደጋገፍ እንዲኖር፤ ከዚህ ጋር በመካከለኛ ምስራቅ ያሉ ሀገራት ከዚህ ጀርባ ያሉትን ምዕራብ እና ሌሎች ትልልቅ ሀገሮች ላይ ያለውን አሰላለፍ በመገንዘብ መፈጠር የሚገባውን ደረጃ/ ደረጃዎች ማስተሳሰር / ማቆራኘት፣ መደጋገፍ እና ነጥቦቹን ለይቶ መስራት፡፡ የአለማችን ትልልቅ ሀገራትም እንደየ ባህሪያቸው እና ትስስራቸው ለተመሳሳይ አላማ መስራት፡፡ ከቻይና ጋር በተሻለ መልኩ የሚያገናኘውን እና መሄድ የሚችልበትን ርቀት ልክ መሆን፣ ከአሜሪካ ፕላን ‹ኤ› እና ፕላን ‹ቢ› በዴሞክራቶች እና ሪፐብሊካኖች ከምርጫው ጋር አዛምደን (የጆ. ባይደን የመመረጥ እድል የሰፋ ይመስላል)፤ የአውሮፓ ህብረት፣ እንግሊዝን እና ራሺያን ጨምረን አላማችንን እና አመለካከታችንን፣ የእነርሱን ጥቅማ ጥቅሞችን የሚጎዳ እና ሀገርን እያፈረሰ ያለው ቡድን ለመግራት የሚያግዝ መግባባትን/ ውይይቶችን መፍጠር፡፡

## 2.4. **የትግራይን ህዝብ ዘላቂ ጥቅም የሚያረጋግጥ የአዲስ ምዕራፍ ግንባታ !**

### 2.4.1. **የኢትዮጵያ እና የትግራይ ህዝብ ግዛት (ኢምፓየር) ማቋቋም !**

I. ጠላት ወድቆ የሚያሸጋግር ጊዜያዊ መንግስት ተቋቁሞ ህገ መንግስታዊ ስርዓት ተመልሶ፣ የህገ-መንግስታዊ ስርዓት ቆመን በአንድ በኩል ሀገርን ማረጋጋት በሌላ መልኩ ደግሞ በመጪው

የሀገራችን እድል በጣም ሰፋፊ እና ጥልቀት ያላቸው ውይይቶችን እና ክርክሮችን፣ ውሳኔዎች (እስከ ሪፈረንደም ድረስ የሚሄዱ ውሳኔዎች) ተደርጎ የዚህች ሀገር የተረጋገጠ አዲስ ማስተካከያ መሰረተ ድንጋይ የሚነጠፍበት ሆኖ እንዲወጣ መታገል እንደሚገባን አስምረን - አስቀምጠናል። በመሆኑም እኛም ሆንን ሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች በጊዜያዊ መንግስት ተልዕኮ ማእቀፍ ብቻ ታጥረን ነገሮችን ማየት የለብንም። አሁን ካለው ሁኔታ ባሻገር ተመልክተን በራሱ በችግሩ ላይ እሳት ሆነን እሳቱን ለዘለቄታው የሚያስወግድ መፍትሄ በመያዝ የረጅም ጊዜ ጉዳያችን/ ግባችን የተረጋገጠ ማድረግ አለብን።

አሁን ላይ ወደ ተመሳሳይ አደጋ የምንገባበትን ሁኔታ በፍፁም መፍቀድ የለብንም። ያለፈው ጉዞዋችን ሙሉ በሙሉ አንጠፍጥፈን ልንማርበት እና እንዲህ ያለ ሌላ አጋጣሚ ለአንዴ እና ለመጨረሻ እንደማይደገም ማድረግን አልመን ልንሰራበት ይገባናል። ካልሆነ ግን በህልውናችን እና ማንነታችን መጫወት ነው የሚሆነው። አንድ አንድ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን እንደሚሉት አንድ የጥፋት ሁኔታ በመጀመሪያ ካጋጠ የሚያሳዝን / ትራጀዲ/ ተግባር ሲሆን ለሁለተኛ ጊዜ ካጋጠመ ግን ቀልድ /ፊርስ/ ነው የሚሆነው ይላሉ። በአሁኑ ትውልድ ላይ ቀልድ፣ ስንፍና እና ያለመምራት ምክንያት የትግራይ ህዝብ በአሁኑ ወቅት ወደ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ጥፋት ከገባ የትውልድ ታሪካዊ ጥፋት ነው የሚሆነው። ከዚህ ለመውጣት የትግራይ ህዝብ አሁንስ ወዴት? እያለ ነው። መመለስ አለብን። ለዚህም ሲባል መለስ ብለን የኢትዮጵያ እና የትግራይ ህዝብ ግዛት (ኢምፓየር) መመስረትን እንመልከት።

II. የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ግዛት በማጠናቀቅ በ19ኛው ክፍለ ዘመን (በ1881ዓ.ም) ከሰሜን ሸዋ የተነሳው ንጉስ አፄ ሚኒሊክ በአሁኑኗ ኢትዮጵያ ደቡባዊ ፣ ምዕራባዊ እና ምስራቃዊ ክፍል ነበሩ ነፃ እና ከፊል ነፀ የሆኑ መንግስታትን እና አስተዳዳሪዎችን በሀይል ጨፍልቆ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር አስገብቷል። አፄ ሚኒሊክ በኢትዮጵያ ደቡባዊ ክፍል ያካሄደው ግዛትን የማስፋፋት እንቅስቃሴ /ንቅናቄ/ ግዙፍ ምጣኔ ሀብታዊ ምንጭ እና የሰው ሀይል አቅም በማፍራት የሰሜን ተቀናቃኝ መሳፍንቶቹን በሀይል ለማስገበር ሙሉ እድል ስለፈጠረለት የሰሜን ተፎካካሪ/ ተቀናቃኝ በተለይ ትግራይ እምቡር እንቡር ቢሉም የማታ የማታ የአፄ ሚኒሊክን የበላይነት እና ግዛት አሜን ብለው ተቀበሉ። ከዚህ ወቅት በኋላ ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጫፍ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ጫፍ በአፄ ሚኒሊክ ግዛት ስር ገብታ የኢትዮጵያ ግዛት/ ኢምፓየር ተመሰረተ።

III. በመሳሪያ ሀይል (ነፍጥ) አንግቦ የአፄ ሚኒሊክ ነፍጥ ያነገበው ሀይል ወታደራዊ የበላይነቱ ቋሚነት ባለው የፖለቲካ - ምጣኔ ሀብታዊ የበላይነት ተክቶታል። ነፍጠኛው ሀይል

የየአካባቢውን ለም መሬት እየነጠቀ ባለቤት ሆነ፡፡ ይህ ሰፊ እና ለም መሬት ራሱ አርሶ ሊጠቀምበት ስለማይችል ህዝቡ መሬቱ ተነጥቆ ሲያበቃ ተመልሶ ነፍጠኛውን በሲሶ ገባርነት / አርሶ አደርነት  እንዲያገለግል ተደረገ፡፡ ለመገመት የሚያዳግት ጭቆና፣ ባርነት እና ግፍ ቀጠለ፡፡ በኢትዮጵያ ሰሜን ክፍልም ቢሆን የነፍጠኛው ስርዓት ባይመሰረትም እንኳን በትግራይ፣ አማራ እና ሌሎች የነበሩ ገዢ መሳፍንት፣ የአፄ ሚኒሊክን እና ነፍጠኞችን ፖለቲካዊ ልዕልና/ የፖለቲካ የበላይነት ተቀብለው የየአካባቢያቸውን ገባር / አርሶ አደር በባሰ ሁኔታ የሚበዘብዝበትን፣ ሙሉ በሙሉ ወደ ባርነት እና ተገዢነት የገባበትን የባሰ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

IV. በሀይል የተመሰረተው የኢትዮጵያ ግዛት /ኢምፓየር/ የተማከለ ግዛትን ለማጠናከር የሚያግዝ በአፄ ሚኒሊክ ዘመን ዳዴ ማለት የጀመረውን ዘመናዊ ቢሮ ክራሲ እና አስተዳደር የጀመረበትን በአፄ ሀይለስላሴ ከጣሊያን ወረራ ጋር የተጠናከረ ካፒታል የውጪ ጣልቃ ገብነት ታክሎበት የተደላደለ ግዛታዊ ጭቆና እና ብዝበዛ ፍጹም ፀረ ዲሞክራሲያዊ አፈና እና መሰረት ላይ ተገንብቶ ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ግዛት /ኢምፓየር/ ከ100ዓመት በላይ ጥልቅ/ ሰፊ የመደብ ብዝበዛ - ጨቋኝ ፖለቲካዊ ስልጣን፣ የዴሞክራሲያዊ እና ሰብዓዊ መብቶች አፈና መለያው የሆነ ግዛታዊ ማዕከልነት በመሆን ስር የሰደደ ብሔራዊ ጠቅላይነት / አፈና ልዩ ክረት/ መካረር ያለበት ብሔራዊ ግጭት እና ጭቆና (75% የህዝብ) በልኳ ሲኦል የተሰፋላት የኢትዮጵያ ግዛት እስከ 1983ዓ.ም ቀጠለ (ለ102 ዓመታት)፡፡

V. ከ1983 ዓ.ም መጨረሻ የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተበት እና የመራው ትግል ድል ነስቶ አሀዳዊ አገዛዝ ፈርሶ እኩልነት ላይ የተመሰረተ ህገ-መንግስታዊ፣ ህብረ-ብሔራዊ ፌደራሊዝም መሰረት ያደረገ የሽግግር አዲስ ምዕራፍ ተጀምሮ - የእኩልነታዊ የአንድነት ጉዞ ተበሰረ፤ አስገራሚ ፈጣን ልማት፣ ሰላም እና ዲሞክራሲ ለ27 አመታት ያህል ተጉዞ ረጅም ርቀት ሳይጓዝ ከሩብ ክፍለ ዘመን እድሜ በኂላ ከ2010ዓ.ም ጀምሮ አሁን በአዳዲስ የብሄራዊ ጠቅላይ ሀይሎች ተተክቶ ወደ ነበረበት አሀዳዊ፣ ፍፁም ፀረ-ዲሞክራሲ እና አምባገነን ስርዓት ተመልሶ እነሆ ይህች ሀገር የመበታተን የመጨረሻው ጫፍ ላይ ትገኛለች፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በ132 አመታት ውስጥ የብዝሀነት ታሪክ መካከል በኢህአዴግ የተጀመረው የአዲስ ምዕራፍ ግንባታ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህች ሀገር ድምር ጉዞዋ ግን ህብረ ብሔራዊ ሀገረ መንግስት ግንባታ ወይም ብሔረ-መንግስት ግንባታ ሳታካሂድ በማያቋርጥ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ እና ስነ ልቦናዊ ግጭት እና ጦርነት ውስጥ ተዘፍቃ ቆይታ አሁንም እዚያው ላይ ነች፡፡ ምስረታዋ በጦርነት እና ወረራ ቀጣይ ሂደቱም በጦርነት እና የመጠቅለል ግጭት የምትገለጽ ሀገር፡፡

VI. የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ የታሪክ እና ስልጣኔ ተጅም መዋዕል ካላቸው የአለም ህዝቦች አንዱ ሆኖ በዚሁ ረጅም የታሪክ መዋዕሉ ውድቀትን፣ ትንሳኤን፣ ረሀብ እና ጥጋብ፣ ማጣትን እና ማግኘትን፣ የብዙ ወረራሮች እና ምክታዎች ዋልታ የሆነ ህዝብ ከዚህም የሚመነጭ በርካታ ፍላጎቶቹን እያሳደገ ግን የበዛ ውስብስብነት ውስጥ የገባ ረጅም እና አስደናቂ ታሪክ እና አስተሳሰብ የሀገር ቤዛ ሆኖ ለአለም ያበረከተ ሆኖ ሳለ እስከዛሬ ድረስ ፍላጎቶቹን ጫፍ ያላደረሰ ህዝብ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መከራዎችን ያሳለፈ ለዘመናት በራሱ መሳፍንት ፍዳውን ያየ እና ከኢትዮጵያ ግዛት ምስረታ በኂላም የመደብ ጭቆና እና ብዝበዛ፣ ብሔራዊ ጠቅላይነት ጫፍ ወጥቶ ከሸዋ አገዛዝ በተሻረኩ መሳፍንት፣ ሽፍቶች መሬቱን፣ ጥሪቱን፣ ንብረቱን፣ ጉልበቱን በዝብዘው ጥቅል ኂላ ቀርነት እና ድንቁርና ረግረግ ውስጥ አስቀርተውታል፡፡ በብሄራዊ ማንነቱ ተዋርዶ እንደ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዜጋ ተቆጥሮ በትግራዋይነቱ እየታደነ እንዲገደል፣ እንዲታሰር እና እንዲበሰብስ ተደርጎ በባሰ የባርነት ቀንበር ስር ገባ፡፡

VII. ጭቆናን እና ባርነትን አልቀበልም ወግድ ብሎ የትግራይ ህዝብ መሳሪያ አንግቦ ለ17 አመታት (ወይኖ) እርሱን ከመሰሉ ጭቁኖች ጋር እንብኝ አልገዛም ብሎ ተባብሮ ከ100 አመታት በላይ የቆየውን የመደብ ጭቆና እና ብዝበዛ ፣ ብሔራዊ ተቅላይነት/ አሀዳዊነት ሰንሰለት በጣጥሶ የህብረ-ብሄራዊ ፌደራላዊ ሀገረ መንግስት ግንባታ መሰረት የሆነ ህገ መንግስት አብስሮ ግንባታውም ተጀምሮ በሚጓዝበት መንገድ በውስጣዊ ውድቀት እና መሽርሽር ተሸንፎ/ ድል ተነስቶ የነበረው አሀዳዊው እና ጠቅላይ ሀይል መቃብር ፈንቅሎ ተደራጅቶ ወደ አዲስ ጥቃት ተሸጋግሮ ከአዲሱ የለውጥ ምዕራፍ በ27ኛው አመቱ ዳግም ስልጣን ጨብጧል፡፡ የኢትዮጵያ ግዛት /ኢምፓየር/ ቀጥሎ እንደ አዲስ ሁሉም የእኩልነት ሀይሎች በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ መልሶ እጅግ በጣም ከባድ የህልውና አደጋ (ኤግዚስቴንሻል ስሪት) ስር ወድቆ ይገኛል፡፡

VIII. አሁን የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ ግዛት ምስረታ ውስጥ ታሪኩ የከፋው / የባሰው አደጋ አጋጥሞታል፡፡ አሁን ላይ የከፋበት/የባሰበት ምክንያት አለው፡፡ የትግራይ ህዝብ አሁን ዳግም የተመለሰውን አሀዳዊ ጠቅላይ ሀይል ራሱ መርቶ የደመሰሰ ቁልፍ ሀይል ስለሆነ እና ይህንን ህዝብ ሳያንበረክኩ ወይም ዳግም እንዳያንሰራራ ካልተደረገ እንደ ትላንትናው ያደርጋል ስላሉ እነዚህ ሀይሎች ወደ ስልጣን ከመጡ በኂላም ሳይውል ሳያድር በንቃቱ ለይቶ በማወቅ መመከቱ እና ሌሎች ክልሎች እና ህዝቦች ለጊዜውም ቢሆን እየተደናገሩ ባሉበት የትግራይ ህዝብ ግን የራሱን እድል በራስ መወሰን እና ራስ ገዝ አስተዳደር መብትን ጠብቆ የክልሉን ሉአላዊነት ያላስነካ በመሆኑ፤ እነዚህን ፀጥ-ለጥ ሳያደርጉ ዛሬ ብታሸንፋቸውም ነገ አፈራቸውን አራግፌው - ተነስተው የሚያጠፊን ናቸው በሚል የእብድ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ፈሊጥ ህልማቸው ከምድረ

ገጽ ሊያጠፉን፣ ነገ ጠዋት እንዳንነሳ ሊያደርጉን ለዚህም ሲባል በእኛ ተቃራኒ የሚሰለፈውን ሁሉም ጠላት እንደ ኢሳያስ ቡድን እና ሌሎቹን አሳልፈው አስተባብረው እኛን ለመንቀል እየታገሉ ይገኛሉ፡፡ እናም የትግራይ ህዝብ ከታሪካዊ ትግሉ እና ወርቃማ ድሉ በኋላ ዳግም በወሳኝ የህልውና አደጋ ውስጥ የገባበት ወቅት ሆኗል፡፡

### 2.4.2. ከአለም እና ሀገራት ምን እንማር !

ችግራችንን እንዴት እንፍታ የሚል ጥያቄን የመመለስ ጉዳይ በመሰረቱ ከውስጣዊ ተጨባጭ ችግር እና ይህንን የተመረኮዘ ሳይንሳዊ መፍትሄ መሰረት መደረግ እንደሚገባ ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ግን ተዛማጅ ተግባራት እና ፍፃሜ እንዲሁም የታዩ መፍትሄዎች እና ውጤቶቻቸው አሁን ያጋጠመንን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ከሌላው አለም (ከአዎንታዊ እና አሉታዊ ጎኑ) ተሞክሮ መማር እና አጣጥሞ መውሰድ፣ መተግበር የላቀ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የመንግስት ምስረታ ታሪክ ከአፍሪካ ሀገራት ምስረታ ታሪክ ጋር በፍፁም አይገናኝም፡፡ የኢትዮጵያ የመንግስት ምስረታ ታሪክ ከአውሮፓ ግዛታዊ መንግስታት ምስረታ ጋር ነው የሚመሳሰለው፡፡ በአውሮፓ የነበሩ ብዙዎቹ የኦቶማን ቱርክ፣ ኦስትሪያ፣ ሀንጋሪ፣ ብሪቲሽ፣ ራሺያ፣ ጀርመን ወዘተ… ትልልቅ ኢምፓየሮች የነበረው እንቅስቃሴ ጋር የሚተሳሰር ነው፡፡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ የግዛት ማስፋፋት ለምሳሌ የኦቶማን ቱርክ ለ600 አመታት ያህል የቆየውም ይሁል ሌሎች አብዛኛዎቹ ተበታትነው ከፊሉ በከባድ ጦርነቶች ከፊሉ ደግሞ መጨረሻ ላይ በሰላም ብሄረ-መንግስት (ኔሽን ስቴት) ነው የመሰረቱት፡፡ የብሪቲሽ ኢምፓየር በተካሄደው ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ሽግግር የኢንደስትሪያል ህብረተሰብ በመፍጠር እና ተጨማሪ የአስተዳደር ነፃነት በመስጠት የሀገረ መንግስት ምስረታ ተካሂዷል፡፡ ቀሪው ሁሉም ሊባል የሚችለው ግን በተለይ በ1848 (እ.ኤ.አ) ገደማ ጀምሮ ቋንቋን መሰረት ያደረገ የብሄርተኝነት ንቅናቄዎች ተወልደው ብሔራዊ ነፃነታቸውን አውጀው በርካታ ብሔረ መንግስታት መስርተዋል፡፡ እንደ ታሪክ እ.ኤ.አ 1848 በአውሮፓ የተካሄዱ ኢምፓየሮች ወደ ብሔረ መንግስት የመበታተን ሂደት እና በእኛ በኩል በ1960ዎቹ የነበረው ፀረ-ብሄራዊ ጭቆና ንቅናቄ ተመሳሳይ ይዘት ነበረው፡፡ እኛ ጋር ግን የህብረ ብሄራዊ ሀገረ መንግስት ግንባታ ወይም ብሔረ መንግስት መስረታ አልተደረገም፣ አልተሳካም በአጠቃላይ ሰፋፊም ሆነ ጠባብ የግዛት ማዕከልነት በፀረ-ዲሞክራሲ ብቻ ብዝሀነት ጨፍልቆ በምንም ተዓምር ማስቀጠል እንደማይቻል በጥቅሉ የአለማችን የግዛቶችን ተሞክሮ ማየቱ ይበቃል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚህ ጉዳይ ተሞክሮ ያላቸው ሁለት ሀገሮችን መዝዘን ማየት የሚጠቅም ይሆናል፡፡ ብዝሀነትን ማስተናገድ አቅቷቸው ደም ባፋሰሰ ጦርነት ከፈራረሱት ሀገራት መካከል ዮጎዝላቪያን ማዕከል በማድረግ እግረ መንገድን በሰላም የተበታተነችውን ቼኮዝላቫኪያን ብዝሀነትን በአግባቡ አስተናግዳ በጋራ በህብረ-ብሄራዊ ፌደራሊዝም ከ150ዓመታት በላይ የቀጠለችው ስዊዘርላንድ እግረ መንገዳችንን የካናዳ - ኩቤክ በማየት የተሻለ ትምህርት መቅሰም ይቻላል፡፡

ዮጎዝላቪያ እና ቼኮዝላቫኪያ የተባሉ ሀገራት ስላቭ ከተባሉ አንድ የህዝቦች ጎሳ የሚመዘዙ በኦቶማን ቱርክ፣ ኦስትሪያ - ሀንጋሬ አፄያዊ አገዛዝ ስር ከባድ ጭቆና፣ አገዛዝ፣ ስቃይ እና መከራ ውስጥ የነበሩ የምስራቅ አውሮፓ ህዝቦች ናቸው፡፡ አንደኛው የአለም ጦርነት መጠናቀቅን ተከትሎ ዮጎዝላቪያ 6 ክልሎች - ደቡባዊ ስላቭ የተባሉ ህዝቦች፤ ቼኮዝላቫኪያ ደግሞ ምዕራባዊ ስላቭ የተባሉ (ቼክ እና ስሎቫኪያ የተሰኙ) ህዝቦችን ይዘው እ.ኤ.አ በ1918 እና 1919 ሆኖ አፈራረሳቸው ግን ዮጎዝላቪያ ደም ባፋሰሰ ጦርነት፣ ቼኮዝላቫኪያ ደግሞ በሰላማዊ ፍቺ ከምስረታቸው በ72ኛው አመት የፈረሱ ናቸው፡፡

ይጎዝ ላቪያን የመሰረቱ የደቡባዊ ስላብ ህዝቦች የተባሉ ሰርቢያ፣ ክሮሺያ፣ ስሎቫኪያ እና ቦስኒያ፣ ሜንተግሮል፣ ሜቅዶኒያ ናቸው፡፡ (በሂደት ኮሶድ እና ቮጅቮጅድያን የተባሉ ሁለት አስተዳደራዊ ክልሎች ተጨምረዋል) ሁለቱም ሀገራት የፈረሱትን የአፄያዊያን ግዛቶች (ኢምፓየር) ተቃውመው የመጡ ሲሆን በተለይ ዮጎዝላቪያ የአንድ ጎሳ ህዝብ ሆና ተበትና አቅም በማጣቷ ለባርነት እና አገዛዝ ተጋልጣለች በሚል ፀረ-ኦስትሪያ፣ ሀንጋሪ፣ ኦቶማን ቱርካዊያን በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ የተቃውሞ ንቅናቄዎችን እያቀጣጠሉ ቆይተው በሰርቢያው ንጉስ አመራር ይንን ህብረት ሲቃወም የነበረ ቢሆንም አብዛኞቹ ግን በአንድነት ላይ ስለተስማሙ ያ ህብረት በስምምነት መስርቷል፡፡ ዮጎዝላቪያን የመሰረቱ /ያቋቋሙ/ 6 ብሔር ብሄረሰቦች የነበሩ ቢሆንም በህዝብ ብዛት አና ተጽእኖ በመፍጠር የመወሰን አቅም የነበራቸው ግን ሰርቢያዊያን 40%፣ ክሮሺያዊያን 20%፣ ስሎቫዊያን 6% ቀሪዎቹ ሙስሊም ስሎቫኒያን ፣ ክርስቲያን ሜንቶግራዊያን እና መደቄዶኒያውያን በጋራ ለ75 አመታት ዘለቁ፡፡

የግዛታዊ አንድነት ጭቆናን እንከላከል የሚል መንፈስ የሰፈፈለበት / የጠቀለለበት የሚያስተሳስር ክር ነገር ግን እያንዳንዳቸው በተለይ ተጽእኖ አላቸው የሚባሉ 3ቱም ብሄሮች በውስጣቸው የየራሳቸው ፍላጎት እና መሻት ስለነበር ከውጥን ከምስረታው ጀምሮ የመጎርበጥ ምልክት ታዬ፡፡ በዮጎዝላቪያ ምስረታ ላይ ንግግር ያሰማው ንጉስ አሌክሳንደር የዮጎዝላቪያ አንድነት በሶስቱም (ሰርብ፣ ክርአት እና ስሎቫ) አንድ ብሄር በ3 ጎሳ የሚመደቡ የሚል ንግግሩ ከክሮሻዊያን

ፖለቲከኞች እና ምሁራን ተቃውሞ ገጥሞታል። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ክሮሺያዉዊያን ክህደት እንደተፈፀመባቸው ይሰማቸው ጀመር። ከሀገር ምስረታው ጀምሮ የሰርባዊያን እና ክሮሺያዊያን አለመጣጣም ጥንስስ ቂም ተቋጠረ እነዚህ ብሄሮች የየራሳቸው ቋንቋ፣ ማንነት፣ ባህል እና ታሪክ የነበራቸው በሐይማኖትም ክርስትና (ኦርቶዶክስ እና ካቶሊክ) ሙስሊም የሆኑ በስላቭ ስም የአንድ ጎሳ ህዝብ የደረሰባቸው ግዛታዊ ጭቆና እና ስቃይ ካልሆነ በስተቀር ይህ ነው የሚባል የጋራ ታሪክ ያልነበራቸው ናቸው።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ፍላጎታቸውን እና መሻታቸውን አስመልክቶ የነበረባቸው ልዩነት ነው። ሰርባዊያን ራሳቸውን የሚመለከቱበት መነጽር በ15ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የነበረንን ጠንካራ ሀገር እና ንጉስ በኦቶማን ቱርክ ተነጥቀናል ብሎ ያኔ የነበራቸውን እና የተነጠቁትን ዝና እና ታሪክ ወደ ቦታው የመመለስ ህልም በውስጣቸው ይዘው ራሳቸውን በዚህ አሳምነው በእነርሱ የምትመራ / የምትገዛ ዮጎዝላቪያን ለመገንባት የሚያስቡ ከዚህም በመነሳት ሰርባዊያን የተቀሩትን በተለይ ደግሞ ክሮሻዊያንን እና ቦስኒያዊያንን የዩጎዝላቪያ ፀረ አንድነት አድርገው ይስሏቸው ነበር። ሌሎቹ ብሄሮች በተለይ ክሮሻዊያን እና ስሎቫኒያ ደግሞ የይጎዝላቪያን ሀገር የሚፈልጉትን ማንነታቸውን እውቅና የምትሰጣቸው፣ ከፌደሬሽን ተሻግሮም የኮንፌደሬሽን መስተካከል/ ምህዳር ያላት ሀገር እንድትሆን ግዙፍ ፍላጎታቸው/ ምኞታቸው እየሆነ ቆይቷል። ይህ እና መሰል ልዩነት የፈጠረው በሂደት በመካከላቸው ቀላል ያልሆኑ ግጭቶች ቂም በቀል፣ ግድያ እና አፈና (እ.ኤ.አ በ1982 - 1934 በ10 አመት) ውስጥ እየተጠናከረ ክሮሺያዊያን ደግሞ የዮጎዝላቪያ አካል አንሆንም በሚል ሀገር የሚመሰርቱበትን አጀንዳ ይዘው በወቅቱ በውስጣቸው የነበረ አንድ ፋሺስታዊ ፓርቲ በሂትለር ታግዞ በሰርባዊያን እና ሌሎች ህዝቦች ላይ ጭፍጨፋ ፈጽሟል፤ በጊዜያቸው ሰርባዊያን ተበቀሏቸው። እንዲህ እያለ በተለይ ሰርብ እና ክሮሺያ እያንዳንዱ በማያቋርጥ ግጭት እና መጠፋፋት ውስጥ በመግባት የመፈራረስ አፋፍ ላይ ደረሱ።

እንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሳሉ ሁለተኛው የአለም ጦርነት ተጠናቆ ፀረ-ፋሺስትነት ሲታገል የቆየው የክሮሺያ ተወላጅ የሆነው ማርሻል ጆሴፍ ቲቶ እና ፓርቲው እድል አግኝቶ ወንድማማችነትን እና አንድነትን ለማዳን በሚል አንድነቷ የተጠበቀ ዮጎዝላቪያ ብሎ እ.ኤ.አ በ1945 የሶቬት ህብረት ሞዴል በመጠቀም የስድስቱን ብሄሮች መሰረት ያደረገ አዲስ የፌደራሊዝም አደረጃጀት ስርዓት በህገ መንግስት አጽድቆ መሰረተ። ማርሻል ጆሴፍ ቲቶ በመራባቸው 35 አመታት ውስጥ ህገ-መንግስቱን ለ5 ጊዜ ያህል አሻሽሏል። በተለይ እ.ኤ.አ በ1974 መጨረሻ ላይ ክልሎች የራሳቸውን ክልላዊ ጉዳዮች ራሳቸው የሚወስኑበትን ሙሉ

እውቅና የሚሰጥ ማሻሻያ አድርጎ በሰርቢያ ይኖሩ የነበሩ ኮሶቮ እና ቮድቮዲናም የራስ ገዝ አስተዳደር እንዲያገኙ አደረገ፡፡ እነዚህ ክስተቶች/ እድገቶች ግን በሰርቢያዊያን አይን ለዲሞክራሲያዊ አንድነት መሻት ሳይሆን ሆነ ተብሎ ሰርባዊያንን ለማዳከም የተደረገ ነው ብለው በህዝባቸው ፀረ-ቲቶ ህቡዕ እና ይፋ የሆነ ሰፊ ጎራ ከፈቱ፡፡ ጆሴፍ ቲቶም ሞተ፡፡

ዮጎዝላቪያ ከማርሻል ጆሴፍ ሞት በኋላ የዮጎዝላቪያን አንድነት ያስቀጥላል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው ጠቅላይ ሚኒስቴር ካር ማሊክ (የክሮሺያ ተወላጅ) መምራት አቅቶች ፓርቲው ተዳክሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ክልሎች በየራሳቸው ብሄርተኛ ድርጅቶች መመራት ስለጀመሩ ከፌደራል መንግስት ቁጥጥር እየራቁ በሂደትም የሰርቢያ አክራሪ ብሄርተኞች በስሎቮዳን ሚሎሶቪች እየተመሩ የዮጎዝላቪያ ፖለቲካዊ ቀውስ እየተካረረ ቆይቶ በተካሄደው ምርጫ ሁሉም የአንድነት ድርጅቶች ከሜቄዶንያ በስተቀር በሁሉም አንዳምን ድምጽ ያላገኙ ብሄርተኛ ድርጅቶች ወደ ስልጣን መጡ፡፡ ሰርባዊያን አክራሪ ብሄርተኛ መሪያቸውን በስሎቮዳን ሚሎሶቪች በይፋ ወደ ስልጣን አመጡ፡፡ ሚሎሶቪች በቀጥታ ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር በሚያመች የፌዴራል ተቋማት በሰርብ ተወላጆች እንዲያዙ አደረገ፡፡ እንቅፋት ይሆናሉ ያላቸውን ለዘብተኛ ሰርብንም ጨምሮ በዋናነት ግን የክሮሺያ ተወላጆችን መንጥሮ አባረራቸው፡፡ ቋሚ ጠላቶች እንዳይሆኑ በሚል የተሻለ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም በሚገኙባቸው የግል ድርጅቶች መደቧቸው፡፡ ጠቅላላ ሚዲያው ፀረ ክሮሺያዊ፣ ስሎቫኒያ፣ ኮሶቫውያን፣ ሙስሊም ቡስኒያውያን፣ የዮጎዝላቪያ አንድነትን የሚቃወሙ ናቸው በማለት ሁሉንም ወንጀሎች ማሸከሙን ቀጠለ፡፡ የዩጎዝላቪያ የመከላከያ ሀይል 50በመቶ የሰርብ ተወላጆች ስለነበሩ እና በተፈጠረው የጽንፈኛ ብሄርተኝነት ሳቢያ የመከላከያ ሀይሉንም በእጁ አስገባ፡፡

ብሎም የቆየውን ህገ-መንግስት ንዶ እውቅና የነበራቸውን እንደ ኮሶቮ በሀይል ወሮ የሰርብ አካል አደረገ፡፡ ይህንን የተመለከቱ ክልሎች በሙሉ ወታደራዊ ጥቅት እንደማይቀርላቸው የተገነዘቡ በተለይ ክሮሻዊያን እና ስሎቫኒያ ተቀላጥፈው የየራሳቸውን የመከላከያ ሀይል ግንባታ ጀመሩ፡፡ የሀገር እንሁን አጀንዳዎችን ጀመሩ፤ በተለይ ስሎቫዊያን እ.ኤ.አ በ1990 ክልላዊ ህገ መንግስታቸውን በማሻሻል የመገንጠል መብትን በህገ መንግስታቸው አሰፈሩ፣ በዚህ ወቅት አጠቃላይ ዩጎዝላቪያ እንደ አዲስ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ከማርሻል ጆሴፍ ቲቶ በፊት ወደ ነበሩበት ሙሉ በሙሉ ቀውስ ውስጥ ገቡ፡፡ ብሔሮቹ የራስን እድል በራስ የመወሰን እና የኮንፌደሬሽን ቅርጽ ያለው አደረጃጀት እና አስተዳደር ሲጠይቁ የሚሎሶቪች መንግስት በአንፃሩ እ.ኤ.አ በ1974 በመጨረሻው የቲቶ ዘመን የወደቀውን ህገ መንግስት ሀገር በታኝ ነው፣

ሰርቫዊያንን ለማዳከም ሆነ ተብሎ የፀደቀ ነው፣ በሴራ የተሞላ ህገ መንግስት ተብሎ እንዲፈርስ እና ፀረ ክሮሺያ ደግሞ የተቀናጀ የሚዲያ ጥቃት በመቀጠል የታላቋ ሰርቢያ አንድነታዊ ግዛት በሚል መሪ ቃል በ1991 በክሮሺያ፣ ስሎቫኒያ እና ቦስኒያ ይፋዊ የመንግስት ወረራ ተፈፀመ፡፡ የስሎቫዊያን ጦርነት በቀላሉ በ37 ወታደሮች (ከእዚህ 132 ወታደሮች ስሎቫዊያን) በሆኑት ሲጠናቀቅ ስሎቢያ ነፃነቷን አወጀች፡፡ በክሮሺያ እና ቦስኒያ ላይ የነበረው ጦርነት ግን የደም መፋሰስ መልክ ይዞ ዘልቆ በተለይ በክሮሺያ እና ሰርብ መካከል የተካሄደው ጦርነት ከ200ሺ በላይ ህይወት የቀጠፈ እና ከ1ሚሊየን በላይ ህዝብ ያፈናቀለ ሲሆን የአለም ማህበረሰብ ገብቶበት ጦርነቱ ቆሟል፡፡ ዮጎዝላቢያ በ72 አመቷ ተበታተነች፤ ሁሉም ነፃ መንግስታት መሰረቱ፡፡

ዩጎዝላቢያ ፍትህን እንዲህ በመሰለ ደም አፋሳሽ ጥፋት አጠናቃለች፡፡ ከአጠገቧ በተመሳሳይ ወቅት ቼኮዝላቫኪያ ካለ ምንም ግጭት ተመሳሳይ ፍትኂን አገባለች፡፡ የሁለቱም ኩነት የየራሱ መሰረታዊ ምክንያቶች ነበሯቸው በእኩልነት የመኖር አመለካከት መሰረታዊ ጉድለት በሰርቢያ በኩል ከፍተኛ የትምክህት አመለካከት ሆኖ ከዚህ የሚነሳም የመጠቅለል አመለካከት እና ተግባር ሌሎቹን ህዝቦች ደፍጥጦ ለመግዛት በወታደራዊ እና በመሳሪያ ሀይል የታጀበ ወረራ ታጅቦ በሰርብ የበላይነት የምትዋጥ ሀገር ለመፍጠር አልመው ወረራ ፈጽመዋል፡፡ የፈለገ ሀይል ቢኖረውም በማንኛውም መንገድ አንዱ በሌላኛው ላይ ከእኩልነት እና መተሳሰብ ውጪ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መንበርከክም ይሁን አብሮ መኖር እንደማይቻል እና በደም መፋሰስ መጠፋፋትን ብቻ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ በቼኮዝላቫኪያ የነበሩ ሁለት ብሄረ ቼክ እና ስሎቫኪያ የዚሁ የትምክህት እና የጠቅላይነት አመለካከት አልነበረም፡፡ አንኳር የችግሩ ምንጭ ዮጎዝላቢያን ደፍጥጦ፣ ጨፍልቆ ጠቅልሎ መግዛት የሚፈልግ እና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ይዘው በእኩልነት እና በነፃነት መኖር በሚፈልጉ መካከል ፖለቲካዊ ግጭት ነው የነበረው፡፡ በቼኮዝላቫኪያ የሚገኙ ስሎቫካዊያን ጥያቄያቸው በእድገት ከቼክ ወደኋላ ቀርተናል፣ ከቼክ ጋር በመዋሀዳችን ነው ሲሉ ነበር፡፡ ቼክ ደግሞ ስሎቫካዊያን እንደ ግዛታቸው በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ላይ ምንም አስተዋጽኦ እያበረከቱ አይደለም የሚል ሲያነሱ ነበር፡፡ የመፋታት/ የመለያየጥ ጥያቄ በስሎቫካዊያን ተነስቶ ቼክም በአዎንታ ተቀብሎ ፍቺውን በሰላም ጨርሰው ሀብታቸውን ተከፋፍለው ወደየ ጎጆዋቸው ገብተዋል፡፡

ከዚህ እኛ ምን እንማራለን፦ በሀገረ ዮጎዝላቢያ ያጋጠመው ሁኔታ ጉዞው በሙሉ የእኛን ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ የግዛታዊ አንድነት ምንጭ መጀመሪያ ላይ በሀገራችን በሀይል እና ድፍጠጣ/ ጭፍለቃ በዮጎዝላቢያ ከነበረው የግፍ ፍላጎት በሚመስል መልኩ ተመስርተዋል፡፡

ከዚያ በኋላ ያለው ፍላጎት እና አመለካከት ግን ሁኔታው ለእኛ ስዕል ነው፡፡ ብዝሃነት ያለው ሀገር በፍላጎትም ይፈጠር በጉልበት / በሀይል በእኩልነት የሚያኖር አስተማማኝ እና ዋስትና ያለው ማስተካከያ ከሌለ የወቅቱ ሁኔታ የፈለገ ቢሆንም መጨረሻው መበታተን ነው፡፡ ለዛውም ደም በሚያፋስስ ጦርነት፡፡ ወደ ሀገራችን ስንመጣ የኢትዮጵያ ግዛት ሙሉ በሙሉ በሀይል የተፈፀመ ሲሆን በዚህች ሀገር እኩልነታዊ አንድነት ፍላጎት እና አመለካከት ሆነ ነፃ መንግስት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ሊሂቃል በሰርብ እና እነ ክሮሺያ እና ሌሎች መካከል የነበረው መሰረታዊ ልዩነት እኛም ጋር ካለ ልዩነት ደፍጥጦ፣ ፍልቆ፣ ጠቅልሎ መግዛት የሚፈልግ እኩልነታዊ አንድነት እንዲተገበር የሚፈልግ ከፊሉ ደግሞ ራሱ የሚጠቀልላት ካልሆነም ደግሞ መውጣት የሚፈልግ ነው፡፡ የዚሁ የፍላጎት እና የአመለካከት መሰረታዊ ልዩነት ዘወትር የተጠመደ ፈንጂ ከእኛም ጋር ያለ ነው፡፡

ታሪክ ራሱን ሲደግም ደግሞ ኢትዮጵያ በኢህአዴግ የመለስ መሪነት በደርግ ውድቀት ለመበታተን አፋፍ ላይ ደርሳ የነበረችውን ሀገር ታድጓት ለ27 አመታት ተጉዛለች፡፡ በማርሻል ጆሴፍ ቲቶ ወቅት ከ2ኛው የአለም ጦርነት መጠናቀቅ በኋላ በመበታተን ጫፍ ላይ ደርሳ የነበረችው ዮጎዝላቪያ ቲቶ እና ፓርቲው ታድገዋት ለ35 አመታት ዘልቃለች፡፡ በሁለቱም ሀገራት ኢትዮጵያ እና ዮጎዝላቪያ የማዳኑን / የመታደጉን እና ተነፃፃሪ ለውጡን የመሩ ፓርቲዎች በተለይ መሪዎቻቸው ከሞቱ በኋላ ድርጅቶቹም ለተወሰነ ጊዜ ቢቆዩም ውስጣዊ የአገዛዝ ትግል ተዳክሞ የመጡ የሁለቱም ሀገራት መሪዎች በተመሳሳይ ደካሞች ነበሩ (ካርማሊክ፣ ሀይለማርያም ደሳለኝ) ከሁለቱም ሀገራት የቆዩት አብዮታዊ ፓርቲዎች በስብሰው ከወደቁ በኋላ የተተኩ ፓርቲዎች እና መሪዎቻቸው ደግሞ እልል የተባለላቸው አሀዳዊያን እና ፍፁም አምባገነን የሆኑ በኢትዮጵያ አብይ አህመድ፣ በዮጎዝላያ ደግሞ ስሎቮዳን ሚሎሶቪች በተለያየ ዘመን እና አህጉር ነገር ግን ከአንድ ማህጸን የወጡ አንድ አይነት ባህሪ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ተግባርም አንድ የሆኑ እልል የተባለላቸው ፀረ-ህዝብ አመራሮች መጥተዋል፡፡ አብይ አህመድ ደግሞ ሁሉም ስሎቮዳን ሚሎሶቪች ያደረጋቸውን እያደረገ ነው፡፡ አንድ የምትቀረው ወታደራዊ ወረራ ነው - ሚሎሶቪች ለይቶ ክሮሺያ ላይ ወረራ እንደፈፀመ ሁሉ አብይም አቅም ካገኘ ካለ ጥርጥር በትግራይ ላይ ወረራውን ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ ግን አሁን ኢትዮጵያ ልክ ዮጎዝላቪያ ስትበታተን የነበራት ሁኔታ አላት፡፡ እጣችንን አላወቅንም - ወዴት እንል ይሆን?.....

የስዊዘርላንድ ተሞክሮ - ስዊዘርላንድ ከዘመናት በፊት በውስጣቸው የተለያዩ ጦርነቶችን እያካሄዱ ቆይተው በኋላ ላይ ዋነኛ ነዋሪዎች የሮማንሽ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ፈረንሳይ ብሔሮች ባደረጉት

አዲስ የፌደራሊዝም ስርዓት ማስተካከያ ለረጅም ጊዜ ገንብተው እየኖሩ የሚገኙ እና ለአለም አብነት/ አርአያ የሆኑ ህዝቦች ናቸው፡፡ ህገ-መንግስታቸው ሲጀምር የሚገልፀው ‹‹ህዝብ እና ካንተንስ (ክልሎች) ለስዊዘርላንድ ፌደራላዊ ስርዓት ስዊዝን እንደሚመሰርቱ ይደነግጋል››፡፡ የፌደራል ስርዓቱን የሚመሰርቱ ካንተንስ (ክልሎች) 26 ሲሆኑ 20 ሙሉ ካንተንስ እና 6 ደግሞ ግማሽ ካንተንስ ናቸው፡፡ በህገ-መንግስታቸው ካንተንስ (ክልሎች) ሙሉ የሚባል ሉአላዊ ስልጣን አላቸው ይህ ሉአላዊ ስልጣን በህገ መንግስታቸው የተቀመጠ ሆኖ የተስማሙበትን የፌደራል ህጎች የማይቃረን ሲሆን ለውስጥ የክልሎች ሉአላዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ክልል ከክልል ጋር፣ ክልሎች/ ካንተንስ ከውጪ መንግስታት ጋር የሚገናኙባቸው ጉዳዮች ትልቅ መብቶችን የሚፈቅድ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ የክልሎች ግዛታዊ ሉአላዊነት ደግሞ የፌደራል መንግስት የመጠበቅ እና የመከላከል ግዴታ እንዳለበት፣ አዲስ ክልል ለመፍጠር ወይም ለመቀየር ሲያስብም የካንተንስ እና የህዝቡን ይሁንታ/ ፈቃድ እንደሚጠይቅ በህግ የተቀመጠ ነው፡፡

በስዊዘርላንድ የህዝቦች ፖለቲካዊ መብቶች በጥብቅ ተጠናክረው የተቀመጡ ናቸው፡፡ ህዝቡ የምክር ቤቶችን ምርጫ ብቻ ሳይሆን ዜጎች በቀጥታ ራሳቸው ተሳትፈው የሚወስኑበት አስገዳጅ እና እንደ አማራጭ የተቀመጡ በሁለት የተከፈለ የህዝበ ውሳኔ (ሪፈረንደም)፣ የፌደራል ህገ መንግስት ማሻሻያ፣ የጋራ ደህንነት የአስቸኳይ ሁኔታ አዋጅ አደረጃጀት እና ማስተባበር እንዲሁም አጠቃላይ የፌደራል ህገ-መንግስት ማሻሻያ እንደ አስገዳጅ ህዝበ-ውሳኔ (ማንዳቶሪ - ሪፈረንደም) እንደ አማራጭ ለህዝብ የሚቀርቡ ጉዳዮች ደግሞ የፌደራል ህጎች፣ ከአንድ አመት በላይ የቆየ አስቸኳይ አዋጅ፣ የፌደራል መንግስት ከህገ-መንግስት ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች፣ አለም አቀፋዊ ስምምነቶች፣ ህግ ሆነው በፌደራል ምክር ቤት እንዲፀድቁ የሚጠበቁ አማራጭ ህዝበ - ውሳኔ ተብለው የሚታወቁ ስርዓቶች አሏቸው፡፡ በአጠቃላይ በስዊዘርላንድ ፌደራላዊ ስርዓት የካንተንስ / ክልሎች ከፍተኛ ሉአላዊ ስልጣን፣ ልል (ከፊል ኮንፈደሬሽን) የፌደራል ስርዓት የገነባ ህዝብን በሰፊው ቀጥተኛ ተሳትፎውን የሚያረጋግጥ ብቻ ሳይሆን ጉልበተኛ የሆነ ማእከላዊ ወይም የፌደራል መንግስት እንዳይፈጠር፣ ጉልበታም እንዳይሆን የካንተንስ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በአስተማማኝ ሁኔታ የሚከላከል ነው፡፡ የፌደራል መንግስት ውሳኔዎች እና ተግባራት በሙሉ በካንተንስ /ክልሎች እና ህዝብ ጥቅም ይለካል፡፡ በአጠቃላይ በዋናዎቹ መስራቾች አራት ብሄሮች ሮማንሽ ተወላጆች እና ጥቂት ጀርመን ፍፁም አብላጫ ቁጥር ያላቸው ጣሊያን እና ፈረንሳይ ሆነው ብዙዎች ደግሞ ከተለያዩ የአውሮፓ እና ሌሎች የአለም ሀገራት ይዛ በሚያስገርም መረጋጋት ከ150 አመታት በላይ የዘለቀች፡፡ የሚያስደንቅ የማያቋርጥ የእርስ በእርስ ጦርነት እና መጠፋፋት ለ132 አመታት ደግሞ በኢትዮጵያ ግልጽ ትምህርት ነው፡፡

የካናዳ - ኩቤክ ተሞክሮ የፌደራሊዝም ስርዓቱ ህብረ ብሄራዊ ባህሪ የለው ሆኖ የተቀረፀ ነው በተለይ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የኩቤክ ብሄሮች ልዩ ከለላ የሚያደርግ በየጊዜው እያደገ የመጣ አብነታዊ የፌደራል ስርዓት ነው፡፡ በካናዳ በማዕከላዊ መንግስት እና ክልሎች መካከል ያለው የስልጣን ክፍፍል በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከተባበሩት የአሜሪካ መንግስታት እንደ ተሞክሮ ወስደው የተገበሩት ነው፡፡ ከ1980ዎቹ ጀምሮ ደግሞ የኩቤክ ብሄር የሉአላዊነት ጥያቄ እየተጠናከረ ከመጣ በኋላ የካናዳ የፌደራሊዝም ስርዓት የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን የማረጋገጥ ጉዳይ እንደ አውራ የዴሞክራሲ ስርዓት ተደርጎ እየተወሰደ የመጣ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ኩቤክ እንደ አንድ ሉአላዊ ክልል የራሷ ህገ-መንግስት እንዲኖራት ከሌሎች ፕሮቪንስ /አውራጃዎች/ በተለየ መልኩ የህግ አውጪ ምክር ቤት፣ የብሄራዊ ጉባኤ ሁለተኛ ምክር ቤት ያላት ክልል ነች ኩቤክ፡፡ የካናዳ ማዕከላዊ መንግስት በየ5 አመቱ ምርጫ ሲያካሂድ ኩቤክ ደግሞ በራሳቸው ህግ በየ4 አመቱ ምርጫ ያካሂዳሉ፣ በኩቤክ ህገ-መንግስት የተቀመጡ ልዩ መብቶችም አሉ፡፡

ኩቤክ ሉአላዊ እና በህገ-መንግስት እንደተመሰረተች እንዲሁም ሉአላዊ ስልጣን እንዳላት ይህ ደግሞ የኩቤክ ሉአላዊነት ህጋዊ ደረጃውን ለመወሰን የማይጣስ መብት እንዳላት በመሆኑም በካናዳ የሚደረጉ ህገ-መንግስታዊ ማሻሻያዎች ኩቤክን እስካልጎዳ ድረስ ነው፡፡ የሚጎዱ ጉዳዮችን አስመልክቶ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት ተቀምጦላታል፡፡ የውስጥ ክልላዊ ጉዳዮችን የራሷ የመወሰን ስልጣን በመያዝ እስከ ስልጠና ድረስ ባሉት ጉዳዮች የውጭ ግንኙነት እና ዝምድናዎችን የመፍጠር መብት አላት፡፡ ግንኙነትን እንድትመሰርት፣ እንድትደራደር፣ በአለም አቀፋዊ ጉዳዮች ኩቤክ እንድትወክል፣ ከአለም እና አለም አቀፋዊ ተቋማት ጋር እንድትገናኝ የሚያደርግ ስልጣን ተቀምጦላታል፡፡

የኩቤክ ዜጎች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ መብት በቂ ህጋዊ እና ተቋማዊ ዋስትና አላቸው፡፡ በአጠቃላይ ኩቤክ እንደ አንድ የካናዳ ፌደራል አንድ አካል ሆና ነገር ግን አንድ መንግስት ማሟላት የሚገባውን ግዛት፣ ህዝብ እና አስተዳደራዊ ነፃነት ያጠቃለለች ሆና በካናዳ ሉአላዊ ነፃነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እየኖረች ትገኛለች፡፡ የመገንጠል ጥያቄ ሲነሳም ውድቅ እያደረጉ ቀጥለዋል፡፡ እንግዲህ ሁለት መልክ ያላቸው በቂ ተሞክሮች ታይተዋል፡፡ በብዝሀነት የተመሰረቱ ሀገራት በሉአላዊ ነፃነት እና አንድነት መድረክ ሙሉ በሙሉ ማስተካከያ እያደረጉ የሚሄዱ የተሟላ የሰላም እና የልማት ሽግግር እና ዘላቂ ጉዞ ዋስትናን የሚያረጋግጡ፣ በዚህ መሄድ ያልቻሉ መጠፋፋት፣ መበላላት እና መበታተን፡፡

አንዱን ጉዞ ከዮጎዝላቪያ፣ ሌላኛው ጉዞ ደግሞ ከስዊዘርላንድ እና ካናዳ ማየት ይቻላል፡፡ እኛስ ወዴት ?.........

### 2.4.3. የዚህች ሀገር እና የትግራይ ህዝብ የመጨረሻ ጉዞ

I. እስካሁን ድረስ በግልጽ ቋንቋ ከውስጣችን የጉዞ ሂደትም ሆነ ከአለም ተሞክሮ የተገነዘብነው የመጨረሻው መልዕክት ብዝሀነቷ መገለጫዋ የሆነው ኢትዮጵያ ከዚህ በኋላ በግዛታዊ አንድነት (ኢምፓየር) አንድም እርምጃ መራመድ / መቀየል አትችልም፡፡ አሁን ባጋጠመው ውድቀት ሁሉም ነገር ተቀያይሯል፡፡ የቆየው ህገ-መንግስታችን ያረጋገጣቸው ሁሉን አቀፍ መሰረታዊ መብቶች ስላሉት እሱም ወደ ቦታው እንዲመለስ እንደ ቁልፍ መፈክር /መሪ ቃል/ ይዘን በዚሁ ስልታዊ መድረካችን መታገል እና አሁንም ቢሆን ጠላት እስኪወድቅ ድረስ መቀጠላችን ግዴታችን እና ትክክለኛው የትግሉ ስልት ነው፤ ይህንን ካልያዝን ወደ ሌላ መሸጋገር ስለማይቻል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ በኋላ በነበረው ማስተካከያ መቀጠል አይቻልም - ቃል ኪዳኑ ፈርሷል፡፡ በዚያ መቀጠል አይቻልም ብቻ ሳይሆን መጠነኛ ማስተካከያ ተደርጎበትም የሚፈታ እና የሚዘልቅ አይደለም፡፡

II. ከተጨባጩ መሬት በላይ ያ የቆየው ህገ-መንግስታዊ ማስተካከያ ለህብረ-ብሄራዊ ሀገረ መንግስት ግንባታ እንደ ቁልፍ እሳቤዎች የተወሰዱ ጉዳዮችም ነበሩበት፡፡ የልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር እየተጠናከረ እና እየጎለበተ እንዲወጣ እና የጭቆና ትግል በቀጣይ እንዲቀጣጠል፣ በዚህም ጠባብነት እና ትምክህት እየተዳከሙ ዲሞክራሲውን ብሄርተኝነት እየጎለበተ እንዲወጣ፣ ተጀምሮ በነበረው ፈጣን ልማት የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በልማታዊነት እንዲተካ፣ ስለዚህም በልማት እና ሽግግር ተመጋጋቢ ሐዲድ ላይ ሆነን በፍጥነት ልናመልጥ እንችላለን በሚል እንጂ አደጋው ተጨባጭ እና ቅርብ እንደሆነ መስመራችን አስቀምጦታል፡፡ በእነዚሁ ሁኔታዎች ደግሞ አደጋው ገጥሟል፡፡ ኢህአዴግ የለም፤ በሀገር ደረጃ ልማታዊ ዴሞክራሲ ድኖ የመደብ ትግል አይሎ ትምክህተኝነት እና ጠባብነት ትርጉም ወደሌለው ደረጃ የሚወርድበት ወቅት ማንም ሊገምት እና እርግጠኛ ሊያደርገው አይችልም፡፡ የሁለቱም ግዙፍ ብሄሮች ሊሂቃን የትምክህት እና ጠባብነት አመለካከት በአንድ ላይ ወይም እየተበራዩ በበላይነት ስሜት እየተናከሱ ልክ እንደ አሁኑ ይቀጥላል፡፡ ይህ ደግሞ የማያባራ ጦርነት፣ መጠፋፋት እና መውጫ የሌለው አዙሪት ነው፡፡

III. የኢትዮጵያ ብሔር እና ብሄረሰቦች ከተጨባጭ ውስጣዊ ሁኔታዎች እና አለም የሚወስደው ትምህርት ተወስዶ የራሳቸው የመንግስት ቅርጽ እና ፍላጎት ሙሉ ዋስትና በሚሰጥ አዲስ የአስተዳደር እና ፖለቲካዊ ስርዓት - መሰረታዊ ማስተካከያ / ለውጥ (ራዲካል ቼንጅ)

ካልተደረገበት የሚያስቀጥል ሁኔታ የለም። ስለሆነም በዚህ ወቅት በሀገራችን ሁለት አማራጮች ናቸው የዚህች ሀገር ጨፍላቂ ተፈጥሮአዊ ምስረታ ሊደረጉ የሚችሉ መፍትሄዎች መዋቅራዊ ማስተካከያ/ ለውጥ (ሪ-ስትራክቸር) አንዱ የልማት እና ሽግግር ሁኔታ አንዱን ፖለቲካዊ አስተዳደር እና ፀጥታ እንዲሁም አካባቢያዊ እና አለም አቀፋዊ ትስስሮችን የሚወስኑ ስልጠን እና ሀላፊነት በሙሉ ለብሄሮች/ ክልሎች በማውረድ የክልሎች ጠንካራ ሉአላዊ ስልጣን የሚያረጋግጥ ከዚህ ጋር የዜጎች የመንቀሳቀስ እና ሀብት የማፍራት ሙሉ መብትን የሚያረጋግጥ፣ የጋራ ይቅሞች እና ትስስሮችን የሚገልጽ ክልሎች በተናጥል ለመስራት የሚያስቸግራቸው ነገር ግን የእያንዳንዱ ክልል ፖለቲካዊ፣ ፀጥታዊ እና ልማታዊ ነፃ ጉዞ በፍፁም የማይገዛ እና ተቆጥረው በሚቀመጡ የቃል ኪዳን ስምምነቶችን የሚደግፍ ልል (ሉዝ ፌደራል ሲስተም) የፌደራል መንግስት መፍጠር።

ይህ የፈለገ ስም ቢሰጠውም ነገር ግን እንዲህ አይነቱ አዲስ ለውጥ/ ማስተካከያ እንደ እነ ስዊዘርላንድ አይነት መሰረታዊ ለውጥ የግድ ያስፈልጋል። ይህ ለውጥም ወደድንም ጠላንም በጋራ ለቆየንበት እና አሁን ሊገኝ የሚችለውን በታላቋ ሀገር ጥላ ስር የጋራ ጥቅምን ጠብቆ ሀገር ሳትበታተን በጋራ የሚያስቀጥለን አማራጭ ነውና። ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ጉዞው የብሔረ መንግስት ግንባታ ነው። የየራሱ ማንነት ያለው ማንኛውም ህዝብ፣ ብሄር ብሄረሰብ በማንኛውም ምክንያት የፈጠራቸው ትስስሮች ዋነኛ ልዩነቱ ከመንግስታዊ ይዘት ጋር ያለው ግጭት ነው። ስለሆነም የላይኛው እድል ሊገኝ ካልተቻለ አርፎ የሚቀመጥበት ሁኔታ የለም። በታሪክም አልታየም። ከሁሉም ኢምፓየሮች የምንማረውም ይህንኑ ነው። ስለሆነም በከፍተኛ ቅን ልቦና እና ህዝባዊ፣ ብሔራዊ እና ሀገራዊ ሀላፊነት በተሞላበት እንደ ቼኮዝላቫኪያ ህዝቦች ወይም ደግሞ እንደ ስዊዘርላንድ እና የመሳሰሉ መፍትሄዎችን ከመጠቀም ውጪ አማራጭ የለም። በደም መፋሰስ መበታተን ዘወትር ያለ አደጋ ነው አማራጭ አይሆንም እንጂ። የልማታዊ ዲሞክራሲ መስመር በፍጥነት የሚመለስበት የትምክህት እና ጠባብነት ቁሳዊ /ማቴሪያላዊ መሰረቱ የሚደርቅበትም በእነዚህ አማራጮች ነው። የትግራይ ህዝብም ድርጅቱ ህ.ወ.ሓ.ት ጊዜውን ሳያጠፋ ከሁለቱ አንዱን አቋም ይዞ መንገዱን ያስተካክል።

### 2.4.4. **ለትግራይ ህዝብ ዘላቂ ጥቅም የማያዳግም መፍትሄ !**

**(አይደገምም - ኔቨር አጌን)**

I. የትግራይ ህዝብ ከረጅም እና መራራ የትጥቅ ትግል በኋላ በከፈለው መስዋትነት አስገራሚ ድሎችን ጨብጦ ሀገር የራሷ ጉዳይ ሳይል የቆየ የሚኒሊክን ግዛታዊ አንድነት ሰባብሮ አዲስ በእኩልነታዊ አንድነት የሚኖርበትን ፕሮጀክት በማብሰር በመበታተን አፋፍ ላይ ደርሳ

የነበረችውን ሀገር በመታደግ ከአጋሮቹ / ጓዶቹ ጋር ነገር ግን ቁልፍ አስተዋጽኦ / አበርክቶውን የተወጣበት ታሪክ ሰርቷል፡፡ እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ብሄር የሚኖሩበትን መድን አማራጩን አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ በትግሉ መንግሎ የጣለውን ጨፍላቂ ስርዓት የድሎቹ መገለጫ ወደ ማይመለስ ደረጃ ሳያደርስ መሀል ላይ ተነስቶ በመልሶ ማጥቃት የትግራይን ህዝብ ወደ ዳግማዊ የጭቆና እና ብዝበዛ፣ ብሔራዊ ጠቅላይነት አገዛዝ የሚመልስ የጠቅላይ / የአሀዳዊ ሀይል ስልጣኑን ተቆጣጥሮ አደገኛ የሞት ሽረት ግጥሚያ / ፍልሚያ ከ27 አመታተ በኂላ ገጥሞታል፡፡

II. የትግራይ ህዝብ አሁንም ያጋጠመው የህልውና ስጋት ተጋጥሞ ከመመከት እና እየመከተም ስለሚገኝ ማሸነፍ/ ድል መንሳት ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም፡፡ ነገር ግን ይህንን መክቶ ወዴት የሚል ጥያቄ በዚሁ የምከታ እምብርት ላይ ሆኖ ካለፈው ጉዞ ሙሉ ትምህርት ቀስሞ/ ወስዶ እንዲህ አይነት የመሳሰሉ ሁኔታዎች ዳግም እንዳይመለሱ ይልቁንም አዙሪቱን ሰብሮ በፍጥነት ወደ ዘላቂ ከፍታው የሚወጣበትን አስተማማኝ ለውጥን ይዞ መውጣት እና መተግብ አለበት፡፡ ይህ ጉዳይ ለትግራይ ህዝብ ጊዜ አይሰጥም፣ ተቀጣጣይ ነጥብ ነው፡፡ መጠረግ እንዳለበትም በመስማማት/ መግባባት ላይ ነው፡፡ ለመጣል ከእያንዳንዱ ለሚፈለገው መስዋትነት እና ዝግጁነትን ማጠናከሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው፡፡ ከአብይ ቡድን በኂላ በተለይ ዘላቂ እና አስተማማኝ ዋስትና ያለው ጉዞዋችን ወዴት ነው ምንድን ነው፣ ወዴት ነው የሚለውን ግን የደረሰበት ስምምነት የለም፡፡ በድርጅቱ ደረጃ ታይቶ መነሻዎች ቀርበው ነገር ግን ህዝባችንም ሆነ የትግራይ ልሂቅ አመለካከቱን/ እሳቤውን ይዞ በትግራይ የወደፊት እድል ዙሪያ መከራከር እና መወያየት አለበት፡፡ የመንገዳችን / ጉዞዋችን ዘላቂ ዋስትና እንዴት እናረጋግጥ? እንደ የስጦታ እቃ ተሸፍኖ የሚቆይ እና ሁሉም ነገር ካለቀ በኂላ እንደ ማስደመሚያ (ሰርፕራይዝ) የሚገለጥ መሆን የለበትም፡፡

III. በመሆኑም ዘላቂ ጥቅማችንን የሚያረጋግጥ አቋማችንን ይፋ አድርገን በድርጅታችን፣ መንግስታት እና ህዝባችን እንዲሁም ልሂቆቻችን መካከል መጠነ ሰፊ ክርክሮች እና ውይይቶችን አድርገን ስምምነት ላይ ደርሰን ለምከታውም እጅግ ጠቃሚ አቅሞችን ልናከማችበት እና ልንሰበስብበት እና ልናጎለብትበት ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት ከየትኛው አማራጭ በፊት ነው አቋም የሚጠቅመን ? ለምን የሚል ማንሳታችን በማንኛውም ሁኔታ ስር የማናደርገውን ለአቋማችንም ታሳቢ የማናደርጋቸውን ነጥቦች አስቀምጦ ማለፉም ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከሁሉም በፊት በማንኛውም አይነት ሁኔታ ይሁን ማንኛውም አይነት መከራ ስር ሆነንም የባርነት ግዛታዊ አንድነትን አንቀበልም፣ አናስበውምም፡፡ እየጎዳን በአዙሪት ውስጥ የሚያኖረን ሹማዊ እኩልነታዊ አንድነትም አያስፈልገንም፡፡ ከአዙሪት የማያወጣንን የቆየውን ፌደሬሽን ማስተካከያ/ ለውጥም

ሆነ ይስተካከላሉ/ ይለወጣሉ የተባሉ ጉዳዮች በማንኛውም መንገድ ወደ ዳግም የህልውና አደጋ የማይመልሱን መሆን አለባቸው፡፡

IV. አቋማችን የቆዩ እና የተዛቡ የአንድነት እና መገንጠል ዝንባሌዎችን የሚያስወግድ መሆን አለበት፡፡ ከአንድነት ጋር ተዛምዶ በአንዱ ወይም በሌላ ከውስጥም ከውጪም የተዛቡ አስተምህሮዎች ቆይተዋል፡፡ ትግራይ ደሃ እና ራሷን መቻል የማትችል ከኢትዮጵያ ተለይታ መኖር የማትችል የኢትዮጵያ ጥገኛ አድርጎ የሚያይ የተዛባ አመለካከትን ምን ይዘን ነው ሀገር የምንሆነው የሚል ተሸናፊ ስነ ልቦና በመያዝ በማንኛውም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መኖር አማራጭ እንደሌለው በሚያይ አመለካከት ተይዞ የትግራይን ደህንነት፣ ዋስትና ወደ መደራደር ነው የሚወስደው፡፡ ከዚህም አልፎ የአንድነትን ጥቅም ከሚገባው በላይ ለጥጦ በመውሰድ ከአንድነት ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ አንድነትም ይሁን ነፃነት የሚያረጋግጥልን ዘላቂ ጥቅም ግብ እንጂ በራሳቸው ግቦች አይደሉም፡፡ በአጭሩ አማራጮቹ በተጨባጭ ነባራዊ ወቅት እና ለዘለቄታው የሚኖራቸው ጥቅም እና ጉዳት በማመዛዘን እንጂ ራሳቸውን እንደ ግብ በመውሰድ መሆን የለበትም፡፡

V. ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ተቆርቋሪነት እና ፍቅርን ይዞ ኢትዮጵያዊነት ከጥንት ታሪካችን በፍፁም የማይለያይ ገመድ / ክር በሚመስል ቅኝት ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ ከመኖር ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ የሚያስመስል አመለካከት፣ ከዚህም አልፎ የኤርትራ፣ ደቡብ ሱዳን እና ሌሎች ሀገሮች ተሞክሮዎችን በማየት ተገንጥለው / ተነጥለው ከጦርነት፣ ድህነት፣ አፈና፣ ስደት እና የከፋ ኑሮ ውጪ ምን ተጠቀሙ፡፡ ኤርትራ ባህር ይዛ፣ ደቡብ ሱዳንም ነዳጅ ይዛ ምን አገኙ እኛማ ምንም ሳይኖረን የሚገጥመን እድል የከፋ/ የባሰ ነው የሚሆነው ከሚል የሚመነጭ አመለካከትን ፀረ ዋስትናዋ የተረጋገጠ ትግራይ ነው፡፡ ከጊዜያዊ ስሜት እና ግፊት የሚነሳ የመገንጠል / የመነጠል ጥያቄ በራሳችን የስራ እቅድ እና ጊዜ ያልተመሰረተ በሌላው ሀይል ሙቀት እና መቀዛቀዝ እየተነሳሱ እንገንጠል የሚል፤ ከዚህም ባሻገር ተገንጥሎ ከውጪም ይሁን ከሀር ውስጥ የሚኖረውን እድል እና ፈተና ያላስተዋለ አመለካከት ሄዶ-ሄዶ ወደ ግራ የሚጥላቸው ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ግልጽ ባልሆነ አቅጣጫ / መስመር ወዲህ ወዲያ ማለት ከዛሬ ነገ እየተባለ ሁሉም እድል ካመለጠን ችግር ነው የሚሆነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን እና ሌሎችን ከግምት አስገብተን ሀሳባችንን ይዘን ለህዝባችን ተደራሽ ማድረግ አለብን፡፡

VI. እንደ ህዝብ ያለን የተቀመጠ አማራጭ የኢትዮጵያ አካል ሆኖ መቀጠል እና ነፃ ሀገር ሆኖ መመስረት እንዲሁም የብሄረ መንግስት ግንባታ ናቸው፡፡ አሁን ከመገንጠል ወዲህ በዚህች ሀገር ያለውን እድል አንጠፍጥፈን ማየት አለብን፡፡ እዚህ ላይ የሚመጣው ወሳኝ / አንኳር ጥያቄ ግን

በየትኛው ማስተካከያ /አሬንጅመንት/ የሚለውን ግና በግልጽ መልሰን በውስጣችን፣ ህዝባችን መካከል ሙሉ በሙሉ መግባባት ላይ ደርሰን ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የብሄር ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ፣ ፀጥታዊ እንዲሁም ሀገራዊ እና አለም አቀፋዊ ተቋማት ዝምድና እና ሙሉ ሉአላዊ ስልጣን አስመልክቶ የራሳችን ህገ መንግስታዊ መብታችንን የሚሰጥ ከሌሎች ብሔሮች/ ክልሎች ጋር ተስማምተን ለፌደራል መንግስት የምንሰጠውን የተወሰኑ ከመተባበር የማይሻገሩ የጋራ ጥቅምን የሚደግፉ የቃል ኪዳን ጉዳዮችን የሚያካትት በአጠቃላይ ግን የፌደራል መንግስት በክልላችን ጉዳዮች ገገዢ እና ውሳኔ ሰጪ የማይሆንበት በራሳችን የፖሊሲ መስመር ስናድግ፣ ስንሮጥ የማያደናቅፈን ይልቁንም የሚደግፈን እና አዲስ መሰረታዊ ለውጥ እንዲኖር ስሙ የፈለገ ቢሆንም ይህ እንዲሆን ነው የምንታገለው፡፡

VII. የትግራይ ህዝብ ለረጅም ጊዜ ከተበታተነው ግዛትም ሆነ ከኢትዮጵያ የግዛት ምስረታ ጀምሮ ህዝቧን እና አድሀሪ ሀይሎቹን ለይቶ በማየት ለጋራ ጥቅም ግንባታ፣ ለውጥ እና ለሀገር ብልጽግና ሲል በጉዞው ሂደት በርካታ መስዋትነቶችን እየከፈለ ቆይቷል፡፡ ባለፉት 17 አመታት ትግል ከፍተኛ መስዋትነት የተከፈለበት እና ጎልቶ የሚታየው የቅርብ ጊዜው ነው፡፡ ይህንን ሁሉ የከፈለው የትግራይ ህዝብ በገገዢ አድሀሪ ሀይሎች የደረሰበት ጭቆና፣ ግፍ እና መከራ ስፍር ቁጥር የሌለው ሆኖ ይሁን እንጂ አሁንም የትግራይ ህዝብ በዲሞክራሲያዊ አንድነት ላይ ተስፋ ሳይቆርጥ የትላንትናውን አሳድጎ / አበልጽጎ አዲስ በጋራ የሚያስቀጥል ፕሮጀክት ይዞ ቀርቧል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ከተሳካ በጋራ ለመኖር እንመርጣለን፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የትግራይ ብሄረ መንግስት ምስረታ እና ግንባታ ጊዜው አሁን ነው፡፡ በቀጣይ ጥቂት አመታት በአንዱ አግባብ የትግራይ ህዝብ የጉዞ ዋስትና የሚረጋገጥበት የዘመናት አዙሪትን ሰብሮ የሚወጣበት የመጨረሻው ታሪካዊ እርምጃ አድርገን ልንታገልበት የሚገባ ነው፡፡

VIII. ይህ ከሞላ ጎደል ጥቅል አቅጣጫ ነው፡፡ እዚህ ላይ ከተስማማን በኋላ ከተለያዩ ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አመለካከት ዲስፕሊን፣ ችሎታ እና ሙያ ያላቸው ከምሁራን፣ ከህዝብ የተወጣጣ አንድ ግዙፍ ኮሚቴ ከውስጡ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያካተተ እንደቋቋም እና ስራውን በአስቸኳይ እንዲጀምር የተተነተነ ሀሳብን ይዘን ለማሳመን እንረባረባለን፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም የብሔራችን /ክልላችን/ ህገ-መንግስት መሰረታዊ ማሻሻያ አንኳር ግብዓት የሚሆንበት ተደርጎ ከዚህ ጋር ተቀናጅቶ የሚፈፀምበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ ግን በተደጋጋሚ በጽሁፍ እንደተቀመጠው በታሪካችን ከሚያጋጥመን እንቅፋት እና ፈተና አሁን የገጠሙን የህልውና ፈተናዎች ጋር የዚህች ሀገር ተፈጥሮአዊ ምስረታ እና ያለፉት 27 አመታት ተሞክሮዎች ታይተው የራሳችንን ጥቅም ማዕከል አድርገን ነገር ግን እኛን የመሳሰሉ ብሄር ብሄረሰቦችን

እንደሚጠቅማቸው በሚያሳይ መልኩ ሙሉ ዝግጅት ተቀላጥፈን ልንተገብረው የሚገባ ነው። ይህ የህዝባችን ዘላቂ ዋስትና የማረጋገጥ የመፍትሄ ሀሳብ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን አስተሳስረን / አዛምደን እንሄድበታለን። አንዱ እና ከሁሉም በፊት የዚሁ ስልታዊ መድረክ ትግላችን የአብይን ቡድን መጣል፣ ህገ መንግስታችንን በቦታው መመለስ እና የሚያሸጋግረን ጊዜያዊ መንግስት ማቋቋም እንደ አንድ ግዙፍ ትግበራ የጀመርነውን ማጠናቀቅ። ይህ አዲስ መፍትሄ አሁን የያዝነው ትግል አንድ አካል ሆኖ ነው መፈፀም ያለበት። አንዱ ከአንዱ በኋላ የሚከተል ሳይሆን ሳይነጣጠሉ ተሳስረው/ተመጋግበው በጥብቅ እንዲሄዱ የሽግግር ጉዜያዊ መንግስት መሰረታዊ ተግባር እንዲሆን ነው የተያዘው።

IX. የዚህ ጉዳይ ተቀባይነት እና ተፈፃሚነት እንዴት ነው

በአጠቃላይ አሁን እየተነሳ ያለው ጉዳይ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ መድረክ ግዙፍ እና ጥልቀት ያለው ሀይሎች የራሳቸው ቦታ ለይተው የሚተናነቁበት አዲስ እና ታሪካዊ መድረክ ይሆናል። የአብይ ቡድን ከወደቀ ወይም ከተንበረከከ በኋላ፣ ተገዶ የሽግግር ጊዜያዊ መንግስት ወደ መመስረት ከደረስን በኋላ የሚቋቋመው ሸንጎ ወቅታዊውን ትግበራ ማለትም ለዘላቂው ሀገር ማስተካከያ/ ለውጥ እና መፍትሔም የሚሰራ ነው። አሁን ባስቀመጥነው አቅጣጫ ከተጓዝን የሸንጎ አብላጫ ቁጥር ብሄር ብሄረሰቦችን የሚወክሉ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። ብሔር ብሄረሰቦችን የሚወክሉም አካላት ስልታዊውን ሆነ ዘላቂ የመፍትሄ ሀሳብ የመቀበል እድሉ ሰፊ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ ዋናው ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ጉዳዩን እንዴት ይመለከቱታል የሚል ነው።

X. የትግራይ ህዝብ፣ የትግራይ ሊህቅ አብዛኛው የአሁኑን መፍትሔ ይቀበለዋል ብቻ ሳይሆን የሚያቀጣጥል፣ ጠንካራ የፖለቲካዊ አንድነት እና የስነ ልቦና የበላይነት በመገንባት ወደ አዲስ ጉዞ - ብሩህ ተስፋ ሊያሸጋግረው ይችላል። የድርጅታችን እና መንግስታችን አመራሮችም እንደዚሁ። በመሆኑም በሀገራዊ ፖለቲካ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚኖረው የትግራይ ህዝብ በሚያሳው ጥንካሬ እንደ አንድ ቁልፍ የሀይል ሚዛን አቅም ሆኖ ይወጣል። የኦሮሞ ህዝብ፣ የኦሮሞ ሊሂቃን ምንም መወላወል አያሳዩም ባይባልም እንኳ ነገር ግን በአዲሱ ማስካከያ / ለውጥ ሁሉም መሰረታዊ ስልጣን የሚባሉ በክልሎች እጅ የሚገባ ስለሚሆን አብላጫ ቁጥር ቢያንስ እንደታችኛው መጠን የከፍተኛ ፍላጎታቸውን ወስደው ሊቀበሉት እና ለተፈፃሚነቱ ሊሰሩ የሚችሉ ናቸው። በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ መድረክ ሁለት ቁልፍ ተዋንያን ትግራይ እና ኦሮሞ መጣሉ - በአግባቡም ይደጋገፋሉ።

XI. ሶስተኛው ጠቃሚ ተዋናይ ሀይል የአማራ ህዝብ እና ሊሀቃን ናቸው፡፡ የህዝቡ መሰረታዊ ፍላጎት ከሌሎቹ ህዝቦች የተለየ ባይሆንም የአማራ ልሂቅ አደናግሮ ሊከፋፍለው ይችላል፡፡ የአማራው ልሂቅ በተለይ የትምክት ማዕከል እና አሽከሮቹ ፀረ-አዲሱ ለውጥ ብቻ ሳይሆን ፀረ-መጠነኛ ጥገናዎችም ናቸው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ፀረ-ያለውን ፌደሬሽን እና ህገ-መንግስትም ናቸው፡፡ ስለሆነም በውስጥም ይሁን በውጪ በሁሉም መዋቅሮች እና መረቦች / ኔትወርኮቹ ጨፍላቂ አመለካከቱን ይዞ ይረባረባል፡፡ የፖለቲካ ገበያንም ይጨምራል፡፡ መጪው እድላቸው እና ተስፋቸውን በተለያየ ምክንያት የሚደበዝዝባቸው የተወሰኑ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በተለይ ከደቡብ ሊኖሩ ይቻላሉ፤ ነባራዊ ችግራቸውን ተገንዝቦ በሚፈታ አቅጣጫ ማቀፍም ይቻላል፡፡ በዋናነት ግን የትግራይ እና ኦሮሞ ሌሎች አራቱም ዳር እና ዳር / ወሰን ላይ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች እንዲሁም ከፊል የደቡብ ብሔሮችን ጨምሮ የአማራው ትምክተኛ ሊህቅ እና ሌሎች ብሄሮች ዋና / ወሳን የፖለቲካ ሀይል እንዳይሆኑ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተወሰኑ ደግሞ ሀገር እየፈረሰ ስለሆነ በጋራ ጥቅም እና እሴት የቆየውን የአንድነት መሰረት / ዱካ/ ስላለ ይህንንም ለዘብተኛው የአማራ ክፍል ሊያቅፍ ይችላል፡፡ በተለይ የሀይል ሚዛን ከተጠናከረ፡፡ ወጣም ወረደ ግን አማራጭ የሌለው ጉዞ ነው እየሆነ ያለው፡፡

XII. የውጪ ሀይሎች የቅርቡ ኢሳያስ ቡድን እና ሌሎች የኢትዮጵያን መረጋጋት የማይፈልጉ የሩቆቹ ምዕራባዊ አለም ሀይሎች የሪፎርም ጥቅሞቻቸውን ላለማደናቀፍ እና አለምአቀፋዊ አመለካከታቸው እና ዞናዊ / ቀጠናዊ ጥቅሞቻቸው ጋር ተሳስሮ/ ተቆራኝቶ በትኩረት የሚከታተሉት እና ጥቅሞቻቸውን የሚጎዳ በመሰላቸው ጉዳይ እጃቸውን መስደድ / ጣልቃ ለመግባት ይሞክራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ቁልፉ ነገር የሀገር ውስጥ ጥንካሬ ነው የሚወስነው፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ግን እነዚህ ሀገራት እና አጠቃላይ የአለም ማህበረሰብ በጉዳዩ እንደሚኖራቸው ጥቅም እና ትኩረት የሀሳብ እና ለውጥ ምንነት፣ የራሳቸውን ጥቅም እንዴት እንደማይቃረን እና ይልቁንም ሀገር ከፈረሰች የሚኖረውን አደጋ እና ጥፋት፣ የእነርሱን ጥቅም እንዴት እንደሚጎዳ፣ በዚህ ቀጠናም የተሻለ ሰላም እና መረጋጋት እንዴት እንደሚፈጠር፣ በአካባቢያችን ጂኦ-ፖለቲካ ዙሪያ አዲስ ክስተት እንደሚያስከትል፣ በሀገሪቱ ተፈጥሮአዊ ምስረታ ላይ ሁከት፣ የመበታተን ነባራዊ / የሚታይ አደጋ መሆኑን ከዚህም አልፎ ወደ ተሻለ ዘላቂ ልማት እና ትብብር የሚያደርስ መፍትሄ እንደሚያመጡ ይህም በተደራጀ መንገድ ሲሰራበት ነው፡፡ በዚህ በኩልም ወደ መግባባት እና መደጋገፍ ማሸጋገሩ የሚቻል ይሆናል፡፡

XIII. እንግዲህ ህ.ወ.ሓ.ት እና የትግራይ ህዝብ የሀገሪቱን ተፈጥሮ ለውጦ የትግራይ ህዝብ ዘላቂ ጥቅምን በማያዳግም የሚያረጋግጥ ጉዳይ ሰንቆ መሰስ ብሎ በመውጣት ይዞት የቆየውን የቀያጅ

ታሪካዊ ቦታውን አጠናክሮ የዚህም ነበልባል ተጽእኖ በአፍሪካ ቀንድ እና ቀይ ባህር ዙሪያ መስፋፋት እንዲችል የትግራይ ህዝብ እና ድርጅታችን ህ.ወ.ሓ.ት ዋስትና የሚያረጋግጥ አዲስ መድህን እና አማራጭ ይዞ ደምቆ ይውጣ፡፡ በትግራ ፖለቲካዊ መድረኮች የተለየ ምዕራፍ ይሆናል፡፡ በዚሁ ድል በኩል ዞሮ ዞሮ ለረጅም ጊዜ እቅድ አላማችን ማብሰሪያ የሆነውን ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመር የሚጠበቅበት እና ተጠናክሮ የሚወጣበትን እድል የሚያሰፋ ይሆናል፡፡ ይህም ሆነ ሌላ አንዱን ለመፈፀም ግን ትላንትም ሆነ ዛሬ ወይም ነገ የወትሮ ጉዳያችን ውስጣዊ አቅማችንን የማጠናከር፣ የመደራደር አቅማችንን ጫፍ ላይ የሚያደርስ በዲፋክቶ መንገድ ከፍተኛ ደረጃ ማሸጋገር ላይ እንገኛለን፤ ለዚህም ሁሉም አይደገምም ብለን እንነሳ፡፡

**መስመራችንን አጽንተን ለምከታ**

**አሸናፊ ነን**

**የህ.ወ.ሓ.ት ጽ/ቤት**

**መስከረም 30/2013**